ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

እሁድ | 82ኛ ዓመት ቁጥር 274 ሰኔ 4 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00 | ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!


## “የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ፈተናዎችን በመቋቋም አዎንታዊ እድገት ማስመዝገቡን ቀጥሏል”

ለገሰ ቱሉ (ዶ/ር) የመንግስት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስትር



ፎቶ - እዮብ ተፈሪ

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ሁሉንም ዓይነት ጫናዎች በመቋቋም አዎንታዊ ዕድገት ማስመዝገብ መቀጠሉንና ኢኮኖሚውን ከዳግም ስብራት ወደ ላቀ የእድገት ምህዋርነት በመቀየር በ2023 ዓ.ም ጠቅላላ የአገር ውስጥ ምርት 156 ነጥብ 08 ቢሊዮን ዶላር እንደሚጠበቅ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የመንግስት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት አስታወቀ፡፡ግጭት የዜጎችን ደህንነት አደጋ ላይ እንዳይጥል ከሂሳብ ማወራረድ የጥላቻ መንፈስ ለመውጣት አቅጣጫ ተቀምጦ ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑን አመልክተዋል፡፡

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የመንግስት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስትር ለገሰ ቱሉ (ዶ/ር) ወቅታዊና ቀጣይ የመንግስት የትኩረት አቅጣጫዎችን አስመልክተው በሰጡት መግለጫ፤ ሰሞኑን ጠቅላይ ሚኒስትሩን ጨምሮ የአገሪቱን ከፍተኛ አመራሮች ያሳተፉ መድረኮች መካሄዳቸውንና በተለይ በሁለተኛው አገር በቀል የኢኮኖሚ ሪፎርም አገራዊ የኢኮኖሚ ልማትና ብልጽግና ማስፈጸሚያ የመካከለኛ ዘመን ረቂቅ እቅድ ላይ ሰፊ ውይይት

“የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## የኢፕድ ስልጠና ማዕከል የአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ አመራሮችና ባለሙያዎችን አሰለጠነ

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የስልጠና ማዕከል “አገልጋይ ስብዕና ለውጤት” በሚል መሪ ሀሳብ ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ንግድ ቢሮ አመራሮችና ባለሙያዎች ስልጠና ሰጥቷል።

ስልጠናው ትናንትና በኤሊያና ሆቴል ሲሰጥ በንግግር የከፈቱት የቢሮው የሰው ሀብት ልማት ዳይሬክተር አቶ ዳንኤል ሚኢሳ እንደተናገሩት፤ “አገልጋይ ስብዕና ለውጤት” በሚል መሪ ሀሳብ የቢሮው አመራሮችና ባለሙያዎች በኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የስልጠና ማዕከል መሰልጠን ጀምረናል።

የኢፕድ ስልጠና ማዕከል ያቀረበልን አሰልጣኞች ብቁ እና በዘርፉ ልምድ ያላቸው ናቸው ያሉት ዳይሬክተሩ፤ ከዚህም ባለፈ ታዋቂና የተመሰከረላቸው አሰልጣኞች በመሆናቸው የቢሮውን ሥራ ቀልጣፋና ምቹ የሚያደርግ ክህሎት እንደሚያገኙበት ተናግረዋል።



ፎቶ - አሸናፊ ጉደታ

ለዚህም ኢፕድን ማመስገን ይገባል ያሉት ዳይሬክተሩ፤ ይህ ስልጠና ከዚህ በፊት ከሚሰጠው ስልጠና የተለየ ችሎታን የሚያላብስ በመሆኑ የቢሮው አመራሮችና ባለሙያዎች ከስልጠናው ያገኙትን በሥራ ቦታ ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል ብለዋል።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ጌትነት ታደሰ በበኩላቸው፤ በኢፕድ የስልጠና

የኢፕድ ስልጠና ማዕከል... ወደ ገጽ 4 ዞሯል










### “የቤት ግብር ተመኑ ድንገተኛና የወቅቱን የኑሮ ሁኔታ ያላገናዘበ ነው”

\- ነዋሪዎች

### “ተመኑ ጥናትን መሠረት ያደረገ ነው፤ ቅሬታ ያላቸው የሚያቀርቡበት አሠራር አለ”

\- የአዲስ አበባ ገቢዎች ቢሮ

ገጽ 4

## “ሠራዊታችን ስተፈናቀሉ የሚረዳ እንጂ ተቸግሮ ከአሰራር ውጪ የሚጠቀም አይደለም”

-የኢፌዴሪ መከላከያ ሚኒስቴር

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ሠራዊታችን በቂ ሎጅስቲክ ያለው በዓለም አቀፍና በሀገር ውስጥ ለተፈናቀሉትና በድርቅ ለተጎዱት በዓይነትና በገንዘብ የሚረዳ እንጂ ተቸግሮ ከአሰራር ውጪ የሚጠቀም አይደለም ሲል የኢፌዴሪ መከላከያ ሚኒስቴር ገለጸ፡፡

የኢፌዴሪ መከላከያ ሚኒስቴር ትናንት በሰጠው መግለጫ እንዳስታወቀው፤ ዩኤስኤአይዲ (USAID) ሰሞኑን አጣርቻለሁ ብሎ ባወጣው መግለጫ ለሰብአዊ እርዳታ የመጣን እህል ከሌሎች መንግስታዊ አካላት ጋር በመሆን መከላከያ ሠራዊታችንም እንደተጠቀመ አድርጎ ያቀረበውን ሪፖርት የተለያዩ ሚዲያዎች ሲዘግቡት አስተውለናል፡፡ ይሁንና ሠራዊታችን በቂ ሎጂስቲክ ያለው በዓለም አቀፍና በአገር ውስጥ ለተፈናቀሉትና በድርቅ ለተጎዱት በዓይነትና በገንዘብ የሚረዳ እንጂ ተቸግሮ ከአሰራር ውጪ የሚጠቀም አይደለም፡፡

የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት በጥብቅ ዲስፕሊን የሚመራ ዘመናዊ ሠራዊት ነው ያለው መግለጫው፤ ሰብዓዊ ድጋፍ የሚደረግላቸውን ወገኖቹን ቀለብ ሊቀማ

“ሠራዊታችን ስተፈናቀሉ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል






አቶ ኡቶ ኡኮት

# ጋምቤላ ክልል ወደ ቀድሞው ሰላማዊ ሁኔታው ተመልሷል

መክሊት ወንድወሰን

አዲስ አበባ፡- በጋምቤላ ክልል ባሳለፍነው ሳምንት ተከስቶ የነበረው ግጭት ተረጋግቶ አካባቢው በአሁኑ ወቅት ወደቀደመ ሰላሙ መመለሱን የክልሉ ሰላምና ጸጥታ ቢሮ ገለጸ። በኅብረተሰቡና በጸጥታ አካላት ርብርብ በስርቆት እና ንጥቂያ የወንጀል ድርጊት ውስጥ የተሰማሩ 32 ተጠርጣሪዎች ተይዘዋል።

የጋምቤላ ክልል ሰላምና ጸጥታ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ ኡቶ ኡኮት ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር ባደረጉት ቆይታ፤ ክልሉን ወደነበረበት ሰላምና ጸጥታ ለመመለስ ሥራዎችን በመሥራት ተፈጥሮ የነበረውን ግጭት ማረጋጋት መቻሉን ተናግረዋል።

በክልሉ በተለያዩ አካባቢዎች ተፈጥሮ በነበረው ግጭት የዘጠኝ ሰዎች ህይወት ማለፉን እና 17 ሰዎች ላይ ጉዳት መድረሱን የገለጹት አቶ ኡቶ፤ በተያዘው ሳምንት በክልሉ ተነስቶ የነበረውን ግጭት ማረጋጋት መቻሉን አብራርተዋል።

አቶ ኡቶ እንደገለጹት፤ ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታት ሕዝቡን በማቀራረብ እና በማወያየት ችግሮች በሰላማዊ መንገድ ብቻ እንዲፈቱ ለማስቻል እንደሚሰሩም ገልጸዋል። አያይዘውም ቢሮው ግጭቶችን አስቀድሞ ለመከላከል እንዲቻል በክልሉ ግጭቶች ይነሳባቸዋል ተብሎ የሚገመቱ ቦታዎች ላይ ትኩረት በማድረግ፤ ሰላምና መረጋጋትን ለመፍጠር እየሠሩ እንደሚገኙ ገልጸዋል።

በሌላ በኩል በስርቆት እና ንጥቂያ የወንጀል ድርጊት ላይ ተሳትፈዋል ተብለው የተጠረጠሩ ግለሰቦችን ከአካባቢው ማኅበረሰብ ጋር በመተባበር በቁጥጥር ሥራ የማዋል ተግባር መጀመሩን አስታውቀዋል።

አቶ ኡቶ በዘላቂነት በክልሉ የሚደርሱ ወንጀሎችን ለመከላከል ኅብረተሰቡን በማወያየት አካባቢያቸውን እንዲጠብቁና ወንጀለኞችን ለህግ አካላት አሳልፈው እንዲሰጡ ለማስቻል ሥራዎች መሠራታቸውን ተናግ ረዋል። በዚህ ርብርብም በአንድ ሳምንት ውስጥ 32 የሚሆኑ ተጠርጣሪዎች እንደተያዙ ገልጸዋል።

በክልሉ በስፋት የሚታየው የተደራጀ ዘረፋ አለመሆኑን የሚገልጹት አቶ ኡቶ፤ ስርቆት እና ንጥቂያዎች መኖራቸውን በመጠቆም፤ ይህንን ለመከላከልም የሁለት እግር ተሽከርካሪዎች ከምሽቱ ሦስት ሰዓት እስከ ንጋት 12 ሰዓት እንዳይንቀሳቀሱ እገዳ መደረጉን ተናግረዋል።ይህም በሞተር ሳይክሎች የሚፈጸሙ ወንጀሎችን ለመከላከል ጊዜያዊ መፍትሄ እንደሚሆን አክለዋል።

የወንጀል ድርጊቶቹን ለመከላከል ኅብረተሰቡን ማሳተፍ አስፈላጊ ነው ያሉት ኃላፊው፤ ከወጣቶች ጋር ውይይት በማድረግና የግንዛቤ ማስጨበጥ ስራ በመስራት ተደራጅተው አካባቢያቸውን እንዲጠብቁ ለማድረግ መቻሉን ተናግረዋል።

ከዚህ በተጨማሪም በክልሉ የተደራጀ የፓትሮል ስራዎች ተጀምሯል ያሉት አቶ ኡቶ ፤ ሥራው ከተጀመረ ጀምሮ ምንም አይነት የወንጀል ሪፖርት አለመመዝገቡን አክለዋል። በክልሉ ድንበር አልፈው የሚገቡ ህገወጥ ግለሰቦችን ለማስቆምም ከሚሊሻና ከፌዴራል የጸጥታ አካላት ጋር በመቀናጀት ሰላምን የማስከበር ስራዎች እየተሰሩ መሆናቸውን ተናግረዋል።

ሰላምና ጸጥታ የሚረጋገጠው በህግ አስከባሪ አካላት ብቻ አለመሆኑን የተናገሩት አቶ ኡቶ፤ ኅብረተሰቡ በንቃት አካባቢውን መጠበቅ እንዳለበት እና ለህግ አስከባሪ አካላት ትብብር በማድረግ የበኩሉን አስተዋጽኦ እንዲያበረክት አሳስበዋል።

# ለሀገራዊ ምክክሩ ስኬታማነት የበኩላቸውን ሚና ለማበርከት መዘጋጀታቸውን አባገዳዎች ገለጹ

መዓዛ ማሞ

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ ዘላቂ ሰላም ለማምጣት በመጪው ዓመት ለሚደረገው ሀገራዊ ምክክር ስኬታማነት የላቀ ሚና ለማበርከት መዘጋጀታቸውን አባገዳዎች ገለጹ።

የቱለማ አባገዳ እና የኦሮሞ አባገዳዎች ሕብረት ጸሀፊ አባገዳ ጎበና ሆላ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ሀገር ለመውረር የመጣውን ጠላት በጋራ አሸንፈው የሀገርን ሉዓላዊነት አስጠብቀው ያቆዩአት ሀገር ናት። ይህችን ሀገራችንን ለማስቀጠል እና አንድነታችንን ለማጠናከር ለሚደረገው ሀገራዊ ምክክር ስኬታማነት የበኩላችንን ለማበርከት ተዘጋጅ ተናል።

በምክክር የማይፈታ ነገር ባለመኖሩ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚፈጠሩ የእርስ በርስ ሽኩቻዎች በሀገራዊ ምክክሩ እንደሚፈቱ እምነታቸው መሆኑን ተናግ ረው፤ የኦሮሞ አባ ገዳዎች ምክክሩ ስኬታማ እንዲሆን የበኩላቸውን ድጋፍ እንደሚያደርጉ ገልጸዋል።

የሃይማኖት መሪዎች፣ታዋቂ ግለሰቦች፣ምሁራን እንዲሁም ለኢትዮጵያ አንድነት እና ለሕዝቦቿ ሰላም የሚያስቡ ሁሉ ለሀገራዊ ምክክሩ መሳካት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ማድረግ እንዳለባቸውም ጠቁመዋል።

በኢትዮጵያ ዘላቂ ሰላም ለማስፈን ሊደረግ የታቀደው ሀገራዊ ምክክር በጣም አስፈላጊ ነው ያሉት አባ ገዳ ጎበና፤ አሁን በሀገራችን እየታየ ያለውን አሳሳቢ ችግር ለመቅረፍ ተጨማሪ ጊዜ ሳይጠየቅ በተቻለ ፍጥነት መከናወን እንዳለበትም ተናግረዋል።

ምክክሩ በሃሳብ ለመግባባት፣እውነታውን



አባገዳ አልይ መሀመድ ስሩር

ለመ ለየት እና የተሰሩ ስህተቶች ተመልሰው እንዳይደገሙና ሀገሪቱ ወደ ቀጣይ የዕድገት ምዕራፍ እንድትሸጋገር እጅግ አስፈላጊ መሆኑን የተናገሩት አባገዳው፤ ዘላቂ ሰላም ማምጣት ለአንድ ወገን የሚተውና ጊዜ የሚሰጠው ጉዳይ ባለመሆኑ ሁሉም ዜጋ ተሳትፎ በማድረግ ለምክክሩ ውጤታማነት የበኩሉን አስተዋጽኦ ማድረግ እንዳለበት አስገንዝበዋል።

የሲኮ ማንዶ አባገዳ የሆኑት አባገዳ አልይ መሀመድ ስሩር በበኩላቸው፤ ሀገራዊ ምክክሩ በማንግባባቸው አንዳንድ ጉዳዮች ዙሪያ ተቀምጠን ተነጋግረን ችግሮችን ለመፍታትና ለሀገር ዘላቂ ሰላም ለማምጣት ፋይዳው የጎላ እንደሆነ ገልጸው፤ ምክክሩ ግቡን እንዲመታ አባ ገዳዎች በየአካባቢያቸው የላቀ ሚና ለማበርከት ዝግጁ እንደሆኑ ተናግረዋል።

ይህቺ ሀገር ያሉባትን ችግሮች ፈትተን ልናስቀጥላት የምንችለው በመመካከር ነው ያሉት አባገዳው፤ በምክክሩ ላይ ላለመግባባት ምክንያት የሆኑ አጀንዳዎችን በማቅረብ በግልጽነት መወያየት ከተቻለ ችግሮች ተፈተው በሀገራችን ዘላቂ ሰላም ሊሰፍን እንደሚችል አመልክተዋል።

ከዚህ ቀደም ከሀገራዊ ምክክር ኮሚሽኑ ጋር ውይይት ማድረጋቸውን ያስታወሱት አባገዳው፤ በቀጣይም ለምክክሩ ውጤታማነት ማኅበረሰቡ በንቃት እንዲሳተፍ እና ችግሮችን ፊት ለፊት አምጥቶ እንዲወያይ በማድረግ አባገዳዎች ከምክክር ኮሚሽኑ ጎን መቆም እንዳለባቸውና ለዚህም ዝግጁ መሆናቸውን ተናግረዋል።

እርስ በርስ መገዳደል እና መፈናቀል እንዲቆም ነው የምንፈልገው የሚሉት አባገዳ አልይ፤ ከሰላም እንጂ ከጦርነት የሚገኝ ትርፍ እንደሌለ ባለፉት ዓመታት ተመልክተናል። ከዚህ ትምህርት በመውሰድ ሁሉንም ችግሮች በሰላማዊ መንገድ በምክክር ለመፍታት ማኅበረሰቡ መዘጋጀት እንዳለበት ተናግረዋል።

# በሳይንስና ቴክኖሎጂ ፈጠራ ሥራዎች የልምድ ልውውጥ የተደረገበት አውደ ርዕይ ዓላማውን አሳክቷል

ማህሌት ብዙነህ

አዲስ አበባ፡- በሳይንስና ቴክኖሎጂ ፈጠራ ሥራዎች ለሶስት ቀናት የልምድ ልውውጥ የተደረገበት አውደ ርዕይ ዓላማውን ማሳካቱን የአዲስ አበባ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ገለጸ፡፡ 8ተኛው ከተማ አቀፍ የሳይንስ ፈጠራ አውደ ርዕይ ትናንት ተጠናቋል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ኃላፊ ዶክተር ዘላለም ሙላቱ በመርሀ- ግብሩ ማጠናቀቂያ ላይ እንደገለጹት፤ አውደ- ርዕዩ ተሳታፊዎችን በተወዳዳሪነት መንፈስ ያሳተፈና ችግር ፈቺ የፈጠራ ሥራዎችን ለኅብረተሰቡ በማሳየት ጥሩ የልምድ ልውውጥ የተደረገበት በመሆኑ የተያዘለትን ዓላማ ያሳካ ነው፡፡

መድረኩ በሳይንስና ቴክኖሎጂ ፈጠራ ሥራዎች ልምድና ዕውቀት ያካበቱና የተሻለ የፈጠራ ሥራ ይዘው ለቀረቡ መምህራንና ተማሪዎች እውቅና የሚሰጥበት መሆኑን አመልክተው፤ አውደ-ርዕዩ ለቀጣይ ሥራ የሚያበረታታና በሌሎች ላይ ከፍተኛ ተነሳሽነት በመፍጠር ተሳትፎ የሚጨምር በመሆኑ ድርሻው ከፍተኛ ነው ብለዋል፡፡

አሁን ላይ ለትውልድ በምንሰጠው ልዩ ትኩረት ለነገ ሀገር መበልጸግ ትልቅ ሚና አለው ያሉት ዶክተር ዘላለም፤ይኸው አውደ ርዕይ በከተማዋ የሚገኙ ትምህርት ቤቶች መምህራንና ተማሪዎች በሳይንስና ቴክኖሎጂ የታገዘ ትምህርት እንዲማሩ ምቹ ሁኔታ በመፍጠርና ጤናማ የሆነ የውድድር መንፈስ በማላበስ የልምድ ልውውጥ እንዲኖር ለማስቻል የታለመ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

ይህ በወዳጅነት አደባባይ የተካሄደው ከመ ንግስትና ከግል የትምህርት ተቋማት የተወጣጡ መምህራንና ተማሪዎች የተሠሩ የፈጠራ ሥራዎች የቀረቡበትና የተጎበኙበት መድረክ በተሰጠው ዳኝነት መሰረት የተሻለ ውጤት ላመጡ ተሳታፊዎች እውቅና ተሰጥቷል፡፡



ፎቶ፡- ዳኜ አበራ

በሽልማቱም የመጀመሪያና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት በአማርኛ ስርአተ ትምህርት ዘጠኝ ተማሪዎችና ስምንት መምህራን፣ በአፋን ኦሮሞ ዘጠኝ ተማሪዎችና ስድስት መምህራን በድምሩ 18 ተማሪዎችና 14 መምህራን እውቅና አግኝተዋል፡፡ ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት 15 ተማሪዎች እና 13 መምህራን በሰሩት የፈጠራ ሥራ እውቅና ተሰጥቷቸዋል፡፡

በተጨማሪ ከአዳሪ ትምህርት ቤቶች የተሻለ የፈጠራ ስራ ያቀረቡ ዘጠኝ ተማሪዎች እና ሁለት መምህራን እውቅና ያገኙ ሲሆን፤ በልዩ ፍላጎት የትምህርት ዘርፍ አራት ተማሪዎች እና ሶስት መምህራን የእውቅና ሽልማት ተበርክቶላቸዋል፡፡

በ8ተኛው ዙር ከተማ አቀፍ የሳይንስ ፈጠራ ስራ ውድድር አጠቃላይ ከተወዳደሩ 11 ክፍለ ከተሞች ውስጥ የለሚኩራ ክፍለ ከተማ የአንደኛ ደረጃ በመያዝ አሸናፊ ሆኗል፤ የካ ክፍለ ከተማ ሁለተኛ እንዲሁም ንፋስ ስልክ ክፍለከተማ የሦስተኛ ደረጃ በመያዝ ውድድሩን አጠናቀዋል፡፡

ለተከታይ ሶስት ቀናት‹ በሳይንስና በቴክኖሎጂ የዳበረ ትውልድ ለሀገር ብልጽግና › በሚል መሪ ቃል ሲካሄድ የቆየው አውደ ርዕይ ዓላማውን ባሳካ መልኩ ተጠናቋል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## ጥቂት መዘናጋት ትልቅ ዋጋ ያስከፍላል!

በዓለም አቀፍ ደረጃ የ40 ሚሊዮን ሰዎችን ሕይወት ለመቅጠፍ ሁለት አስርተ ዓመታት ብቻ የበቃው ኤች አይ ቪ ኤድስ በኢትዮጵያ ከጫፍ ጫፍ አካሎ 134 ሺህ ሰዎችን ሕይወት ለመንጠቅ ብዙ ጊዜ አልፈጀበትም። ቫይረሱ በኢትዮጵያ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ እንደተገኘ በይፋ ከተነገረ አራት አስርተ ዓመታት ተቆጥረዋል። በነዚህ ዓመታትም እስካለፈው 2014 ብቻ ከ744 ሺህ በላይ ሕፃናትን ያለወላጅ አስቀርቷል።

በኢትዮጵያ የቫይረሱ ስርጭት ፍጥነት ጣሪያ የነካው በ1988 ነው። ከዚያ በኋላም የስርጭቱ ፍጥነት በአገር አቀፍ ደረጃ ለተወሰኑ ዓመታት የመቀነስ አዝማሚያ ማሳየቱን ቢነገርም አሁን ላይ ከ610 ሺህ በላይ ዜጎች ከቫይረሱ ጋር እንደሚኖሩ በጥናት የተደገፉ መረጃዎች ይጠቁማሉ። በቫይረሱ እየተያዙ ካሉት ዜጎች 70 መቶ የሚሆኑት አምራች ኃይሎች መሆናቸው ደግሞ ችግሩን እጅግ አሳሳቢ ያደርገዋል።

በአዲስ መልክ ከሚያዙት የኅብረተሰብ ክፍሎች ዕድሜያቸው ከ15 እስከ 30 ያሉ ዜጎች 70 በመቶውን መያዛቸው ወጣቱ ትውልድ ምን ያህል እንደተዘናጋ አስረጂ ነው። ስርጭቱን ይበልጥ አስከፊ ያደረገው ሌላው ጉዳይ ደግሞ በሴቶች የሚበረታ መሆኑ ነው። የቅርብ ጊዜ ጥናቶች እንደሚጠቁሙት 1.4 በመቶ በሃገሪቷ ባሉ ሴቶች የታየው የስርጭት ብዛት በወንዶች ቀንሶ 0.8 በመቶ ነው። ከ15-19 ዓመት እድሜ ክልል ውስጥ ያሉ ሴቶች 0.2 በመቶዎቹ ቫይረሱ በደማቸው ይገኛል። በተመሳሳይ የዕድሜ ክልል የሚገኙ ወንዶች በአንፃሩ ተጋላጭነታቸው ዜሮ ነው። በወጣትነት እድሜም ቢሆን በሴቶች የሚጎላው የቫይረሱ ስርጭት ከ25- 29 የእድሜ ክልል ያሉ ወጣት ሴቶች ላይ ሲሆን፣ 2.9 በመቶዎቹ ቫይረሱ በደማቸው እንዳለ ሲረጋገጥ በተመሳሳይ እድሜ በወንዶች የታየው ስርጭት መጠን 0.9 በመቶ ነው።

በኢትዮጵያ ቫይረሱን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር ባለፉት 30 እና 40 ዓመታት ብዙ ሥራ ተሠርቷል። በተሠራው ሥራ ልክም ስርጭቱን መቀነስ ቢቻልም በአሁኑ ወቅት ቫይረሱ እንደጠፋ የሚያስበው መብዛቱን በተለይም ወጣቱ ትውልድ መዘናጋቱን ከተጠቀሰው ቁጥር የበለጠ ማሳያ አይኖርም። የቫይረሱ ስርጭት ወጣት እና አፍላ ዕድሜ ላይ የሚገኙ ዜጎች ላይ እየጨመረ የመጣበት ዋነኛ ምክንያትም መዘናጋት ነው።

የቫይረሱ ሥርጭት በሀገር ደረጃ ከአንድ በመቶ በታች መሆኑን የሚጠቁሙ መረጃዎች ቢኖሩም በአንዳንድ ክልሎች ስርጭቱ እያደገ መጥቷል። ስርጭቱ አምራች ዜጎችና ሴቶች ላይ መጨመሩ ደግሞ ወደፊት እንደ ወረርሽኝ መልሶ እንዲያገረሽ ይበልጥ ዕድል መስጠቱ አስከፊው ጉዳይ ነው።

ስለቫይረሱ ሁለገብ እውቀት በበቂ ሁኔታ አለመዳረስ ለስርጭቱ መመንደግ ትልቁን ድርሻ ይወስዳል። ለዚህም ኤች አይ ቪን በተመለከተ በቂ የሚባል ግንዛቤ እና ዕውቀት ያላቸው ሴቶች ከጠቅላላው ቁጥራቸው 19 በመቶ ብቻ መሆኑን ልብ ማለት ያሻል። ልቅ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ፣ ኮንዶምን ሁልጊዜና በአግባቡ አለመጠቀም ብዙዎችን ለቫይረሱ ተጋላጭ አድርጓል። በሴተኛ አዳሪዎች ያለው የቫይረሱ ስርጭት 25 በመቶ ደርሶ አሁንም ግብረሥጋ ግንኙነት ከሚፈጽሙ ወንዶች መካከል 64 በመቶዎቹ ሴተኛ አዳሪዎችን እንደሚጎበኙ በጥናት የተገፉ መረጃዎች እያሳዩ ነው።

ኤች አይ ቪ በኢትዮጵያ መልሶ ሊያገረሽ ወደማይችልበት ደረጃ አልወረደም። ለዚህ ደግሞ ወጥ የኮንዶም ስርጭት አሠራር አለመዘርጋት እና የማሰራጫ ጣቢያዎች የክትትል ሥርዓት አለመኖር ችግሩን በበቂ መንገድ መከላከል እንዳይቻል አድርጓል።

በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የምርመራ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ቁጥር አነስተኛ መሆንና የፀረ ኤች አይ ቪ መድኃኒት ከሚያስፈልጋቸው ለ13 በመቶዎቹ ብቻ መድረሱ የቫይረሱን ቁጥር ለመጨመር እንደ ምክንያት ናቸው።

ዛሬ ላይ ተጋላጭነቱ እየጨመረ በሚገኘው ወጣቱን ትውልድ ለማንቃት የግንዛቤ ማስጨበጫና የባሕሪ ለውጥ ሥራዎች በተለያዩ ጊዜና በተለያዩ አካባቢዎች በልዩ ሁኔታ መስጠት የግድ የሚልበት ደረጃ ላይ ተደርሷል። ከዚህ ቀደም ማኅበረሰቡን በማንቃት ረገድ ከሚሠራው አንጻር አሁን ላይ በጣም ተቀዛቅዟል። በመሆኑም የመንግሥት ተቋማት፣ ኅብረተሰቡና መገናኛ ብዙኃን ከሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ጋር በመሆን ከምርመራ ባሻገር የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራዎችን በስፋት ሊሠሩ ይገባል።

በተለየ ሁኔታ ለቫይረሱ ተጋላጭ ናቸው በተባሉት ዜጎች ማለትም ሴተኛ አዳሪዎች፣ አደንዥ ዕጽ ተጠቃሚዎችና የረጅም ርቀት ሹፌሮች ላይ የሚያተኩር ሥራ ከምንጊዜውም በላይ ትኩረት ሰጥቶ መሥራት ያስፈልጋል። ቫይረሱ ያለባቸውን ሰዎች በምርመራ የመለየት፣ ተገቢውን ሕክምናና ክትትል እንዲያገኙ የማድረግና የቅድመ-መከላከል ሥራዎች ይበልጥ ተጠናክረው ሊቀጥሉ ይገባል።

ፍትሐዊ የኤች አይ ቪ ሕክምና አገልግሎትን ለሁሉም ተደራሽ ለማድረግም ከመቼውም ጊዜ በላይ በትኩረት ሊሠራ ይገባል። ጥቂት መዘናጋት እኤአ በ2030 ኤች አይ ቪ ኤድስ የጤናና የማኅበራዊ ችግር እንዳይሆን የተቀመጠውን ግብ ለማሳካት እንቅፋት ይሆናል። በአጠቃላይ በዚህ ጉዳይ መዘናጋት እንደ ሃገር ትልቅ ዋጋ ያስከፍላልና ዛሬም ትኩረት ለኤች አይ ቪ ኤድስ!


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፦ epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፦ ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ምርትም ሰላምም ይመረት

ወጋሶ

አንዲት አገር ምርታማነቷ የሚገለጸው በተለያየ ዘርፍ ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ የተለያዩ ቴክኖሎጂን በመጠቀም በግብርናው ዘርፍ የተሻለ በማምረት ውጤታማ ልትሆን የምትችል አገር እንዳለች ሁሉ በኢንዱስትሪው ዘርፍ ደግሞ ብዛትና ጥራት ያለው ምርት በማምረት በዓለም አቀፍ ደረጃ ተደራሽነቷን የምታሰፋ አገር ልትኖር ትችላለች።

ከምርታማነት አኳያ ሲታይ ደግሞ በተለይም የኢንዱስትሪ መስፋፋት ጠቀሜታው ዘርፈ ብዙ ነው። አንዲት አገር የትኛውንም የምርት አይነት በጥራትና በብዛት ማምረት የሚያስችላትን አቅም ስታዳብር የዜጎቿን ጥያቄ ለመመለስ አትቸገርም፡ የኢንዱስትሪ መስፋፋትም በመጀመሪያ ከተሞች በተገባቸው ልክ የማደግና የመስፋፋት እድል እንዲኖራቸው ከማድረጉም ሌላ የወጣቶችን የሥራ አጥነት ችግር ይፈታል።

እንደሚታወቀው በአሁኑ ወቅት አገራችንን እየፈተናት ያለው የውጭ ምንዛሪ እጥረት ችግር እንደመሆኑ በከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ተገዝተው ወደአገር የሚገቡ ምርቶችን በአገር ውስጥ በማምረት ይወጣ የነበረውን ወጪ ማዳን ይቻላል። በአገራችን እየተመረተ ያለው የግብርና ምርትን ከኢንዱስትሪው ጋር በማስተሳሰርም ሁነኛ ግብዓት እንዲያገኝ ስለሚያደርግ አርሶ አደሩንም ተጠቃሚ በማድረጉ በኩል አይነተኛ ሚና እንዳለው የሚታወቅ ነው።

ይህን በአግባቡ የተረዳው መንግሥትም ከዓመት በፊት «ኢትዮጵያ ታምርት» በሚል መሪ ሐሳብ ያስጀመረው ንቅናቄ ከኢንዱስትሪው ዘርፍ ሊገኝ የሚችለውን ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ ለመቋደስ የሚያስችል እንደሆነ እሙን ነው። በቅርቡም ንቅናቄው የተጀመረበትን የመጀመሪያ ዓመት ምክንያት በማድረግ በሚሊኒየም አዳራሽ አንድ መርሐ ግብር መካሔዱም ይታወቃል።

እርግጥ ነው ኢትዮጵያ ልታሳካ ከያዘችው የብልጽግና እቅድ አኳያ ሲታይ የ«ኢትዮጵያ» ታምርት ንቅናቄ የጀርባ አጥንት ነው። የዚህ የንቅናቄው ዓላማም በኢንዱስትሪው ዘርፍ ያለውን ችግር ለመፍታት እና ምርታማነትን ማሳደግ ነው። ይህ በራሱ በጎ ሐሳብ ሲሆን፣ ለተፈጻሚነቱ ግን ቅድመ ሁኔታዎች መኖራቸው የማይዘነጋ ጉዳይ ነው።

ስለዚህ ኢትዮጵያ ኢንዱስትሪዎቿ በሙሉ አቅማቸው እንዲያመርቱ አስተማማኝ የግብዓት አቅርቦትን ይሻሉ። በዚህ በኩልም በአገራችን እየተደረገ ያለ ጥረት የሚያበረታታ ነው። በተለይም በግብርናው ዘርፍ ምርታማነትን ለማሳደግ እየተጣለ ያለ መሠረት ላይ ሁሉም የየበኩሉን ሊያበረክት ግድ ነው። በአንድ ዓይነት የአመራረት ሥርዓት ላይ የሙጥኝ ብለን የኢትዮጵያን ብልጽግናን ለማረጋገጥ አይቻልም። ግብርናን ዘመናዊ በሆነ ቴክኖሎጂ በመደገፍ ሁለትና ሦስት እርምጃ ወደፊት ማስፈንጠር ይቻላል። ይህ እድል ያለው በእጃችን ነው። እውነት ለመናገር ደግሞ አገራችን የውሃም ሆነ የመሬት ችግር የለባትም። የዚህ መኖር «ኢትዮጵያ ታምርት» ለሚለው ንቅናቄ ያው አስተዋፅዖ ላቅ ያለ ነው።

ከዚህ ጎን ለጎን የተፈጥሮ ሀብቱን ብቻ ስለተቸርን የሚመጣ ተዓምር የለምና በሰለጠነ የሰው ኃይል የተሻልን ሆነን መገኘት የግድ ነው። ይህ ደግሞ ተነሳሽነትን እንጂ የተለየ ወይም በሌላ አገር ሄዶ መሰልጠንን የግድ አይልም። ዋናው ነገር አገርን በማሳደጉ ረገድ በሚደረገው ርብርብ ውስጥ ራስን ተሳታፊ በማድረግ የሚጠበቅብንን አስተዋፅዖ ለማበርከት መዘጋጀት ነው።

ይህ በእርግጥ ቅንጅታዊ የሆነ አሠራርን ይፈልጋል። አንዱ በግብርናው ዘርፍ ሌላው ደግሞ በኢንዱስትሪው ዘርፍ መሳተፍ ሲችል (ማዕድንም ሌላው ሀብታችን መሆኑ ሳይዘነጋ) የሰመረ ውጤት ማስመስገብ ይቻላል። ለሁለቱም ዘርፎች ስኬታማነት የኃይልም ሆነ የብድር አቅርቦቱ ተፈላጊ በመሆናቸው በዚህ ረገድ ያለው እንቅስቃሴም ለ«ኢትዮጵያ ታምርት» ንቅናቄ ዋናዎቹ መሆናቸው እሙን ነው።

ኢትዮጵያ በዜጎቿ ቀና ቅንጅት እንዲሁም ባሏት ኢንዱስትሪዎች በሙሉ አቅሟ ማምረት ትጀምር እንጂ በቀጣናው ያሉ አገራትም ሆኑ በአህጉሩ ያሉ አገሮች ብሎም ከአህጉራችን ውጪ ያለው የገበያ እድል በርካታ ነው። ብዙ ሩቅ መሄድ ሳያስፈልግ ከሩቅ ምሥራቅ ወደ አህጉራችን በገፍ የሚገባ ምርትን መተካት ለመቻል መሥራት በራሱ አንዱ በቅርብ ያለ የገበያ ዕድል መሆን የሚችል ነው።

> ‹‹ኢትዮጵያ ታምርት›› ንቅናቄ የበለጠ ጎልብቶ በእርግጥም ኢትዮጵያ በኢኮኖሚዋ እንድታንሰራራም እንድትበለጽግም ወሳኙ ሰላምም ጭምር ነው። ስለሆነም ሰላም ለኢትዮጵያችን፣ ሰላም ለቀጣናችን፣ ሰላም ለአህጉራችን እና ለዓለማችን መሆኑ የግድ ነው

ኢትዮጵያ በደንብ ስታመርት ዋናውና አሁናዊ አንገብጋቢ ጉዳይ የሆነው የሥራ አጥነት ጥያቄን በአግባቡ መመለስ ይቻላል። ኢኮኖሚዋም የሚያንሰራራ ከመሆኑም ባሻገር በብዙ ደጅ ጥናት የሚገኘውን የውጭ ምንዛሪን ለማግኘት ዋና በር መሆን ይችላል። ስናመርት የሥራ እድልን መፍጠር ብቻ ሳይሆን የሥራ ባሕልንም ጭምር እያዳበርን መሄድ ያስችለናል። ይህ ብቻ አይደለም፤ የአገራችን ሕዝብም የአኗኗር ዘይቤው ይቀየራል።

ኢትዮጵያ የኢንዱስትሪ ምርታማነቷ ከዓመት ዓመት እየተሻሻለ ሲመጣ ግብ አድርጋ የያዘችው እቅድ ስኬታማ መሆን ይችላል። በቀጣዮቹ ዘጠኝ እና አስር ዓመታት በኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ የኢንዱስትሪው አገራዊ የምርት ድርሻው ከስድስት ነጥብ ዘጠኝ በመቶ ወደ 17 ነጥብ 2 በመቶ ወደተቀመጠው ግብ መድረሱም አይቀሬ ይሆናል።

ይሁንና ለማምረት አገር ሰላም መሆን አለበት። ይህ ዋና ቁልፍ ጉዳይ ነው። በጥራት እና በብዛት አምርቶና ተወዳዳሪ ሆኖ መገኘት ብቻ የችግር ሁሉ መፍቻ ቁልፍ ሊሆን እንደማይችል ሊታወቅ ይገባል። በጥራትም ሆነ በብዛት የተመረተን ምርት ወደ ዓለም ገበያ ለማድረስም የቀጣናችን ብሎም የአህጉራችን እና የዓለማችን ሰላም መሆን ፋይዳው ወሰን የለውም። ምክንያት ቢባል ለአምራች ኢንዱስትሪው ሰላም ዋና ቁልፍ ጉዳይ ነው።

ሰላም መሠረታዊ ጉዳይ ነው ለማለቴ ሌላው ማሳያ የማምረቻ ኢንዱስትሪ ዕድገት ሊረጋገጥ የሚችለው ከኢንቨስትመንት መስፋፋት ጋር ተያይዞ በመሆኑ ነው። እንደሚታወቀው ኢንቨስትመንትን መሳብ የሚቻለው የመጀመሪያ የሰላም መረጋገጥ እንደሆነ ግልጽ ነው። ሌላው ደግሞ ሌሎች ለኢንቨስትመንት አስፈላጊ የሆኑ ምቹ ሁኔታዎች ናቸው።

ሐቁን ለመናገር በአንዲት አገር ሰላም ታጣ ማለት የጥይት ድምጽ እየተሰማ ነው ማለት ብቻ እንዳልሆነ የሚታወቅ ነው። ሰላም የለም ለማለት ከሚያስደፍረው መካከል አንዱ ለሌላው ጀርባ ሲሰጥም ጭምር እንደሆነ ልብ ሊባል ይገባል። ሰላም ከእርስ በእርስ ሰላማዊ ግንኙነት የሚጀምር እና አንዱ ለሌላው ቀና ማሰብ ሲችል የጭምር ነው። ሰላም የራስን ዙሪያ ያለማስደፈር ብቻ ሳይሆን ለጎረቤትም ጭምር መሟገት ሲቻል ነው።

ስለዚህም «ኢትዮጵያ ታምርት» ንቅናቄ የበለጠ ጎልብቶ በእርግጥም ኢትዮጵያ በኢኮኖሚዋ እንድታንሰራራም እንድትበለጽግም ወሳኙ ሰላምም ጭምር ነው። ስለሆነም ሰላም ለኢትዮጵያችን፣ ሰላም ለቀጣናችን፣ ሰላም ለአህጉራችን እና ለዓለማችን መሆኑ የግድ ነው። የኢትዮጵያ በሙሉ አቅም ማምረት ደግሞ ለምርታማነት፣ ለልማት ብሎም ለድህነት ቅነሳ ላቅ ያለ አስተዋፅዖ አለውና ከዚህ ምርታማነት ለመቋደስ ሰላም ይብዛልን!!!

# “የቤት ግብር ተመኑ ድንገተኛና የወቅቱን የኑሮ ሁኔታ ያላገናዘበ ነው”

- ነዋሪዎች

# “ተመኑ ጥናትን መሠረት ያደረገ ነው፤ ቅሬታ ያላቸው የሚያቀርቡበት አሠራር አለ”

- የአዲስ አበባ ገቢዎች ቢሮ

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- የከተማ ቤት ግብር “አዲሱ ተመን” አሁን ላይ ያለውን የኑሮ ሁኔታ ያላገነዘበ፣ ኢኮኖሚያቸው ላይም አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያሳድርና በድንገት ወደትግበራ የተገባበት መሆኑን ነዋሪዎች ቅሬታ አቀረቡ። ተመኑ ተግባራዊ ሲደረግ በጥናት ላይ ተመስርቶ እንደሆነና በግል በልዩ ሁኔታ የተቸገረ ካለ ቅሬታ ማቅረብ እንደሚችል የአዲስ አበባ ገቢዎች ቢሮ አስታውቋል፡፡

በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ነዋሪና የከተማ ቤት ግብር ከፋይ የሆኑት አቶ ሙሉቀን ትእዛዙ፤ ተመኑ የመንግስትን ገቢ ከማሳደግ አንጻር ብቻ የታየ የሚመስል፤ ማኅበረሰቡን የበለጠ ለወጪ የሚዳርግ በመሆኑ አሁን ካለው የኢኮኖሚ ሁኔታ አንጻር መታየት አለበት ብለው እንደሚያምኑ ለኢፕድ ገልጸዋል። መንግስት በተለይ የጋራ መኖሪያ ቤትን ለድሃው ማህበረሰብ ነው ያቀረብኩት ቢልም ወቅቱን ታሳቢ ያላደረገ አዲስ የግብር ተመን አውጥቶ ማስከፈሉ ኅብረተሰቡ ላይ የኢኮኖሚ ጫና ያሳድራል ብለዋል፡፡

የመኖሪያ ቤት ግብር ሥራ ላይ ሲውል አሁን ባለው ኢኮኖሚ ላይ ሊያመጣ የሚችለውን አሉታዊ ተጽዕኖ በግልጽ ያገናዘበ አይመስልም ያሉት አቶ ሙሉቀን፤ አሁን ላይ ከፍተኛ የሆነ የቤት እጥረት አለ፡፡

“ስለ መኖሪያ ቤት ግብር ለማወቅ ባደረግኩት ጥረት ልክ በተባራሪ ወሬና በዜና ከመስማት ውጪ መረጃ ሊሰጥ የሚችል የተብራራ ነገር ብዙ የለም።የግብር ተመኑ ላይ ብቻ ሳይሆን አስፈላጊነቱ ላይም በቂ የሆነ ግንዛቤ አልተፈጠረም” ሲሉ ተናግረዋል።በመንግስት ደረጃ የሚወሰኑና ሰፊውን ማኅበረሰብ የሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ጠንከር ያለና ነጻ የሆነ የባለሙያዎች ውይይት ተደርጎ የተሻለ የኢኮኖሚ አማራጭ እንዲኖር መደረግ አለበት ነው ያሉት።መበልጸግና ማደግ የሚቻለው ማህበረሰብ የመቆጠብና ኢንቨስት የማድረግ አቅሙ እንዲሁም አጠቃላይ የኢኮኖሚ ይዞታው ከፍ ሲል ነው።መንግስት ክፍያውን ከማሳደግ ይልቅ እዚህ ላይ በትኩረት ቢሰራ የተሻለ ነው ብለዋል፡፡

ተመኑ ከወጣ በኋላ የክፍያ ሂደቱ በራሱ ችግር አለበት የሚሉት አቶ ሙሉቀን፤ አገልግሎቱ በአንድ መስኮት የሚያልቅ ባለመሆኑ ብዙዎች ለእንግልት መዳረጋቸውን ጠቁመዋል።ክፍያውን በዲጂታል መንገድ ማድረግ እየተቻለ በየቀኑ ለሰልፍ መዳረግ ተገቢ እንዳልሆነና እንዲህ አይነት አሰራሮች ለማጭበርበርና ለሙስና በር ከፋች መሆናቸውን ጠቅሰዋል፡፡

ስማቸው እንዳይጠቀስ የፈለጉት የጉለሌ ክፍለ ከተማ ነዋሪ፤ በመርህ ደረጃ ማንኛውም ነዋሪ መንግስት የሚያስቀምጠውን ግብር የመክፈል ግዴታ እንዳለበት ቢያምኑም፤ ተመኑ የግብር ከፋዩን አቅም ያላገናዘበና የተጠየቀው ክፍያ ከአቅም በላይ መሆኑን ተናግረዋል። “ሀገሪቱ ላይ ባለው የኑሮ ሁኔታ የልጆች ትምህርት ቤት ክፍያ ጨምሯል። ትራንስፖርትና መሠረታዊ ሸቀጦች፣ መብራትና ውሃም ክፍያቸው እየጨመረ ነው።ከዚህ አንጻር ክፍያው ወቅቱን ያገናዘበ አይደለም፤ ግዴታ ስለሆነብን ተበድረንም ቢሆን ልንከፍል እንችላለን፤ ነገር ግን ይህ የኢኮኖሚ ችግር ውስጥ ሊያስገባ የሚችል ነው” ብለዋል፡፡

የመኖሪያ ቤት ግብር ላይ መንግስት ለህዝቡ ግንዛቤን በመፍጠር ረገድ ክፍተቶች መኖራቸውንም ነዋሪው ገልጸዋል።“እኔ ከከፋዮቹ አንዱ ስሆን መረጃውን የሰማሁት ለቅሶ ቤት ሆኜ ነው። ሰፊ የሆነ የግንዛቤ ማስጨበጫ የለም።ቀደም ሲል አንድ ነገር ሲፈለግ ሚዲያዎችን ጭምር ተጠቅሞ ቅስቀሳ ይደረግ ነበር።የቴሌቪዥን ግብር ክፍያ እንኳን ደጋግሞ ያስነግር ነበር።ይህ ደግሞ ከዛ ያለፈ እንደመሆኑና ተመኑም ቀላል ባለመሆኑ ተደጋጋሚ ግንዛቤ ያስፈልገው ነበር” ሲሉ ተናግረዋል።

የአከፋፈል ሁኔታው ላይም ቅሬታ አለን የሚሉት ነዋሪው፤ የመክፈያ ጊዜው አጭር መሆኑ ተጽእኖ እንደፈጠረም አመላክተዋል።“ግንዛቤ ሳይሰጥ በጥድፊያ እንድንከፍል ተደርገናል፤ ሰው የመዘጋጀ ጊዜ እንዲኖረው ከታሰበበት ቀድሞ መጀመር ነበረበት” ነው ያሉት፡፡

ጫናው ቤት ላለው ብቻ ሳይሆን በሁሉም ዜጎች በተለይም በድሃው ማህበረሰብ ላይ ሊያርፍ እንደሚችል ጠቁመዋል።የቤት ኪራይንም ሊጨምር የሚችልና አቅመ ደካሞች፣ በጡረታ የሚኖሩ፣ ሥራ የሌላቸው፣ አነስተኛ ገቢ ያላቸው ወገኖችን ለችግር የሚያጋልጥ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ስሜ አይጠቀስ ያሉት የአሸዋ ሜዳ አካባቢ ነዋሪ በበኩላቸው፤ የልጆች አባትና የቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆናቸውን በመግለጽ፤ ትግበራው ወደእኔም ቢመጣ ፈታኝ ነገር ይገጥመኛል የሚል ስጋት እንዳደረባቸው ተናግረዋል።ከኑሮ ውድነቱ ጋር ተያይዞ ማህበረሰቡ ፈታኝ ህይወት ላይ ነው ያለው። የቤት ኪራይ በተወደደበት በዚህ ወቅት ላይ ችግሩን እንዳያባብሰው መንግስት ይህንና መሰል ጉዳዮችን ታሳቢ ማድረግ የሚችልበት ሁኔታ ሊኖር ይገባል ብለዋል።

መንግስት ለተለያዩ ሀገራዊ ወጪዎች የሚጠቀመው ገንዘብ ከሚሰበስበው ግብር እንደመሆኑ መክፈሉ የዜጎች ግዴታ ነው የሚሉት ነዋሪው፤ ሆኖም ቅድሚያ በዚህ ጉዳይ ዙሪያ ግንዛቤ መፍጠር ያስፈልግ እንደነበር አንስተዋል።

በአዲስ አበባ ከተማ ገቢዎች ቢሮ የታክስ ጉዳዮች ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ ዘገየ በላይነህ፤ ግብሩን ወቅታዊ ከማድረግ በስተቀር አዲስ ግብር እንዳልሆነ፤ በኢትዮጵያ ከ1937 ዓ.ም ጀምሮ ሥራ ላይ የቆየ እንደሆነ፤ በደርግ ጊዜም በ1968 ዓ.ም አዋጅ ቁጥር 80/1968 ሆኖ ተሻሽሎ እስካዛሬ እየተተገበረ መሆኑን ገልጸዋል።የተመን ማሻሻያ ውሳኔው በግብታዊነት ሳይሆን በጥናትና ወቅታዊ የከተማ ኪራይን መሠረት ያደረገ እንደሆነ አመላክተዋል። ኅብረተሰቡን ማወያየት ያስፈልግ ነበር ተብሎ ለተነሳው ቅሬታ ምላሽ ሲሰጡ እንደተናገሩት፤ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር፤ በገቢዎች ቢሮ በኩል እስከ ወረዳ ባለው መዋቅር ለኅብረተሰቡ ግንዛቤ እየተሰጠ መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡

ከአገልግሎት ጋር በተያያዘ የሰው በብዛት መምጣት የፈጠረው መጨናነቅ እንዳለ ጠቁመው፤ ይህን ለማቅለልም ሰራተኞች በጠዋት በመግባትና ማታም አምሽተው በመውጣት አገልግሎት በመስጠት ላይ እንዳሉ ጠቅሰዋል።የሰው ኃይል በመጨመር አገልግሎቱ እንዲሰጥ ጥረት እየተደረገ መሆኑንም አንስተዋል።የመኖሪያ ቤት ግብሩ በዚህ ዓመት የሚከፈለው 50 በመቶ ብቻ ሲሆን፤ ይህም ግብር ከፋዩ ላይ የሚደርስበትን ጫና ለማቅለል ታስቦ እየተፈጸመ እንዳለ አመላክተዋል።

“የጋራ መኖሪያ ቤቶች እስካሁን ሳይከፍሉ ነው የቆዩት።አዋጁ ላይ እንደተመላከተው በየጊዜው የአከፋፈል ሁኔታን ወቅታዊ ባለማድረግ ወደ ኋላ የቀረ ነው።ኅብረተሰቡ ላይ ሊመጣ የሚችለውንም ጫና ለመቋቋም እስካሁን መዘግየቱ ሊታሰብ ይገባል” ብለዋል፡፡

ዛሬ በተከፈለው ግብር ተጠቃሚው ማኅበረሰቡ ነው በማለት፤ እስከ ዛሬ ባለመከፈላችን አሁንም ሳንከፍል እንቀጥላለን የሚለው እንደማይሰራ፤ ነገር ግን በግል በልዩ ሁኔታ የተቸገረ (ቤቱን ድርጅት ገዝቶ የሰጠው፤ ምንም አይነት ገቢ የሌለው፤ ምንም መክፈል አልችልም የሚል ሰው) ቅሬታ ማቅረብ እንደሚችል ገልጸዋል፡፡

አፈጻጸም ላይ በጥናቱ ያልታየ፤ በጥናት ጊዜ ግንዛቤ ውስጥ ያልገቡ ነገሮች ካሉ ከማኅበረሰቡ ጋር በመወያየትና የባለሙያ ምክር በመውሰድ እየተሻሻለ ይሄዳል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ግንዛቤ ከመፍጠር ጋር ተያይዞ፤ ከከተማዋ ስፋትና ከግብር ከፋይ ቁጥር አንጻር ሲታይ ሁሉም ሰው ጋር በአንድ ጊዜ ተመሳሳይ መረጃ ደርሷል የሚል ድምዳሜ እንደሌላቸው በመግለጽ፤ ጊዜው ያጠረው በበጀት ዓመቱ ውስጥ መሰብሰብ ያለበት ግብር በመሆኑ እንደሆነም ጠቅሰዋል፡፡

አቶ ዘገየ፤ “ግብሩ ሳይከፈል ወደ ኋላ በመጓተቱ፤ ልኬት ተለክቶ የሚመጣው ከመሬት ቢሮ በመሆኑ፣ ለዚህ ዓመት ድካም ሊኖረው ይችላል። ከድካም በጸዳና በአነስተኛ ጊዜ ሰው ሳይቸገር ግዴታውን ተወጥቶ መብቱን ተጠቅሞ ቢሄድ ተገቢ ነው። ይህን እንደ አቅጣጫ ይዘን እየሰራንበት ነው። እየተሻሻለም ነው። አንዳንድ ቅርንጫፎች ላይ ሰው በዝቶ እየተቸገሩ እንደሆነ አይተናል። ስለሆነም የሰው ኃይል ከሌላ በማንቀሳቀስ ድካሙን ለመቀነስ እንሰራለን” ብለዋል። ቀጣይ ድካምና እንግልትን በሚቀንስ መልኩ እንደሚሰራም ተናግረዋል።

# “ሠራዊታችን ስተፈናቀሉ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ቀርቶ፤ ከቀለቡ ቀንሶ የሚያካፍል ሠራዊት መሆኑን የሀገሩ ዜጎች ብቻ ሳይሆኑ በአህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ሰላም ማስከበር በተሰማራባቸው ቦታዎች ሁሉ የዕለት ከዕለት ተግባሩ መሆኑን የደረሰላቸው ሕዝቦች፤ መንግስታት እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ሁሉ የሚያውቁት ስመ ጥር ሕዝባዊ ሰራዊት ነው ብሏል።

ሃገራችን ኢትዮጵያ ለሠራዊቷ ደመወዝና ቀለብ መስጠት ከጀመረች፤ ቀዳሚ ነን ከሚሉ ሀገራት ተርታ የምትሰለፍ ነፃ እና ታሪካዊት ሀገር መሆኗን መግለጫው አመልክቶ፤ሠራዊታችን ዘመናዊ ነው ከሚያስብሉት አንዱ ደግሞ ይኸው ሲወርድ ሲዋረድ የመጣው የሎጅስቲክ ግዥ እና አቅርቦት ጉዳይ መሆኑን ገልጿል።

የሠራዊታችን ቀለብ ለሀገር ውስጥ ነጋዴዎች ዕድሉን በመስጠት በግልፅ ጨረታ ተወዳድረው ስንዴም ሆነ ሌሎች ምግብ ነክ ፍጆታዎች የሚቀርብለት በተሟላ አሰራር እና አመራር የሚመራ ሠራዊት መሆኑንም ሚኒስቴሩ በመግለጫው አስገንዝቧል፡፡

የኢፌዴሪ መከላከያ ሠራዊታችን ማንኛውንም ዓይነት ምግብ በበጀቱ በሕግና በግልፅ ጨረታ ገዝቶ የሚጠቀም እንጂ ተቸግሮ የሕዝብ እርዳታ አካባቢ ሄዶ ርዳታ ላይ የሚሻኮትበት ዓይነት ድህነት የለበትም ያለው መግለጫው፤ ጥቆማ የሰጠ አካል እንኳ ቢኖር እስኪጣራ ሳይጠበቅ፤ እንደ ተቋምና እንደ ሠራዊት ስም የሚያጠፋ የሚዲያ ሽፋን መስጠት የኢትዮጵያን መከላከያ ሠራዊት ክብር ይነካል ብሏል።

ምንም እንኳ አገራችን በሚሊዮን የሚቆጠር እርዳታ ጠባቂ ሕዝብ ቢኖራትም ሠራዊቷን መመገብ የምትችልና በቂ ምግብና በጀት በመመደብ ሠራዊቱ ራሱ በሕግና በተቋም ሎጅስቲክ አማካኝነት የምትመግብ አገር መሆኗን መግለጫው አመልክቶ፤ ሠራዊታችንም ኩሩና የችግረኞችን ስንዴ የማይሻማ ፕሮፌሽናል ሠራዊት ነው። ስለሆነም የርዳታ ስንዴ የሚጠቀም ተቋም ወይም ዩኒት ወይም ወታደር የለንም ነው ያለው በመግለጫው።

ዩኤስኤአይዲ (USAID) በሠጠው መግለጫ መሠረት ምናልባት የመከላከያ አባል የሆነ ወታደር በማይመለከተው ገብቶ ከመዋቅር ውጪ ሕግ የማስከበር ሥራውን ተጠቅሞ ከሌቦች ጋር በመተባበር ርዳታ ተሰርቆ እንዲወጣ በግል የተባበረ ካለ እና ተጣርቶ ከተገኘ የሀገር መከላከያ ሠራዊት አመራር የማያዳግም እርምጃ እንደሚወስድም ነው መግለጫው ያመለከተው፡፡

የመከላከያ ሠራዊታችን ሕዝባዊ ተፈጥሮ፣ አሰራርና ሥርዓት ሳይታወቅና መረጃ እንኳ ቢመጣ፤ አጣርቶ ሳይታወቅ፤ መረጃ የቀረበበት አካል ሳይጠየቅ፤ የሚዲያ ሽፋን መስጠት ትክክል አይደለም ብለን እናምናለን ያለው መግለጫው፤ የሚመለከታቸው የእርዳታ ሰጪ ድርጅቶችና የኢትዮጵያ መንግሥት እንዲያጣሩ እንተባበራለን። ከተጣራ በኋላ ሁሉንም ለሕዝብ ይፋ እናደርጋለን ሲል በመግለጫው አሳውቋል።

## የኢፕድ ስልጠና ማዕከል...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ማዕከል ከዚህ በፊት በተለያዩ የስልጠና ርዕሶች ዙሪያ ከ70 በላይ ለሚሆኑ ለፌዴራል፣ ለክልል ተቋማትና የግል ድርጅቶች በአዲስ አበባና ከአዲስ አበባ ውጪ ተመሳሳይ ስልጠናዎችን በመስጠት ማስመረቁን ጠቅሰዋል።

“አገልጋይ ስብዕና ለውጤት” በሚል መሪ ሃሳብ የተዘጋጀውን ስልጠና ዶክተር ወዳጄነህ መሀረነ ያሰለጠኑ ሲሆን፤አስተያየታቸውን ለኢፕድ የሰጡት ሰልጣኞች በበኩላቸው፤ ስልጠናው ለሥራቸው ትልቅ አቅም እንደሚፈጥርላቸው ተናግረው፤ ሥልጠናው ሳቢና ተግባር ተኮር በመሆኑ በቀጣይ ተጨማሪ ስልጠናዎችን በኢፕድ እንዲሰጣቸው እንደሚፈልጉ ገልጸዋል።

በኢፕድ የስልጠና ማዕከል ባሳለፍነው ሳምንት የልማት ባንክ፣ አዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን፣ አዲስ አበባ ንግድ ቢሮ፣ ምኒልክ ሆስፒታል፣ ቅርስ ጥበቃ ባለስልጣን እና ቡናና ሻይ ባለስልጣንና ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ስልጠናዎች እየወሰዱ እንደሚገኙ ታውቋል።

# “የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

መደረጉን ጠቅሰዋል።

የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ሁሉንም ውጫዊና ውስጣዊ ፈተናዎችን በመቋቋም አዎንታዊ እድገት ማስመዝገብ መቀጠሉንና በተያዘው በጀት ዓመት ሰባት ነጥብ አምስት በመቶ ዕድገት እንደሚጠበቅ ከዘጠኝ ወራት አፈጻጸም ግምገማ መረዳት እንደተቻለ በማንሳት፤ ኢኮኖሚውን ከዳግም ስብራት ወደ ላቀ የእድገት ምህዋርነት በመቀየር በ2023 ጠቅላላ የአገር ውስጥ ምርት 156 ነጥብ 08 ቢሊዮን ዶላር ይደርሳል ተብሎ ይጠበቃልም ብለዋል።

ሚኒስትሩ እንዳሉት፤ ያለፉትን የኢኮኖሚ ሪፎርም ስኬቶች ለማጠናከርና ክፍተቶችን ለማረም አገራዊ መደላድልና አስቻይ ሁኔታን በመፍጠር የተረጋጋ ማክሮ ኢኮኖሚ በአገሪቱ እንዲኖር፣ የአገር በቀል የኢኮኖሚ ሪፎርም ማሻሻያ ማድረግ እንደሚገባ ታምኖበት በቀረበው ረቂቅ ማሻሻያ ላይ በየደረጃው ውይይት እየተደረገበት ይገኛል።

የሁለተኛ አገር በቀል የኢኮኖሚ ሪፎርም ማሻሻያ እንደመነሻ አድርጎ የወሰደው ያለፉትን ዓመታት የኢኮኖሚ ሪፎርም ስኬቶች እንደሆነ የገለጹት ሚኒስትሩ፤ የማክሮ ኢኮኖሚ መዛባቶችን ከማረም ባሻገር የኢኮኖሚ መልሶ ግንባታ በማፋጠንና አገራዊ የእድገት አቅሞችን በማነጽ የአስር ዓመት የልማት እቅዶች ግቦችን ለማሳካት ያለመ እንደሆነ ጠቁመዋል፡፡

ሪፎርሙ የማክሮ ኢኮኖሚ መረጋጋትን ማረጋገጥ፣ የኢንቨስትመንትና የንግድ አካባቢን ማሻሻል፣ ምርታማነትና ተወዳዳሪነትን መጨመርና የመንግስትን የመፈጸም አቅም ማጎልበትን ከግምት ውስጥ ያስገባ እንደሆነም አመላክተዋል።

የሪፎርም አተገባበር በአመራሩ ቁርጠኝነትና በኅብረተሰቡ ሰፊ ንቅናቄ ላይ ሊመሰረት እንደሚገባም አቅጣጫ መቀመጡን ተናግረዋል። በአሁኑ ወቅት በማሻሻያዎቹ ላይ ውይይት እየተደረገ ሲሆን በመጪዎቹ ሶስት ዓመታት የሚተገበር እንደሆነ ጠቅሰዋል፡፡

ሚኒስትሩ እንዳሉት፤ ሁለተኛው ምዕራፍ አገር በቀል የኢኮኖሚ ሪፎርም ለዘላቂ የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር መሠረት እንደሚጥል ታምኖበታል።የግሉን ዘርፍ ይበልጥ እንደሚያጠናክር፣ የዲጂታል አሰራርና ምርታማነትን በማጎልበት ጥራት ያለው ዘላቂ የኢኮኖሚ እድገት እንደሚያረጋግጥ ተስፋ ተጥሎበታል።የዋጋ ንረትን በመቆጣጠር፣ የውጭ ምንዛሬ እጥረትን በመቅረፍ፣ ዘላቂና ፍትሐዊ የኢኮኖሚ እድገት በማረጋገጥ ድህነት በሁሉም መለኪያዎች ትርጉም ባለው መልኩ ይቀንሳል ተብሎ ይታሰባል።ዓለም አቀፍ ንግድን በማስፋፋት የአቅርቦት ሰንሰለትን ቀልጣፋ በማድረግ የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት እድሎችንና ለዜጎች ኑሮ መሻሻል መሠረት እንደሚጥልም ይታመናል።

ኢኮኖሚው የኮረና ወረርሽኝ፣ የአገር ውስጥ ግጭቶች፣ የዩክሬንና ሩሲያ ጦርነት፣ ድርቅ፣ ጎርፍ፣ አንበጣና የልማት አጋሮች የገቡትን ቃል አለመፈጸም የደቀኑትን ጫናዎች ሁሉ ተቋቁሞ ዕድገቱን ማስቀጠሉ ሃየገር በቀል የኢኮኖሚ ሪፎርም ትግበራው ውጤታማነትን የሚያመለክት እንደሆነ አመላክተዋል፡፡

በግብር አወሳሰድ በተወሰዱ ርምጃዎች፣ በውጪና በአገር ውስጥ ብድር ላይ የተወሰዱ ቁጥብነቶችና በድጎማዎች ላይ የተወሰዱ ሪፎርሞች፣ የፊስካል ዲሲፕሊን መሻሻልን በማምጣት ለግብር ገቢ ማደግና የእዳ ክምችት መቀነስ አስተዋጽኦ እንደነበራቸው ገልጸዋል፡፡

የመንግስት ብድር ከአገራዊ ምርት ያለው ድርሻ በከፍተኛ ደረጃ እየቀነሰ መምጣቱን በመጠቆም፤ መንግስት የተከተለው የብዝኃ ኢኮኖሚ አቅጣጫና የአገር በቀል ኢኮኖሚ ሪፎርም የመፍጠንና የመፍጠር አቅሙ እያደገ በመምጣቱ ችግሮችን ተቋቁሞ የእድገት ቀጣይነቱን ማረጋገጥና ስጋቶችን ወደ ዕድል ለመቀየር ችሏል ነው ያሉት።

ውጤቱ ውጫዊ ጫናዎች በሰው ሰራሽና በተፈጥሯዊ ፈተናዎች ሳይበገር በመላው ሕዝብና በየደረጃው ባለው አመራር የተቀናጀ ጥረትና ርብርብ በድምር የተመዘገበ ነው።

በቀጣዮቹ ጊዜያት ኢንቨስትምንትን ማስፋፋትና አገራዊ ቁጠባ ምጣኔን ማሳደግ ጤናማ የሆነ የመንግስት በጀት ጉድለትን በራስ አቅም ለመሸፈን መትጋት፣ የዋጋ ንረትና የኑሮ ውድነትን ማረጋጋት፣ የስራ አጥነት ችግሮችን መቅረፍ፣ የክፍያ ሚዛን ጉድለት ማጥበብና የውጭ ምንዛሬ አቅርቦትን ማሻሻል፣ የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥን ማፋጠን፣ የሃገር ውስጥ ገበያ ሥርዓትን ማዘመን እንደሚገባ በተካሄዱት መድረኮች የጋራ መግባባት ተፈጥሯል ብለዋል።

በዚህም ኢኮኖሚውን ከዳግም ስብራት ወደ ላቀ የእድገት ምሁዋርነት በመቀየር በ2023 ጠቅላላ የአገር ውስጥ ምርት 156 ነጥብ 08 ቢሊየን ዶላር እንደሚጠበቅ ገልጸዋል፡፡

በሌላ በኩል በሀገሪቱ የሕግ የበላይነትን ማስከበር የመንግስት ተቀዳሚ ተግባር ነው ያሉት ሚኒስትሩ፤ ግጭት የዜጎችን ደህንነት አደጋ ላይ የሚጥል በመሆኑ ከሂሳብ ማወራረድ የጥላቻ መንፈስ ለመውጣት አቅጣጫ ተቀምጦ ተግባራዊ እየተደረገ እንዳለ በመጥቀስ፤ መንግስት በወሰደው የሰላምና ህጋዊ እርምጃ በአሁን ወቅት በአማራ ክልል ላይ ከየትኛውም አካባቢ ያልተናነሰ ሰላም መስፈኑንና ከሸኔ ጋር የተጀመረው ሰላም የማስፈን ስራም ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ተናግረዋል፡፡

ሰሞኑን እርዳታ ያለአግባብ ከመጠቀም ጋር ተያይዞ አጋር አካላት በመንግስት ላይ ያቀረቡት ክስ ተቀባይነት የሌለው፣ የፕሮፖጋንዳ ዓላማን የያዘ እንደሆነ ገልጸዋል። ያለበቂ ምርመራ ርዳታን ማቋረጥ ከዓለም አቀፍ መርሆዎች ጋር የሚጻረርና ተረጂ ዜጎች ላይ ጉዳት የሚያደርስ መሆኑንም ጠቅሰዋል።አጥፊዎች ካሉ ግን በህግ እንዲጠየቁ መንግስት ያምናል ነው ያሉት።ለዚህም ጉዳዩን የሚመረምር ኮሚቴ መቋቋሙን ገልጸዋል፡፡

# ነፃ ሃሳብ

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል። በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።



በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

## ልጆቻችንን እየነጠቀን ያለው ቲክቶክ ፤

**(የመጨረሻ ክፍል )**

በክፍል አንድ መጣጥፌ ልጆች እንዴት የተንቀሳቃሽ ስልክ ወይም የሞባይል፣ የጌም፣ የማኅበራዊ ሚዲያና የቴሌቪዥን ምርኮኛ እንደሆኑ፤ ወላጆች ልጆቻቸውን ለማሳደግ እንዴት እየተቸገሩ እንደሆነ፤ እግረመንገድ የሰው ሰራሽ አስተውሎት Artificial Intelligence/AI/ይዞት እየመጣ ያለውን ትንግርት በጥቂቱ ያነሳሳሁ ሲሆን በዛሬው ጹሑፌ ደግሞ ልጆችን ለሱስና ለአዕምሮ ሕመም እየዳረገ ስላለው የማኅበራዊ ሚዲያ በተለይ ስለቲክቶክ አነሳሳለሁ። በአሜሪካው ነጩ ቤተ መንግሥት የሕዝብ ጤና ተጠሪው ወይም ሰርጀን ጄነራል ዶ/ር ቪቬክ ሙርዚ የልጆችንና የወጣቶችን የማኅበራዊ ሚዲያ ሱስ የወቅቱ የሕዝብ የጤና ቀውስ ይሉታል ።

በኮቪድ ወረርሽኝ እንኳ ወጥተው ምክርም ሆነ ማስጠንቀቂያ ሰጥተው የማያውቁት ዶ/ር ቪቬክ በአደባባይ ወጥተው፤ "እንደ ኢንስታግራምና ቲክቶክ ባሉ ማኅበራዊ ሚዲያዎች የተነሳ የልጆቻችን የአዕምሮ ጤና ጉዳይ በብርቱ ያሳስበኛል።" ሲሉ ለመንግሥታቸውም ሆነ ለአሜሪካውያን የማንቂያ ደወሉን አሰምተዋል። ነግ በእኔ ነውና ነገሩ በዚህ አጋጣሚ ልጆቻችንን ከዚህ አደገኛ የቲክቶክ በአጠቃላይ የማኅበራዊ ሚዲያና የጌም ሱስና ወረርሽኝ ለመታደግና ለመከላከል ምን እየተሠራ፣ እየታሰበና እየታቀደ ነው ስል የሚመለከታቸውን አካላት መቀስቀስ እፈልጋለሁ። በይደር ወዳቆየሁት የቲክቶክ ጉዳይ ስመለስ ፦

ፋሪድ ዘካሪያ በ"ዋሽንግተን ፖስት"ጋዜጣ ፣ "Why banning TikTok won't do any good" ወይም "ቲክቶክን ማገድ ለምን ፋይዳ ቢስ ይሆናል" በሚል ርዕስ ባስነበበን የግል አስተያየቱ፤ ሰለ ቲክቶክ ባሰብሁ ቁጥር ይበልጥ ያስፈራኛል የሚለው ፋሪድ ዘካሪያ በአንድ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ለተከታታይ ሁለት እሁዶች በዋሽንግተን ፖስት ጋዜጣም ሆነ በCNN/GPS ጽፎ አያውቅም። ባልተለመደና ተከታዮቹን ባስገረመ ሁኔታ ሰለ ቲክቶክ ግን ጻፈ። ይህ የቻይናው መተግበሪያ አሜሪካንን እንዴት እንዳሳሰባትና እረፍት እንደነሳት ጥሩ ማሳያ ነው። ፋሪድ፣ ባለፈው ሳምንት የቲክቶክን መታገድ ተቃውሜ ሞግቼ ነበር ይለንና። ከተለያዩ ሰዎች ጋር ባደረግሁት ውይይት የተገነዘብሁት ነገር ቢኖር፤ የአሜሪካውያን ዋና ስጋት ቲክቶክ የቻይናዊ ንብረት መሆኑ ሳይሆን ከየትኛውም ማኅበራዊ ሚዲያ በላይ አደገኛ ሱስ አስያዥ መሆኑ ነው። ይህ ደግሞ ሁላችንን እያሳሰብ ያለጉዳይ ስለሆነ ሳንዘገይ አንድ ነገር ማድረግ አለብን።

አሜሪካውያን በ2022 ዓም ከሁሉም የማኅበራዊ ሚዲያ መተግበሪያዎች በአንደኛ ደረጃነት ቲክቶክን አውርደዋል። ሁለት ሦስተኛ የሚሆኑ የአሜሪካ ብላቴናዎች ወይም ታዳጊ ልጆች ቲክቶክን ይጠቀማሉ። ከስድስቱ አንዱ ደግሞ በቲክቶክ ሱስ ተለክፈዋል። ከ2018 እስከ 2021 በተደረገ ጥናት የቲክቶክ ተጠቃሚዎች አኃዝ በ67 በመቶ ሲተኮስ፤ የፌስቡክና የዩቲውብ ተጠቃሚዎች በ10 በመቶ ብቻ ነው ከፍ ማለት የቻለው። ቲክቶክ ምን የተለየ ነገር ቢያደርግ ነው አዳሜን እንዲህ በሱስ የሚያብከነክነው ሲል ፋሪድ ይጠይቅና መልሶ ለነገሩ ማንም አያውቅም ይለናል። በርሊን በሚገኘው ማክስ ፕላንክ ተቋም ተመራማሪ ሊቅ የሆኑት ፊሊፕ ሎሬንዝ የሚያሳዝነው ስለ ቲክቶክም ሆነ ሊያስከትል ስለሚችለው መዘዝ ብዙ የምናውቀው ነገር የለም ይሉናል። ፋሪድ ዘካሪያ ስለቲክቶክ ያለን ግንዛቤ ዝቅተኛ የሆነው ምን አልባት ማኅበራዊ ሚዲያውን ዘግይቶ ስለተቀላቀለና የተጠቃሚ ማጥመጃ ስልቱ ወይም አልጎሪዝም እጅግ የተራቀቀ ስለሆነ ይሆን ሲል ይመረምራል ።

ሌሎች ማኅበራዊ ሚዲያዎች ጓደኛህ የወደደውን ወይም ያጋራውን ተንቀሳቃሽ ምስል፣ ፎቶና መልዕክት

**ቲክቶክን የሰው አዕምሮ ምግብ፣ አደንዛዥ እጽና ወሲብ ሲፈልግ ከሚያመነጨው ከዶፓሚን ወይም dopamine ንጥረ ነገር ጋር ያነጻጽሩታል። ሌላው ከሰዎች ጋር የሚያገናኘን፣ የሚያቀራርበንና ቤተሰብ የሚያደርገን ነገር ስናገኝ ደስተኛ መሆናችን ለእነ ቲክቶክ ሱስ አጋልጦናል የሚሉም አልታጡም**

ሲያደርሱ፤ ቲክቶክ ግን ፍላጎትህንና የምትወደውን ነገር እየገመተ አጫጭር ተንቀሳቃሽ ምስሎችን ወይም ቪዲዎችን በአናት በአናቱ ያዥጎደጉድልሀል። አንዱ ያስወደደው ነገር ይህ ነው። በርካታ የሥነ ልቦና ጠበብት ቲክቶክን የሰው አዕምሮ ምግብ፣ አደንዛዥ እጽና ወሲብ ሲፈልግ ከሚያመነጨው ከዶፓሚን ወይም dopamine ንጥረ ነገር ጋር ያነጻጽሩታል። ሌላው ከሰዎች ጋር የሚያገናኘን፣ የሚያቀራርበንና ቤተሰብ የሚያደርገን ነገር ስናገኝ ደስተኛ መሆናችን ለእነ ቲክቶክ ሱስ አጋልጦናል የሚሉም አልታጡም ።

ማኅበራዊ ሚዲያ ምን ያህል አዕምሮአችንን እየተቆጣጠረው እንደ ሆነ ለመረዳት የሥነ ልቦና ሊቁን ስኪነር ንድፈ ሀሳብ ማንሳት ተገቢ ነው። "operant conditioning" በሚለው በዚህ ግኝቱ ሰዎች ጥሩ ሲሠሩ የምትሸልማቸው ከሆነ ያን ጥሩ ሥራ ደጋግመው ያከናውኑታል። ማኅበራዊ ሚዲያው በእሱ መመዘኛ ጥሩ ተሳታፊ የሆኑ ተከታዮችን ገንዘብን ጨምሮ በላይክ፣ በሼርና በኮሜንት ያበረታታል። የሚዲያው ተጠቃሚ ዩቲውበር ከሆነ ባገኘው ሰብስክሪፕሽን፣ ቪውና ላይክ መጠን ስለሚከፈለው ዩቲውበሩ የተሻለ ክፍያ እንዲያመጣለት ይጥራል ።

አንድ ዩቲውብር ቀድሞ የሚመለከተው ትላንት የጫነው ቪዲዮ ምን ያህል ሰብስክሪፕሽን፣ ቪውና ላይክ እንዳገኘና የተሰጠውን አስተያየት ነው። የቲክቶክ፣ የፌስ ቡክ፣ የቲዊተር፣ የኢንስታግራም፣ የቴሌግራምና የሌሎች ማኅበራዊ ሚዲያ ተጠቃሚዎችን ይሄን ነው በየዕለቱና ሰዓቱ የሚያደርጉት። ብዙ ጊዜያቸውን እያጠፉበት በሄዱ ቁጥር ሱስ እየሆነባቸው ይሄዳል። እንስሳትን ሰርከስን ጨምሮ ለተለያየ ዓላማ የሚያሰለጥኑ ባለሙያዎች የሚጠቀሙት የስኪነርን ስልት ነው። የሚሰለጥነው ውሻ የታዘዘውን ሳያዛንፍ ሲፈጽም አጥንት ሲሰጠው እንደሚበረታታው ሁሉ ማኅበራዊ ሚዲያውም እነ ላይክንና ቪውን እንደ ዶፓሚን በመጠቀም በሱስ ያጠምዳል ።

በማኅበራዊ ሚዲያ ሐያሲነቱ የሚታወቁትና በኒውዮርክ ዩኒቨርሲቲ መምህር የሆኑት ጆናታን ሄይት ከማኅበራዊ ሚዲያ መስፋፋት ጋር ተያይዞ የአዕምሮ ሕሙማን ብላቴናዎች ቁጥር በከፍተኛ ቁጥር እየጨመረ ነው ይሉናል። ከ2012 ዓም ወዲህ ከዓመት ዓመት በአዕምሮ ሕመም የሚሰቃዩ ሕጻናት ቁጥር በአስፈሪ ሁኔታ እየጨመረ ነው። የስሜት መዋዠቅ፣ በጭንቀት፣ በድብርትና ራስን በማጥፋት ሙከራ የተነሳ ሆስፒታል የሚገቡ ልጆች ቁጥር በአሳሳቢ ሁኔታ እያደገ ነው ።

በተለይ ሴት ልጆች ከወንዶች በባሰ በማኅበራዊ ሚዲያ የተነሳ ለተስፋ መቁረጥ፣ ለጭንቀትና ራስን ለማጥፋት በሚዳርግ የአዕምሮ ሕመም እየተሰቃዩ ነው ይሉናል ጆናታን። በ2010ዎቹ ልጆች የእጅ ስልካቸውን በማኅበራዊ ሚዲያ በታጨቁ ዘመናይ ስማርት ስልኮች መተካት የጀመሩበት ክፉ ዘመን ነው። በ2009 ዓ.ም ፌስቡክ "Like"ን ቲዊተር ደግሞ "retweet"ን በማስተዋወቅ በአጥንት እንደሚደለለው ሠልጣኝ ውሻ ሰዎችን በተለይ ልጆችን ማጃጃል ጀመሩ። ፌስቡክ በ2012 ዓም ኢንስታግራምን ሲጠቀልል ልጅ እግር ተጠቃሚዎችን በብዛት የሚያጠምድበት ተጨማሪ መረብ አገኘ።

ጆናታን ሔይት የልጆች ማኅበራዊ ሚዲያን የመጠቀም መብት ከ13 ወደ 16 ከፍ ሊል ይገባል ሲሉ፤ የሕግ መወሰኛ ምክር ቤቱም 16 ዓመት የሚል ረቂቅ ይዞ ብቅ ብሏል። ማኅበራዊ ሚዲያው ሙሉ በሙሉ የሰው ሠራሽ አስተውሎትን መጠቀም ሲጀምር ደግሞ ልጅ አዋቂ ሳይል አዳሜን የሱሱ ምርኮኛ ያደርጋል ሲሉ ጆናታን ፍርሀታቸውን አበክሮ ይገልጻሉ። በሳንዲያጎ ዩኒቨርሲቲ የሥነ ልቦና ፕሮፌሰር የሆኑት ጄን ትዌንጌ ሰሞኑን በተወዳጁ የTIME መጽሔት ላይ እንደገለጹት።

የአሜሪካ የበሽታ መቆጣጠር ማዕከልን ወይም CDCን ጠቅሰው እንዳስታወቁት በ2021 ዓም ከሦስት አንድ የ2ኛ ደረጃ ሴት ተማሪ ራስን ስለማጥፋት ታስባለች። ከ2011 ጋር ሲነጻጸር ደግሞ ራስን የማጥፋት ሀሳቧ በ60 በመቶ አሻቅቧል። በርካታ ልጃገረዶች ደስተኛ እንዳልሆኑና ተስፋ ቢስነት እንደሚሰማቸው የተለያዩ ጥናቶች እያስታወቁ ነው። ከ2012 ዓም ወዲህ የአዕምሮ ሕሙማን ብላቴናዎች ቁጥር እያሻቀበ ነው። ከ2010 እስከ 2019 በድብርት የሚሰቃዩ ልጆች ቁጥር በእጥፍ አድጓል። ከድባቴ ጋር የተያያዙ እንደ ራስን መጉዳት፣ ራስን የማጥፋት ሙከራና ሌሎች የአዕምሮ በሽታዎች ከወንዶች ይልቅ በልጃገረዶች ዘንድ ይከፋሉ።

ከ2009 እስከ 2015 ዓም ራስን በመጉዳት በድንገተኛ አደጋ ሆስፒታል ከገቡት መካከል እድሜያቸው ከ10 እስከ 14 የሆኑ ሴት ልጆች ብዛት በሦስት እጥፍ ተመንድጓል። ይሁንና ይላሉ ፕሮፌሰር ጄን በአሜሪካ የብላቴና አዕምሮ ሕሙማን ቁጥር በአሳሳቢ ሁኔታ እየጨመረ መሆኑን እኔና ባልደረቦቼ ስናስጠነቅቅ ቁጥራቸው ቀላል ያልሆነ የሙያ አቻዎቻችን ይሳለቁብን ነበር ብለው ያስታውሱናል። ዛሬ ስናናንቀውና ስንክደው የኖርነው በሽታ ዋጋ እያስከፈለን ነው። ላለፉት አምስት ዓመታት የአዕምሮ ሕሙማን ልጆች ቁጥር የጤና ቀውስ ሆኗል። ፕሮፌሰር ለመሆኑ የአዕምሮ ሕሙማን ቁጥር ከዓመት ዓመት ለምን እየጨመረ መጣ ብለው ይጠይቃሉ። በ2009 ዓም ይላሉ ፕሮፌሰር አንዲት ብላቴና አብዛኛውን ጊዜዋን የምታሳልፈው ከጓደኞቿ ጋር በመጫወትና የተወሰነ ጊዜዋን ደግሞ ማኅበራዊ ሚዲያ ላይ ነበር።

በ2016 ዓም ነገርዬው የተገላቢጦሽ ሆነ። ማኅበራዊ ሚዲያ መጠቀም ግዴታ መሰለ። 90 በመቶ የሚሆኑ ሴት ልጆች በየቀኑ ማኅበራዊ ሚዲያ መጠቀም ጀመሩ። ከጓደኞቻቸውና ከአብሮ አደጎቻቸው ጋር ወጥቶ መጫወት በከፍተኛ ሁኔታ ቀንሷል። ይህ ደግሞ ለአዕምሮ ጤና አደገኛ ነው። ከጓደኛና ከአብሮ አደግ ጋር በአካል ተገናኝቶ መጫወት ቀረና ማኅበራዊ ሚዲያ ላይ ተጥዶ መዋል የሕይወት ዘይቤ ሆነ ይላሉ ፕሮፌሰር ጄን። ይህ ደግሞ አደጋ ይዞ ይመጣል። ሴት ልጆችን ለወሲብ ብዝበዛ፣ ከአካል ክፍሎች ጋር ለተያያዘ ነውር ፣ ለስድብና ለማሸማቀቅ አጋለጠ።

ይሄን ተከትሎ የአዕምሮ ሕሙማን እንደ እንጉዳይ ፈሉ። በሳንዲያጎ ዩኒቨርሲቲ የስነ ልቦና ፕሮፌሰር የሆኑት ጄን ትዌንጌ፤ ወላጆች ሆይ ልጆቻችሁ 16 ዓመት እስኪሞላቸው ወይም ከዚያ በላይ እስኪሆናቸው ከማኅበራዊ ሚዲያ አርቋቸው። ካልተቻለ ደግሞ በሚመለከቱት ነገር ላይ የቅርብ ክትትልና ቁጥጥር አድርጉ። ማኅበራዊ ሚዲያ ላይ የሚያጠፉትን ጊዜ ወስኑ ሲሉ ይመክራሉ ።

ይህን አሳሳቢ ችግር ለወላጆች ብቻ በመተው መፍትሔ ማምጣት አይቻልም። ማኅበራዊ ሚዲያዎች የልጆችን ማኅበራዊ ሚዲያ የመጠቀሚያ የዕድሜ ጣራ ከፍ ሊያደርጉ ይገባል። መንግሥትም ይህን የሚወስን ሕግ ሊያወጣ ይገባል ይላሉ ፕሮፌሰር። አሁን አሁን ዴሞክራቶችም ሆኑ ሪፐብሊካኖች የችግሩን ስፋትና ጥልቀት የተረዱ ይመስላል። የልጆችን ማኅበራዊ ሚዲያ የመጠቀሚያ ዕድሜ ወደ 16 የሚያሳድግና ማኅበራዊ ሚዲያዎች ላይ ደግሞ ዕድሜን የሚያጣራ አሠራር እንዲያስቀምጥ የሚያስገድድ፤ እንዲሁም ልጆች ማኅበራዊ ሚዲያ ላይ ተጥደው እንዲውሉ የሚያግባቡና የሚያባብሉ ስልቶችን እንዳይጠቀሙ የሚያስገድድ ሕግ ረቅቆ ለሕግ መወሰኛ ምክር ቤት ቀርቧል ይሉናል ፕሮፌሰር።

ባይቴዳንስ የተባለ የቻይና ኩባንያ ንብረት የሆነው ቲክቶክ የተጠቃሚዎቼን የግል መረጃ ለቻይና መንግሥት አልሰጥም እያለ ቢምል ቢገዘትም ሰሚ ያገኘ አይመስልም። ከአፍጋኒስታን እስከ አሜሪካ፣ አውሮፓ ኅብረት፣ ካናዳ፣ አውስትራሊያ፣ ወዘተረፈ ድረስ በመንግሥት ተቋማት የታገደ ሲሆን አሜሪካ ደግሞ ሙሉ በሙሉ ለማገድ ሕግ አርቅቃ ለማጸደቅ ላይ ታች እያለች ነው።

የቲክቶክ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሾው ቼው በበኩላቸው የቻይና መንግሥት የማንንም የግል መረጃ ጠይቆን የማያውቅ ቢሆንም የአሜሪካውያን መረጃችን በአስተማማኙ የኦራክል ክላውድ ቋት ነው የሚከማቸው። ቻይና ቲክቶክን ተጠቅማ ጸረ አሜሪካዊ የሆነ ፕሮፖጋንዳ ልትነዛ ትችላለች ስለሚባለውም ዋና ሥራ አስፈጻሚው ሲመልሱ 60 በመቶ የሚሆኑት የቲክቶክ ባለቤቶች እኮ ቻይናዊ አይደሉም ይላሉ ።

መረጃን ሆነ ብሎ ማዛባትም ሆነ ፕሮፖጋንዳ ቲክቶክ ላይ ቦታ የለውም ሲሉ ቼው ይገልጻሉ። አሜሪካ በተደጋጋሚ ቲክቶክን ለመግዛት ስላቀረበችው ጥያቄ ዋና ሥራ አስፈጻሚው ሲመልሱ ቲክቶክ አይሸጥም አይለወጥም ሲሉ እቅጩን መልሰዋል። ቲክቶክ ከ15 እስከ 60 ሰከንድ የሚወስዱ አጫጭር ቪዲዮዎችን ማጋሪያ የማኅበራዊ ትስስር መድረክ ሲሆን በመላው ዓለም ሁለት ቢሊዮን ጊዜ ወርዷል ብሎኛል በሰው ሠራሽ አስተውሎት ታግዞ መረጃ የሚያፋልገውና እንደ ሰው የሚያወጋው ChatGPT ።

**ሻሎም ! አሜን ።**

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ

## ‹‹ዓለምን ልትቀይር የምትችለው ሴት መሪ ናት ብዬ አምናለሁ››

-የአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ወይዘሮ መሰንበት ሸንቁጤ አበበ



ሰላማዊት ውቤ

ገጽታቸው መልከ መልካም ሲሆን ተክለ ሰውነታቸው በስፖርታዊ እንቅስቃሴ ሸንቅጥቅጥ ያለ ነው። ሳቂታ፤ ቀልጣፋና ግልጽ ናቸው። ሴትነታቸውንና ሴቶችን እንደ አገራቸው በብርቱ ይወዳሉ። ሴቶችን ዝቅ የሚያደርግ፤ የሚያንቋሽሽና ከተሳትፎ የሚያገል ተግባርን አጥብቀው ይቃወማሉ። “ቅድሚያ ለሴቶች” ቢሉም ያልበቃችን ሴት በማብቃት እንጂ ሥልጣንን ተገን አድርጎ እየተሳሳቡ መጠቃቀም ይሉት ነገር አይጥማቸውም። እንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ ሴቶች ከወንዶች ጋር ሲነፃፀሩ ዝቅ ያሉበትን በደል ያካክሳልም፣ ዘላቂ መፍትሔም ያመጣል ብለው አያምኑም። ሁለቱም ፆታዎች እኩል ቢሆኑም ሴቷ በተዛባ አስተሳሰብ ምክንያት ያጣችውን ዕድል በማብቃት ማሟላት የግድ ያስፈልጋል የሚል አቋም አላቸው። ይህን ኃላፊነት አስቀድመው መውሰድ ያለባቸው ወላጆችና የትዳር አጋሮች መሆን እንዳለባቸውም ይመክራሉ። ማብቃቱ ግቡን መትቶ ከስኬት ጫፍ እንዲደርስና የሥርዓተ ፆታ እኩልነት እንዲመጣጠን ሁሉም ማኅበረሰብ እንዲረባረብም ያሳስባሉ።

ያከበራቸውን ሁሉ ቢያከብሩም በመብታቸው ቀልድ አያውቁም። የኔ ነው የሚሉትን ዕድል በፍርሃትም ሆነ በይሉኝታ አሳልፈው ላለመስጠት ይፋለማሉ። ተናግረው የሚደመጡ፤ ተፎካክረው የሚረቱ ሲሆኑ ለሥርዓተ ፆታ እኩልነት ትልቅ ክብር ይሰጣሉ። ለብዙ ዓመታት ውጭ ተምረውና ሠርተው ወደ አገር ቤት የተመለሱት ባለቤታቸው ማዕድ ቤት ገብተው ጭምር ምግብ እስከማብሰልና ልጆች እስከመንከባከብ ድረስ የዘለቀ የቤት ውስጥ ሥራን የሚጋሯቸውም በዚሁ ምክንያት ነው።

ትልልቅ ተቋማትን መርተዋል። ከአንድም ሁለት ባንኮችን ከመሠረቱት መካከል ፊት መሪ ናቸው። የሚፈልጉበት ደረጃ ላይ የሚደርሱ፤ ከተስፋ መቁረጥ ጋር ትውውቅ የሌላቸው፤ ልምዳቸውን ለሌሎች የሚያካፍሉ፤ የጋራ ዕድገትን የሚመኙ ዓይነት ሰው ናቸው። አሁን ላይ የብዙ ስኬቶች ባለቤት በመሆን በተቋሙ የ75 ዓመት ዕድሜ ዘመን የአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ታሪክ የመጀመሪያዋ ሴት ፕሬዚዳንት ለመሆን ያስቻለ ማማ ላይ ለመቆናጠጥ ያበቃቸው ይኸው ጥንካሬያቸው እንደሆነ የሚያውቋቸው ይመሰክሩላቸዋል። ምክር ቤቱን በፕሬዚዳንትነት እየመሩ የሚገኙት በዘንድሮ መስከረም ከፍተኛውን 431 ድምፅ በማግኘት ለሁለተኛ ጊዜ ተመርጠው ሲሆን፣ የዚህ ሁሉ ስኬት ባለቤት የሆኑት ወይዘሮ መሰንበት ሸንቁጤ የዛሬ የሕይወት ገፅታ እንግዳችን አድርገናቸዋል።

### ውልደትና ዕድገት

መሰንበት ሸንቁጤ የተወለዱት አዲስ አበባ ከተማ ልደታ ቤተክርስቲያን አካባቢ ነው። ከማንኛውም ተፅዕኖ ነፃ ሆነው ያደጉትም በከተማዋ ሲሆን የአንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን የተማሩትና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውንም የቀጠሉት በቅድስት ሥላሴ ትምህርት ቤት ነበር። ሆኖም በደርግ ዘመን በትምህርት ቤቱ በቤተክርስቲያኗ አማካኝነት የመጡትንና የሚያስተምሩትን የውጭ መምህራን እንዲለቁና ትምህርት ቤቱም እንዲዘጋ በመደረጉ እስከ 11ኛ ክፍል ነው የተማሩት። የ12ኛ ክፍል ትምህርታቸውን በተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት ተከታትለዋል። ከዚያም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ማኔጅመንትና ፐብሊክ አድሚኒስትሬሽን በመማር የመጀመሪያ (ቢ.ኤ) ዲግሪያቸውን አግኝተዋል።

እንደሚያስታውሱት ከጣሊያኖች ጋር ይሠሩ የነበሩት አባታቸው ዘመናዊነትንና ሥልጣኔን ብቻ ሳይሆን ከወንድማቸው ያልተነጠለ እኩል ዕድል ሰጥተው ነው ያሳደጓቸው። ዕድሉ ነፃነት ከማጎናፀፍ አልፎ በዘመኑ ለወንዶች ብቻ በተከለለው የእግር ኳስና ሌሎች ስፖርቶች እንዲኖኙም አስችሏቸዋል። ስምንት ቁጥር ቲሸርት በመልበስ 16 ቡድኖች በነበሩት በ“እቱ መላ ምቺ” የሴቶች እግር ኳስ ቡድን በመሐል ተጫዋችነትም ስማቸው ጎልቶ እንዲጠራ አድርጓል። አሁን ድረስ በሚጫወቱበት ቴኒስም ኢትዮጵያን ወክለው እስራኤል አገር እስከ መሄድ በመድረስ ስኬት አግኝተውበታል። ወደ ቤተሰባቸውም ሲመጣ አንድ ወንድና አንዲት ሴት ልጅ ሲኖራቸው ሁለቱም ሊሴ ገብረማርያም ትምህርት ቤት ገብተው በከፍተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ተከታትለዋል። ወንዱ በፈረንሳይና ካናዳ ኤሌክትሮኒክስ ኢንጂነር ሲሆን ሴቷ ደግሞ እዚሁ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ የመጀመሪያ ዲግሪዋን ይዛለች። እንግሊዝ ሀገር ሄዳ ለሁለት ዓመት ኢንተርናሽናል ቢዝነስ ተምራ ወደ አገሯ በመመለስ በመሥራት ላይ ትገኛለች።

### የአጋር እገዛ

‹‹በቤተሰብ ምሥረታ ላይ የትዳር አጋር የሆነው ሰው ሴቷ ወደ ላይ እንድትመጣ ማገዝ አለበት›› የሚሉት መሰንበት አጋጣሚ ሆኖ ባለቤታቸው ብዙ ዓመታት በውጭ አገር የኖሩ፤ ሥልጣኔ የገባቸው ናቸው። የወንድ፣ የሴት በሚባል ሥራ ክፍፍል አያምኑም። በመሆኑም የቤት ውስጥ ሥራዎችን በሙሉ በተራ በተራ ነው የሚሠሩት። በአጭሩ ታጥቀው ማዕድ ቤት በመግባት ምግብ ከማብሰል ጀምሮ ገበታ ሠርተው ቤተሰብ ይመግባሉ። ከጡት ማጥባት በስተቀር አስከትቦ፤ ዳይፐር ቀይሮና ተንከባክቦ ልጆች በማሳደጉ ረገድ ባለቤታቸው ከእሳቸው የሚበልጥ አስተዋፅዖ ነው ያላቸው። በቤት ውስጥ እሳቸው በውጭ ያለውን ኃላፊነታቸውን በብቃት እንዳይወጡም ሆነ በዕለት ከዕለት የቤት ውስጥ ግንኙነታቸው ላይ የሚያሳድሩት ምንም ዓይነት ተፅዕኖ የለም። በድምሩ አብላጫውን የቤት ውስጥ ሥራ ከመሸፈን ጀምሮ በማበረታታት ወደ ላይ ከፍ እንዲሉ ትልቅ እገዛ አድርገውላቸዋል። በተለይ ሁለተኛ ዲግሪያቸውን (ኤም.ኤ) ሲሠሩ በሚያመሹና በሚያጠኑበት ጊዜ ያደረጉላቸው ድጋፍ የተለየ አንደነበር ያስታውሳሉ። መሰንበት አሁን ያሉት ወጣት ጥንዶች በአብዛኛው ልክ እንደነሱ የሚተጋገዙ መሆናቸውን በልጆቻቸው ጭምር በማየታቸው መሻሻል መኖሩንም ያወሳሉ።

### ሴቶች ያሉበት

እሳቸው ዕድለኛ ሆነው ትዳራቸው ይሄን ይምሰል እንጂ የብዙዎቹ ኢትዮጵያውያን ሴቶች ትዳር ብሎም ዕድገት ከተፅዕኖ ነፃ እንዳልሆነ ከታዘቡት ተነስተው ያወሳሉ። በፕሬዚዳንት ሳሕለወርቅ ዘውዴ አማካኝነት ከ138 የተለያዩ የአገሪቱ አካባቢዎች የመጡና በመካከለኛ አመራር ላይ ያሉ ሴቶችን ሲያሠለጥኑ ወደ ሰሙትና “እንዴት አድርገው ነው እነዚህ ሴቶች ወደ ላይ የሚወጡት?” ወዳሰኛቸው የሴቶቹ ትውስታ መለስ ብለውም “ብዙዎቹ ወንድ አጋሮቻቸው በቤት ውስጥ ሥራ አያግዟቸውም። ከሥራ ውጪ በሚሆኑበት ጊዜ እቤት ከመዋል ይልቅ አብዝተው በውጭ እየተዝናኑ ማሳለፍ ይመርጣሉ። ለተወሰነ ሰዓት ቤት ቢውሉም እግራቸውን ሶፋ ላይ ሰቅለው ቴሌቪዥን ከማየት ውጭ አንዳች የሚፈይዱት ነገር የለም። በዚህ ጊዜም ከየትኛውም የቤተሰብ አባል የተለየ እንክብካቤ እንዲደረግላቸው ይፈልጋሉ። ካልሲያቸውን እንኳን ማጠብ ነውር የሚመስላቸው ባሎች ሞልተዋል። ሚስቶቻቸው ወጣ ብለው ጎጇቸውን የሚደጉም ሥራ ሲሠሩና ሲያግዟቸው የማይወዱ፤ ቡና እያፈሉ ቤት ውስጥ ቁጭ ብለው እንዲጠብቋቸው የሚፈልጉ በሽ ናቸው ይላሉ። በሥልጣናው ወቅት ብዙ ጠንካራ ሴቶች በብርታታቸው ይሄን ጥሰው እየወጡ መሆናቸውን ቢረዱም አሁን ካሉበት ወደ ላይ ለመውጣት ያለውን ልምዳቸውን ሲነግሯቸው ከውጭም እንቅፋቶች አሉባቸው። የበቃች ሴት እያለች ለወንድ ዕድሉ የሚሰጥበት አድሏዊ ሁኔታ አለ። እላይ ያሉትን ሴቶች ለመተካት ታች ያሉት ሴቶች በቅተው መምጣት እንዳለባቸው መረዳት የለም። “በመሆኑም ያለፍነው የሚመስለን ችግር አሁንም አለ›› የሚሉት መሰንበት እነዚህን ተግዳሮቶች ለመፍታት የሕግ ማዕቀፉ እንደገና መጠናት ያለበት ስለመሆኑም ይጠቁማሉ።

### የሥራ አሀዱ

በወንዶች ተፎካካሪዎቻቸው ዘንድ በጥንካሬያቸው እንደ እንግሊዟ ጠቅላይ ሚኒስትር ማርጋሪት ታቸር ሁሉ ‹‹ጠንካራዋ እመቤት›› የሚል አጎላማሽ የተሰጣቸው መሰንበት ሥራ ‹ሀ› ብለው የጀመሩት በልማት ባንክ ነበር። በኢትዮጵያ ልማት ባንክ በጀማሪ ባለሙያነት ሲሠሩ ከቆዩ በኋላ በመሐል እንግሊዝ አገር የትምህርት ዕድል አግኝተው በቢዝነስ አድሚኒስትሬሽን የሁለተኛ ዲግሪያቸውን ይዘዋል። ከእንግሊዝ ከተመለሱ በኋላ እዛው ልማት ባንክ ተመልሰው በመሥራት እስከ ምክትል ፕሬዚዳንትነት ደርሰዋል። የዓባይ ባንክን ለመመሥረት ብዙ ጥያቄዎች የመጡትም እዚሁ ሆነው ነበር። ምንም እንኳን በባንኩ ያለባቸው ኃላፊነት ከፍተኛ ቢሆንም፣ በተለይ ሴቶችን ወደ ኃላፊነት ደረጃ ለማምጣት ከጠዋቱ ባደረባቸው ቁርጠኝነት ለጥያቄው ምላሽ ለመስጠት አላቅማሙም። ‹‹ሴቶችን ለማብቃት ያስችለኛል ብዬ ጥያቄውን ተቀበልኩት›› ሲሉ ያስታውሱታል። ዓባይ ባንክን ለሰባት ዓመታት ያህል ከማቋቋም ጀምሮ ሲመሩም ቆይተዋል። እዚህ ለሴቶች ባላቸው ጥብቅናና ወገናዊነት የተነሳ ከተገዳዳሪ አስተሳሰቦችና ሁኔታዎች ጋር ለመዝለቅ ብዙ ሞክረዋል። ‹‹ቢሆንም ሴቶች በብቃታቸው ዕድሉን በሚያገኙበት ጊዜ ቦታውን የሚፈልጉ ወንዶች አቅሙ እንዳላቸው እያዩ በብቃታቸው እንዳላገኙት ‹‹እሷማ እኮ ቦታውን በ--- ዓይነት ሁኔታ ነው ያገኘችው›› ለሚለው ሐሜት ቦታ እንደማይሰጡ ይናገራሉ። ተግባሩን ሲገልፁትም “ቅናት፤ ምቀኝነት፤ ሴቶችን የሚያገል ብልጣብልጥነትና ራስ ወዳድነት የተሞላ ስም ማጥፋት ዘመቻ” ይሉታል። ሁኔታው ዕድል የሚነፍግ በመሆኑ የበለጠ ለመታገል እልህ ውስጥ እንደሚያስገባቸውም ይናገራሉ። ያዘኑበት ጊዜ ቢኖር ዕድሉን ባገኙባቸው አጋጣሚዎች በእንዲህ ዓይነቱ አስተሳሰብ የመብጠልጠል ዕድል የገጠማቸው በመሆኑ መሆኑንም በቅሬታ ያስታውሳሉ። በተለይ የሴቷ ቁመናና ገጽታ የተሻለ ከሆነ በእንዲህ ዓይነቱ ሐሜት መፈረጇ የተለመደ መሆኑን በቁጭት ያነሳሉ። እንዲህ ዓይነቶቹን ታግለዋል፤ ስኬታቸውን አስተካክለው፣ አስተሳሰቡን ቀይረው የሚፈለገው ደረጃ ላይ በመድረስ ውጤት ሲያሳዩ ደግሞ “እሷማ ወንድ ናት፤ ጠንካራዋ እመቤት” (ዘ አይረን ሌዲ) የተባሉበትን መቼም ቢሆን የማይረሱትና ያስደሰታቸው መሆኑን ያወሳሉ።

### የራስ መክሊት

በራስ የመተማመን ሙሉ አቅም ያላቸው ወይዘሮ መሰንበት ውስጣቸውን ሲያዳምጡ ቆይተው የራሳቸው የሆነውን የ‹‹ኒው ዳይሜንሽን›› ማኔጅመንት አማካሪ ድርጅት /ኮንሰልታንሲ/ መሠረቱ። እዚህም የባንክ ብድር የአዋጭነት (ፊሲቢሊቲ) ጥናቶችን ይሠሩ ጀመር። ድርጅቶች ችግር ሲያጋጥማቸው መፈተሽ፤ ከውጭ ድርጅቶች ጋር ለሚሠሩ ድርጅቶች ጥናት መሥራት፤ እንዲሁም ሌሎች የአስተዳደር ሥራዎችን ለመሥራት ሲፈልጉ ማማከር ይሠሯቸው ከነበሩት መካከል ይጠቀሳሉ። በዚህ ሁኔታም ስድስት ዓመታት ሲሠሩ መቆየታቸውንም ያወሳሉ። ‹‹ድርጅቴ በንግድ ምክር ቤት ተመዝግቦ በመሥራቱ ምክንያት አባል ልሆን ችያለሁ›› ሲሉም ወደ ኋላ መለስ ብለው ወደ ኃላፊነት የመጡበትን ዳራ ያስታውሱታል።

### ስኬትና ኃላፊነት

ኃላፊነትን በብቃት መወጣት በአስተዳደጋቸው መሠረቱን የጣለ የፕሬዚዳንቷ ዕጣ ፈንታ ነው። በንግድ ምክር ቤቱ በአባልነት ሲሠሩ ከቆዩ በኋላ የንግዱ ኅብረተሰብ በከፍተኛ ድምፅ መርጧቸው አምነውበትና ፈቃደኛ ሆነው በኃላፊነት መሰየማቸውን ያወሳሉ። በአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ምክር ቤት ላይ በፕሬዚዳንትነት የመመረጥ ዕድል አግኝተው አራት ዓመት አገልግለዋል። በኮቪድ ምክንያት አስቸኳይ አዋጅ በመውጣቱና በአዋጁ ስብሰባ ማድረግ ባለመቻሉ የአገልግሎት ጊዜያቸውን ቢያጠናቅቁም ሲመሩ

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ

## ‹‹ዓለምን ልትቀይር...

ከገጽ 6 የዞረ

የቆዩበት ሁኔታም ነበር። ምንም እንኳን ለሁለት ዓመት የነበረው የምርጫ ዘመናቸው በኮቪድ የተነሳ ቢራዘምም፣ ስብሰባ ሲፈቀድ እንደገና በተደረገው ምርጫ በድጋሚ በከፍተኛ ድምፅ ተመርጠው ምክር ቤቱን በፕሬዚዳንትነት በማገልገል ላይ ይገኛሉ። በተለይ በመጀመሪያው የምርጫ ዘመናቸው አጋጣሚ የራሳቸውን ድርጅትና ዓባይ ባንክን የምክር ቤቱ አባል አድርገዋል።

ይህ ብዙዎች የለፉበትና የታገሉለት ምክር ቤት 75 ዓመቱን ሲያስቆጥርም ታሪካዊ ማስታወሻው በመጽሐፍ መልክ እንዲወጣ ማድረግ ያስቻሉት እሳቸው ናቸው። በ75 ዓመታት ዕድሜው አልፎ አልፎ ከሚታዩት ሴት አባላቱ በስተቀር አንዲትም ሴት በኃላፊነትም ሆነ በፕሬዚዳንትነት አለመምጣቷን በቁጭት ያስታውሳሉ። ምክር ቤቱ በተቻለ መጠን ውጤታማ እንዲሆን መንግሥትን የማሳወቅና የማሳመን ሥራዎች በመሥራት ላይ እንዳሉም አውግተውናል።

መሰንበት በእነዚህ ጊዜያት ሁሉ አሁን ወደ ደረሱበት ደረጃ ለመድረስ ያደረጉትን ጥረት አስመልክቶ በምሳሌነት ከነገሩን ውስጥ የአማራ ባንክንም በኩባንያቸው በኩል ፕሮጀክቱን በመቅረጽና መምራት፤ ወደ ሥራ ከማስገባት ጀምሮ እስከ ቦርድ አባልነት ድረስ እስከ አሁኑ ሰዓት ድረስ እያገለገሉ ይገኛሉ። እንደዚሁም "የኢትዮጵያ ስፔስ ሶሳይቲ"ን የዓባይ ባንክ አባል በማድረግ በሰብሳቢነት እየመሩ ይገኛሉ። በደብረ ብርሃን ዩኒቨርሲቲ የቦርድ አባል፣ የክርስቲያን ኮንሶርቲየም የካቶሊክ ቤተክርስቲያን አባል በሆኑበት ድርጅትም በማገልገል ላይ ናቸው።

### አስተዋፅዖ

ወይዘሮ መሰንበት በንጉሡ ዘመን በራሳቸው በንጉሠ ነገሥቱ ወደ ተመሠረተ አንጋፋ ንግድ ምክር ቤት እሳቸው በመሪነት ከመጡበት ሰዓት ወዲህ የተመዘገቡ ተሞክሮዎችንም ከታሪኩ ጋር እያዋዙ አጋርተውናል።

የአዲስ አበባ የንግድ ምክር ቤት ዘርፍ ማኅበራት ለመዲናችን የመጀመሪያው ነው። በወቅቱ ነጋዴው ራሱን በራሱ ለሀገርም እያደራጀ እንዲራመድ ቀና የሆነ አዎንታዊ ዓላማ የነበረው አወቃቀር ነበር። በደርግ፤ ሥርዓቱ የግል ንግድንም ሆነ የግል ሀብት ማፍራትን የማይደግፍ በመሆኑ ተቸግሯል። ፈተናው የበዛ ስለነበር አመቺ መንቀሳቀሻ መድረክም አልነበረውም። በመሆኑም መሪዎቹም ብዙ ችግር አሳልፈው ለመምጣት ተገድደዋል። ወደ ኢሕአዴግ ዘመን ሲመጣም የኮሚኒዝም ግርሻት ስላጠላበት ማኅበሩም ወደ መንግሥት ያዘነበለ ስለነበረ ብዙም ውጤታማ ሥራ አልተሠራም። እንዲሁም ነጋዴው ጠንካራ ቢሆንም በአዋጅ የተቋቋመበትን ዓላማ ሊያሟላ አልቻለም። ለሀገርም ሊያደርግ የሚችለውን አስተዋፅዖ ጎድቶታል። አሁን ለሀገር አስተዋፅዖ ሊያደርግ የሚችልበት ዕድሉ ተሰጥቷል። በአጠቃላይ የአገሪቱ ዕቅድ ውስጥ የግሉ ዘርፍ ካልተካተተና አብሮ ካልሄደ ዕድገት አስቸጋሪ መሆኑ ታምኖበታል በማለት አጫውተውናል። ‹‹የግል ዘርፉ መካተቱን እኛም ጭምር በተሳተፍንበት መግባባት ተደርሷል››ም ነው የሚሉት።

እንደሳቸው ማብራሪያ ባለፉት ጊዜያት ሊያሠሩ የሚችሉ ሁኔታዎች ሁሉ የተዘለሉበት መሆኑን በመረዳት፣ ከግሉ ዘርፍ ጋር መንግሥት የሚያደርገው ግንኙነት የመካረርና የሚፃረር ሳይሆን ስምም ሆኖ መቀጠል ያለበት ሆኖም ተገኝቷል። በተለይ ምክር ቤቱ አሁን የያዘው አቋም የመንግሥትን አቅጣጫ የሚያግዝ፣ መመሪያና ፖሊሲዎችን በሀገራዊ ዓውድ የሚያይ፤ የነጋዴውን ጥቅም የሚያስጠብቅ ሆኗል። ነጋዴው መብትና ግዴታውን የሚያውቅበት፣ በትብብርና በመግባባት የሚሠራም ለመሆን በቅቷል። ‹‹ስምንት አዕማዳትን (ፒላርስ) በመንተራስ በመሬት ፖሊሲውም፣ በውጭ ምንዛሪው፣ በግብር ዙሪያና በሌሎችም እጅግ ሰፊ የሆነ ጥናት በማድረግ፤ ነጋዴውን አማክረን፣ ችግሮቹን ለይተን ለመንግሥት ምክረ ሃሳብ ሰጥተናል፤ ሊያሠሩ የማይችሉትን የሕግና የፖለቲካ ነጥቦች ነቅሰን አውጥተን በጠቅላይ ሚኒስትሩ በኩል ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች ሁሉ እንዲያውቁት ያደረግነው ከነበረው በተለየ ሁኔታ መንግሥትንም ለማግባባትና ለማሳመን ያደረግነው ጥረት አንዱና ተጠቃሽ ነው፤›› ይላሉ። ሌላው ያነሱት ነጥብ የምክር ቤቱ የውስጥ አሠራሮችና ሁኔታዎች እንዲሻሻሉ መደረጉ ነው።

የምክር ቤቱን አሠራርና አስተሳሰብ፤ አቅም የግንባታና ለውጥ በማምጣት የተስተካከለ መሆኑን ማሳያ ያቀርባሉ። ‹‹በዚህ ከ60 በመቶ በላይ አባሎቻችን ሴቶች የሆኑበት ጊዜ ላይ ደርሰናል። ጠንካራ የሆኑ ሴቶች ወደ ፊት እየመጡ ነው፤ የኔም ሕልም ይኼው ነበር›› ይላሉ። ምንም እንኳን በአገር አቀፍም ይሁን በዓለም ደረጃ የኮቪድና የሰላሙ



ችግር ተፅዕኖ ቢያሳድርም የወደፊት እርምጃቸውን ከመግፋት አላገዳቸው። ከመንግሥት ጋር በመግባባት ሊሠሩ የሚችሉበትን ዕድልም አልዘለሉም። በንግድ ምክር ቤቱ ውስጥ የተደረገውን ሴቶችን ከማብቃትና ወደ አመራር ከማምጣት በተመሳሳይ በዓባይ ባንክም ይሁን በአማራ ባንክ የተደረጉ እንቅስቃሴዎችን አስመልክተውም ‹‹ያኔ ይኼኑኝ ብዬ ነበር ሴቶች ላይ አትኩሬ እሠራ የነበረው፣ ሴቶች አመራር ላይ እንዲቀመጡ በመደረጉ ነው ዛሬ ዓባይ ባንክ ጥሩ እንቅስቃሴና ደረጃ ላይ ያለው ማለት እችላለሁ›› ይላሉ። እንደሳቸው ፖሊሲው ቅጥርና ዕድገት ላይ የሴቶችን አቅምን በመንተራስ ቅድሚያን መስጠት (አፈርማቲቭ አክሽን) የተቃኘም ነበር። አማራ ባንክ ላይም ቢሆን የዓባይ ባንክንና የልማት ባንክን ልምዶች በመውሰድ ነው የሠሩት፣ ከፕሮጀክቱ ደረጃ ጀምሮ ባንኩ እስኪመሠረት ድረስ በሴቶች አጥጋቢ ተሳትፎ ተደርጓል። ባንኩ ከተቋቋመ በኋላ ግን በቦርድ ኃላፊነት ነው የነበሩት። ሆኖም በተቻለ መጠን ሴቶች እንዲሳተፉ፣ እንዲመጡ ጥረዋል። ከ12 የቦርድ አባላት ሴት እሳቸው ብቻ በመሆናቸውና ሥራውን የሚመሩት ሌሎች ስለሆኑ፣ መሪውም ወንድ በመሆኑ ትግሉ ቀላል አልነበረም። ግን ሴቶች በችሎታም ሆነ በብቃት ወደ ፊት እንዲመጡና ለምርጫና ለውሳኔ እንዲበቁ በተቻለ መጠን ድምፃቸውን ከማሰማት አልተቆጠቡም። ደስ የሚለው አቅም ያላት ሴት ከመጣች የቦርድ አባላቱም የሚደግፏቸው መሆኑ ነው። ይሄን ተጠቅመው በቦርድ ደረጃ ሴቶች እንዲያልፉ አድርገዋል።

### ሴትነትና ቁርጠኝነት

መሰንበት ዛሬ በ75 ዓመት ታሪክ ለአንድ ጊዜ እንኳን ሴት ልትመራበት ያልቻለችበትን ከፍተኛ የኃላፊነት ማማ ላይ መቀመጥ የቻሉት ጎታች አስተሳሰብና አመለካከትን በመታገላቸው ነው። ዓባይና አማራ ባንክን ከመመሥረት ባለፈ በርካታ ሥራዎችን የሠሩትም "እችላለሁ!!!" በማለታቸው ነው። እሳቸው ጋ ዕድሉ ሲገኝ እንደ ብዙዎቹ ሴቶች መግደርደር አይሠራም። ዕድሉን ሥራውን ችለውት ሳለ በፍራቻና በይሉኝታ፤ አልያም በቸልታ ለወንዶች አሳልፎ መስጠትም በፍፁም አይታሰብም። ብቃቱ እንዳላቸው ስለሚያምኑ ፈጥነው ነው ኃላፊነትን የሚወስዱት። እችለዋለሁ፤ እሠራዋለሁ፤ ብለውም በአደባባይ ቃላቸውን እየሰጡ ነው በደስታ ኃላፊነትን የሚቀበሉት። ‹‹እኔ የማምነው ዓለምን ልትቀይር የምትችለው ሴት መሪ ናት ብዬ ነው›› የሚሉት መሰንበት ሴቶች ዕድሉን ካገኙ ከወንዶች የተሻለ ሥራ ሊሠሩ እንደሚችሉ ወገባቸውን ይዘው ይሞግታሉ። ሆኖም ማኅበረሰቡ ሴቶችን ዝቅ አድርጎ በመመልከቱ በአብዛኞቹ ችሎታቸውን የሚያስመሰክሩበት ዕድል ባለማግኘታቸው አብዝተው ይቆጫሉ። ‹‹ዕድሉ በተገኘበት ቦታና አጋጣሚ ሁሉ ብቃቱ ያላትና መስፈርቱን የምታሟላ ሴት የምትገኝ ከሆነ ከብዙ አቅጣጫ ኃላፊነቷን በተሻለ ሁኔታ መወጣት በመቻሏ ከወንዱ ይልቅ እሷ ቅድሚያ ማግኘት እንዳለባትም አበክረው ያስገነዝባሉ። ሁሉም ዕድሉን የሚያገኙ ሴቶች ብቃቱ አለኝ፤ እችለዋለሁ፤ እወጣዋለሁ ብለው ወደ ኃላፊነት መምጣት እንዳለባቸው ይመክራሉ። ወደ ኃላፊነት ሲመጣ ያለውን ሁኔታ አስመልክተውም ‹‹እርግጥ ነው ኃላፊነት ያስቸግራል፣ ሴት ሲኮን ደግሞ በብዙ ምክንያቶች የበለጠ ሊከብድ ይችላል›› ይላሉ።

ኅብረተሰብን ከመፍጠርና ልጅን መሥመር ከማስገባት ጀምሮ ያለው ማኅበራዊም ይሁን ተፈጥሯዊው ግዴታ የሴቶች ነው። በሥራ ቦታም ውስጥ ተመሳሳዩን ይዘው ይመጣሉ፤ ሴትን አሳንሶና አግልሎ ማየት፤ ወደ ኃላፊነቱም እንዳትመጣ ከመንገዷ ላይ የሚቆመው ትልቁ ችግር ነው። ‹‹ቤተሰብ እንደ አንድ ተቋም መታየት ያለበት ነበር›› ይላሉ፤ በሀገራችንም ይሁን በዓለም ላይ አሁን እንደሚታየው ትልቅ የመሪነት ችግር፣ የሴት መሪ በጥቅሉ ሲታይ እጅግ አነስተኛ ነው፤ እርግጥ በኛ ሀገር መሻሻሎች አሉ፤ ቢሆንም የሚቀሩ ብዙ ናቸውና ትግሉ እጅግ ከባድ ይሆናል ሲሉ ይናገራሉ።

ሌሎች ችግሮች እንደተጠበቁ ሆነው ወደ ኃላፊነት ለመምጣት ከሴቷ የሚጠበቀው ብዙ ነው። በመጀመሪያ ደረጃ አቅምን ማሳደግ፣ ብቁ ሆኖ መገኘት፣ ተስፋ አለመቁረጥ፣ የመሪነት ሕግና ደንብን ተከትሎ መዝለቅና ቁርጠኛነት እጅግ ያስፈልጋል። ምክንያቱም ዞሮ ዞሮ ሴቶች ውጤት ለማምጣት ከሆነ ያ ‹‹አይችሉም›› የሚለውን አጥርንና ግንብን ለማፍረስ እነዚህን መርሆዎች መከተላቸው ግድ ነው። ‹‹እርግጥ የሴት መሪነትን የማይቀበሉ ሰዎች መኖራቸው መዘንጋት የለበትም›› ይላሉ ደጋግመው። ‹‹ወንዶች ምን ዓይነት ተፈጥሮ እንዳላቸው አውቃለሁ›› የሚሉት መሰንበት እንደሚያክሉት ጨርሶ በራስ ጥረትና ችሎታ ሴቶች የኃላፊነት ደረጃ ሊደርሱ አይችሉም ብለው የዘጉ ሰዎችም አሉ። እንዳውም የስኬታቸውን ምክንያት አቃቂር እየፈለጉ የሚያጣጥሉባቸው ተግዳሮቶቹ እጅግ ብዙ ናቸው፤ ሴትም ሆነ ወንድ ለኃላፊነት ብቁ ሆኖ መገኘት እንዳለበት ያምናሉ። አክለውም ሴትም ብትሆን በትምህርት፣ በሙያና በአቅም ብቁ ሆና መገኘት አለባት። ይህ ከሆነ ወደ ላይ ከፍ ማለት ይገባታል›› ይላሉ። እንደሳቸው ልምድን መሠረት ያደረገ አስተያየት ከዚህ አኳያ ሲነጻጸር ሴቷ ከወንዱ መወዳደር ያለባት በውጤት ነው። የነገሩን እምብርት እንይ ካልን ቤተሰብን እንደተቋም የተሸከመች፣ ያበቃችና የኖረች ሴት ከግል ፍላጎቷ ይልቅ ለጋራው ቤተሰቧ ቅድሚያ ለመስጠት ትጥራለች። ይህ የተወረሰ ባሕሪዋ ሲሆን በኃላፊነትዋ ጊዜ፤ በዕውቀት፣ በችሎታና በአቅም አጎልብታ ስታመጣው የሴቷ አቅም ይበልጣል። መሰንበት ያቀረቡትን አመክንዮ በሰፊው በማብራራትም ‹‹ልምዱ ያሳየኝ በአገር አቀፍ ብቻ ሳይሆን በዓለም አቀፍ ደረጃም ቢሆን ይኼንኑ ነው›› ሲሉ ያጠናክሩታል።

### ፖለቲካ

ፖለቲካ ሰዎችን እየተናገሩ ማሳመን ማለት ነው። ይሄ ወሬ ደግሞ ሄዶ ሄዶ ወደ ኢኮኖሚው ነው የሚመጣው። ፖለቲካ ራሱ ኢኮኖሚ ነው የምለው ለዚህ ነው ይላሉ። የእኔ አመለካከትና እምነት የሰው ልጅ የተሻለ ሕይወት ኖሮት እንዲኖር ነው። ከዚህ አንፃር እኔ ብመራ ደስ ይለኛል። ለኔ ምንም አይከፈለኝ ባለኝ አቅምና ብቃት የተሻሉ ሁኔታዎች እንዲመጡ የተሻሉ ሥራዎችን እሠራለሁ። ሥራዎቹን ለመሥራት ሥልጣን ማግኘት ወሳኝ ነው። ይሄን ለማድረግ ብቃት ይጠይቃል። የተሻለ ሀሳብ ለመሥጠትም ተቀባይነትን ማግኘት ያስፈልጋል። ምክር ቤት ላይ ሆኜ ስመራ ሌሎችን አሳምኜ መሄድ ይጠበቅብኛል። ብዙዎች መሪ መሆንን የግል ጥቅም ማግኛ አድርገው ይወስዱታል። ይሄ ዓይነት ሁኔታ በጥቅሉ በዓለም ላይ ያለ ነው። በፖለቲካው ባሕል ሰዎች ከወጡ በኋላ የተሻለ ሠርተው የሚመሰገኑበት ቢሆን ይመረጣል። የሰዎች ጭንቅላት የተለያየ ነው። ከአንዱ አንዱ የተሻለ ነገር ሊያመጣ ይችላል። በኔ ውስጥ ያለው የተሻለ ውጤት ሊያመጣ ይችላል ብዬ ስል በመሪነት ደረጃ ብቀመጥ ደስ ይለኛል። ሆኖም እኔ ይህን መመኘቴ የሥልጣን ፍላጎት አይደለም። እኔ እንዲህ ዓይነት አስተሳሰብ አለኝ፤ ለሌላ ሰው እንዲጠቅም እንዴት አድርጌ ማውራት እችላለሁ ብሎ ራስን መጠየቅ ያስፈልጋል። እኔ የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት አባል ነኝ። በአዲስ አበባ ከተማ ያሉ ችግሮች እንዲፈቱ ያለኝን ሀሳብ አንፀባርቃለሁ።

### የኑሮ ውድነት

የኑሮ ውድነት አጠቃላይ በዓለም አቀፍ ደረጃ ያለ ጉዳይ ነው ይሉታል መሰንበት። እንደሳቸው ትልቁ መንስኤ ኮቪድ የሰውን እንቅስቃሴ ገድቦ መቆየቱ ነው። በዚህ የተነሳ ከፋብሪካም ሆነ ከሌላ የሚጠበቀው ምርት መገኘት አልቻለም። የፋብሪካዎች ዘረፋና ውድመት ሲደመርበት በኢኮኖሚው ላይ ትልቅ ተፅዕኖ አሳደረ። እንደ አገር ከኮቪድ በተጨማሪ በሰላም እጦት ምክንያት ትራንስፖርት በመስተጓጎሉ፤ ያለው ምርት በተፈለገው ጊዜ ለሚፈለገው አካባቢ ባለመቅረቡ ሰዎች እንደ ልብ ተንቀሳቅሰው መሥራትና ገበያ ልውውጥ ማድረግ ባለመቻላቸው ምክንያት ነው ዋጋ ንረት የተፈጠረው። ይሄን ለመቀልበስ መንግሥታት፤ ዝቅተኛውን የኅብረተሰብ ክፍል እያገዙ የሚሄዱበት፤ የሌለው ያለውን እየረዳ የተጓዘበት ዕድል ተፈጥሯል። ሕዝቡ ይሄን ሰብዓዊ ተግባር የቆየ ኢትዮጵያዊ ባሕል አድርጎ እንዲቀጥል፤ በተለይም በኮቪድ ጊዜ እንደገና እንዲጀምረው፤ እንዲህም ሆኖ የኑሮ ውድነት መሠረታዊ የሆነ ለውጥ ይፈልጋል። በኤክስፖርት ለተሠማሩት ነጋዴዎችም በተሻለ ሁኔታ ማበረታታትን ይጠይቃል። በዓለም አቀፍ ደረጃ የኑሮ ውድነቱን ለማሸነፍ እንዲሠሩ፤ ቀጣይነት ያለው ሰላም እንዲሰፍን ማድረግም ይጠበቃል። ይህን ማስተካከል ያለበት ሰው ራሱ ነው።

### መልዕክት

መሰንበት እንደሚሉት ጠንካራ ሴት በምንም ነገር አትሸነፍም። ገንዘብ መሰብሰብ ብቻ ሳይሆን በምቾት መኖር የሚያስችሏትን ሁሉ ትፈጥራለች። ለሌሎች ደግሞ የተሻለ ሁኔታ እንዲኖራቸው ታደርጋለች። ሴቶች ላይ ያሉ ሁኔታዎችን በልጃቸውም በራሳቸውም ያያሉ። በተለይ ሴት ነጋዴ ስትሆን ብዙ እንቅፋቶች ይገጥሟታል። ድሮ የሚታየው ሴቷ ገንዘቡን የማስተዳደር አቅም ያላት ባለመሆኑ ሊባክንባትና ሊከስርባት መቻሉ ነበር። በባንክ አካባቢ በተለይ ሴቷ ገንዘቡን በደንብ ላትይዝ ትችላለች የሚል የተሳሳተ አስተሳሰብ ነበር። ይሄ አሁንም አልተቀረፈም። ገንዘቡን ለማግኘትም በሴትነቷ ብዙ የሚደርሱባት ችግሮች ነበሩ፤ አሁንም አሉ። ሴትነቷን እንድትሸጥ ወይም መጠቀሚያ እንድታደርግ የሚያደርጉ መሰናክሎች ሁሉ ሊገጥሟት ይችላሉ። እነዚህን ሁሉ ተቋቁማ "ለነገ ሕይወቴ" ብላ ማሰብና ለራሷ ብቻ ሳይሆን ወደ ፊት አርቆ ለብዙሃኑ ማሰብ አለባት።

ፕሬዚዳንት መሰንበት እኔ ካደኩ ብዙኃኑ የሚያድጉበት ሁኔታ አለ ብለው ያስባሉ። ‹‹እኔ ሁልጊዜም ወደ ፊት ያለኝ ስሜት ይሄ ነው›› ሲሉም አቋማቸውን ያረጋግጣሉ። ሌሎች ሴቶችም የሳቸውን ተሞክሮ እንዲቀስሙ መልዕክታቸውን ያስተላልፋሉ። ብዙ ወንዶች ወንድ ብቻ ሊያደርገው የሚችላቸው የሚመስላቸውን ሥራዎች አሉ። ብዙዎች ባንኮች በወንዶች ነው የተመሠረቱት። ግን እሳቸው ወንድ ያደረገውን ማድረግ ችለዋል። ከእሳቸው ቀድማ ሌላ የግል ባንክ የመሠረተች ሴትም እንዲሁ ማድረግ የቻለችው ነው። ‹‹ለሴቶች የምመክረው በምንም ተዓምር ተስፋ እንዳይቆርጡ ነው። ለምንም ዓይነት ተግባር መቻልን ለማሳየት ምስክር ይሆን ዘንድ አቅምን ማሳደግ ሁል ጊዜ በትምህርት፤ ትምህርት ብቻውን በቂ ስላልሆነ በክሂሎት . . . በተለያዩ ቦታዎች ኃላፊነት ሲሰጥ ወስዶ መሥራት፤ ከተለያዩ ኮሚቴዎች የሚመጡ ኃላፊነቶችን አልችልም፤ ጊዜ የለኝም ብሎ አለመግፋት፤ ባሎቻቸው የሚስቶች ማደግ ለእነሱና ለቤተሰቡ ብሎም ለአገር ጠቃሚ መሆኑን እንዲረዱ ማድረግ፤ ችግር እንዳይፈጠርና ትዳር ፈርሶ ልጆች እንዳይበተኑ ማሳመንና መታገስ ከሴቷ እንደሚጠበቅ ይጠቁማሉ። መታገል፤ ሁል ጊዜ ውጤት ማምጣት፤ ሙሰኛ አለመሆን . . . የሴቶችን ሕይወት ለማሻሻልና አሁን ያሉበትን የኑሮ ሁኔታ ለመቀየር ሴቷ ወደ ላይ የግድ መምጣት አለባት። ልጄን፣ ማቄን፣ ቅሌን ብሎ ወደ ኋላ መቅረት ስለማይሠራ ከአጋሯ ጋር በመነጋገር በትግግዝ መወጣት ይኖርባታል።

"ወደ ፊት ሴቶች መሪዎች ካልሆኑ የሴቶችን ሕይወት ሊቀይሩ አይችሉም" ብሎ ማመን ያስፈልጋል። ‹‹የእኛን ዕድል አሳልፈን ለወንድ ከሰጠን አይሆንም›› ይላሉ። ቀጥለውም ይህ ዓይነቱ ቁርጠኝነት በሴቶች ውስጥ እንዲገነባ የሚያስችል ግንባታ የሚጀምረው ከቤተሰብ ነው። ወንድና ሴት ልጆች አብረው ሲያድጉ ሴቶች ከልጅነታቸው ጀምሮ ጠንካራ ሆነው እንዲያድጉ መደረግ አለበት። በትክክል በእኩልነት እንዲያድጉ የማድረግ ኃላፊነትን የመንግሥት ፖሊሲዎችም ሊደግፉ ይገባል። አቅም ያላት ሴት ወደ ፊት እንድትመጣ ማድረግ ያስፈልጋል። እኛ አገር ብዙ ሴቶችን ወደ ፊት ለማምጣት የሚያስችሉ ሁኔታዎች አሉ። አዋጆች፣ ፖሊሲዎች እየተሻሻሉ መጥተዋል። ወደ ታች ተወርዶ ሲታይ ግን ሴቶች ወደ ፊት እንዳይመጡ የሚደረግበት ሁኔታ አሁንም አልተቀረፈም። የሕግ ማዕቀፍን ብንወስድ አሁንም እንደገና መስተካከል አለበት። ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ እየወሰዷቸው ያሉ ሴቶችን የማብቃት ጉዳይ ጥሩ ሆኖ ሳለ፤ በከፍተኛ አመራር ላይ ያሉትን ሴቶች ለመተካት፤ ከመካከልም ሆነ ወደ ከፍተኛው ደረጃ ለማሳደግ በሕጉ በኩል ክፍተት ይታየኛል› ይላሉ። የሰዎች ጭንቅላት የተለያየ እንደመሆኑ ከአንዱ አንዱ የተሻለ ነገር ሊያመጣ ስለሚችል ሴቶችን ማብቃትና ማውጣቱ ከሥር ጀምሮ እንዲተኮርበትም ይጠይቃሉ። እኛም ‹‹ትምህርት ቤቴ ነው›› የሚሉትን ዓባይ ባንክ ከመሰሎቻቸው ጋር ከመመሥረት ጀምሮ ሰባት ዓመት የመሩትንና በርካታ አገራዊና ሥርዓት ያታን አመጣጣኝ አስተዋፅዖ ያበረከቱት ወይዘሮ መሰንበት ሸንቁጤ ያጋሩንን ተሞክሮ በዚሁ ቋጨን።

ኢኮኖሚ

# ባህልና ቱሪዝም

# የቀቤና ብሔረሰብ የበኲር ልጅ



ፎቶ፡-በመሳኩ ሔርሴ

**መሳኩ ሔርሴ**

የቀቤና ብሔረሰብ ባሕሉን፣ቅርሱንና ታሪኩን ጠብቆ የሚያቆይበትና ለማስጎብኘትም ምቹ የሆነ የባሕል ማዕከል ለመገንባት ሲያደርግ የነበረው ጥረት ተሳክቷል፤ ማዕከሉ ግንባታው ተጠናቆ ለምረቃ በቅቷል። ለስኬት ያበቁት ደግሞ በሀገር ውስጥ በተለያዩ አካባቢዎችና በዓለም ክፍሎች የሚኖሩ የብሔረሰቡ ተወላጆች ሲሆኑ፣ ተወላጆቹን በማስተባበርና ማዕከሉ ተገንብቶ ለምረቃ እንዲበቃ ደግሞ የቀቤና ልማት ማኅበር ትልቁን ድርሻ ተወጥቷል።

የባሕል ማዕከሉ ግንባታ የተከናወነው ከአዲስ አበባ 158 ኪሎ ሜትር ላይ በምትገኘው ወልቂጤ ከተማ መግቢያ ላይ ነው። ማዕከሉ በ2 ሺ472 ነጥብ 75 ካሬ ሜትር ላይ ያረፈ ሲሆን፤ በውስጡም የተለያዩ ክፍሎችን አካቶ የያዘ ነው። ከመሬት በላይ ሁለት ወለል፤ ከመሬት በታች አንድ ወለል ያለው ይህ የባሕል ማዕከል እስከ አንድ ሺህ ሰዎችን መያዝ የሚችል የመሰብሰቢያ አዳራሽ፣ 100 ሰዎችን ማስተናገድ የሚችል የቪ አይ ፒ መቀመጫ (ሰገነት)፣ ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውሉ ሁለት መለስተኛ አዳራሾች፣ 6 ቢሮዎች፣ ምስልና ድምፅን በአንድ ላይ ለመቅረጽ የሚያስችል ክፍል ወይንም አውዲዮ ቪዡዋል እና የሳውንድ ሲስተም ክፍልም በውስጡ ይዟል። በ58 ካሬ ላይ ያረፈ መስጂድ፣ 4 መድረሳዎች፣ 2 እንግዳ መቀበያ ክፍሎች፣ የብሔረሰቡን ባሕላዊ ቁሳቁሶች ለእይታ ለማቅረብ የሚያስችል ሙዚየም፣ መፀዳጃ ቤቶችን ጨምሮ የትርጉም ቤት እና ሌሎች ክፍሎች ይገኙበታል።

የማዕከል ግንባታውን ለማከናወን የተደረጉ ጥረቶችን በተመለከተ የቀቤና ልማት ማኅበር የቦርድ ሰብሳቢ አቶ ከማል ሡልጣን እንደገለጹት፤ የቀቤና የልማት ማኅበር በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር ያሉ የብሔረሰቡ ተወላጆችን በማስተባበርና ከመንግሥትና ከሌሎችም የልማት ደጋፊዎች ጋር በመሆን የቀቤና ብሔረሰብ ባሕል፣ ታሪክ፣ ቋንቋና ሌሎችም እሴቶችን ጠብቆ ለማቆየትና ለትውልድ ለማሸጋገር በማሰብ የባሕል ማዕከሉን በመገንባት ለማስመረቅ ችሏል።

ማዕከሉ የቀቤና ብሔረሰብ በትናንትናዋ ኢትዮጵያ በሀገርና ሀገረ መንግሥት ግንባታ በቀቤና አባቶች ለተደረገው ትግልና ለትግሉ ትሩፋት ማስታወሻ እና ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የአሁኑ ትውልድ አሻራ መሆኑን በመጥቀስ፣ ከታሪክ ምንነት እና ከወደፊቱ ተስፋ አንጻር በጥልቀት ሲጤን የባሕል ማዕከሉ መመረቅ ለብሔረሰቡ ተወላጆች ከምረቃዎች ሁሉ የተለየ ምስጢራዊ ትርጉም ያለው እንደሆነም ያስረዳሉ።

የአንድ ማኅበረሰብ ሕልውና የሚጠበቀው በሰፈረበት መልክዓ ምድር፣ ባሕሉን፣ ቋንቋውን እና እምነቱን መሠረታዊ ይዞታውን ሳይለቅ በማቆየትና ዘመኑ በደረሰበት ቴክኖሎጂ በማበልጸግ ለትውልድ ማስተላለፍ ሲቻል ነው ያሉት የቦርድ ሊቀመንበሩ፤ በዘመነ ሉዓላዊነት ለትውልድ የሚተላለፈው ባሕል ከሌሎች ባሕሎች ጋር ያለው መስተጋብር እንዳለ ሆኖ የራሱ እሴቶች የሚቀጥሉበት ቋንቋም ሆነ ታሪኩ በሌሎች ተፅዕኖ ስር ሳይወድቅ ትውልድ የሚቀባበልበት ሥርዓት ሲኖር መሆኑንም አንስተዋል።

ይህንን በተረዱት ጥቂቶች ትግል የተጀመረውን የሕዝብ ጥረት በመደገፍ የቀቤና ልማት ማኅበር የወረዳውንና፣ በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች እንዲሁም በተለያዩ የዓለም ሀገራት የሚገኙ የብሔረሰቡ ምሁራን፣ ተወላጆች እና ሌሎችም የልማቱ ደጋፊዎችን በማስተባበር በባሕል፣ በታሪክ፣ በቋንቋ እንዲሁም በወረዳው ልማትን በማፋጠን የኅብረተሰቡን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ከመንግሥት ጋር በመሆን የተለያዩ የልማት ተግባራትን በማከናወን ላይ እንደሚገኝ አስታውቀዋል።

ከነዚህ የልማት ተግባራት መካከል የቀቤና ባሕል ማዕከል ግንባታ አንዱ ነው ያሉት አቶ ከማል፤ ማዕከሉ የብሔረሰቡን የባሕል፣ የቋንቋ፣ የታሪክ እና የእምነት እሴቶችን በማሰባሰብ በአግባቡ ጠብቆ ለቀጣይ ትውልድ ለማስተላለፍ ከፍተኛ ፋይዳ እንደሚኖረው ተናግረዋል።

እንደ አቶ ከማል ማብራሪያ፤ የልማት ማኅበሩ በቀጣይ ጊዜያትም የብሔረሰቡን ባህል፣ ቋንቋ፣ ታሪክ እና እምነት ከማሳደግ በተጨማሪ መንግሥት በማይደርስባቸው የልማት ተግባራት በተለይም በትምህርት፣ በጤና በውሃ፣ በግብርና፣ በአካባቢና ተፈጥሮ ሃብት ጥበቃ እንዲሁም በራሱ የሚኮራና ለሀገር ጠቃሚ የሆነ ትውልድ ለመፍጠር የተለያዩ ተግባራትን ለማከናወን አቅዶ እየሠራ ይገኛል። በሀገር ውስጥና በውጭ የሚኖሩ የብሔረሰቡ ተወላጆች ለዚህ ተሳትፏቸውን እንዲያጠናክሩ ጠይቀዋል።

የቀቤና ወረዳ ዋና አስተዳዳሪ አቶ ዘይኑ ሻቡዲን በበኩላቸው፤ የቀቤና ባሕል ታሪክ ቋንቋና ቅርስ ለመጪው ትውልድ ለማስተላለፍ፣ ሕዝቡንና ደጋፊዎችን በማስተባበር



**በቀቤና ብሔረሰበብ ተወላጆች የተገነባው የብሔረሰቡ የባህል ማዕከል በቅርቡ በደማቅ ሥነ ስርዓት ተመርቋል**

የባሕል ማዕከሉን ማስገንባት መቻሉን ጠቁመዋል። ማዕከሉ ለቀቤና የበኲር ልጅ ነው ያሉት አስተዳዳሪው፤ የበኲር ልጅን ለምረቃ ለማብቃት ሕዝቡ ብዙ ውጣ ውረዶችን አልፏል ብለዋል።

የበኲር ልጅ ለመውለድ ምጥ የሚያስቸግር መሆኑን ያስታወሱት አስተዳዳሪው፤ የቀቤና ሕዝብም የበኲር ተቋሙን ለማጠናቀቅ ብዙ ውጣ ውረዶችን ማሳለፉን ጠቁመው፤ ከዚህ በኋላ ሌሎች ተቋማትን ለመገንባት የሚያስችል አቅም መገንባቱን ጠቁመዋል። የሕዝቡን የመፈጸም እና የማስፈጸም አቅም ያሳየበት መሆኑንም አንስተዋል።

እንደ አቶ ዘይኑ ማብራሪያ፤ የማዕከሉ ፋይዳው ከፍ ያለ ነው። የባሕል ማዕከሉ የቀቤና ሕዝብ ቅርሶች የሚደራጅበት፣ የቀቤንሲና ቋንቋ ማበልጸጊያ እና በቋንቋው ዙሪያ ጥናትና ምርምር የሚደረግበት፣ እና መድረሳ ጨምሮ የያዘ ነው። በተጨማሪም የቀቤና ሽማግሌዎች (የአገት) አባቶች የሕዝባቸውን ጉዳይ በቢሮ ውስጥ ተመካክረው እንዲፈቱ ምቹ ሁኔታ የፈጠረ ማዕከል ነው። ትላልቅ ሀገራዊ መድረኮችን ለማስተናገድ የሚችል ሀገራዊ፣ ክልላዊ እና ዞናዊ እንዲሁም መንግሥታዊ እና መንግሥታዊ ያልሆኑ አካላት የሚያዘጋጁዋቸውን መድረኮች ለማስተናገድ ብቁ የሆኑ አዳራሾችን የያዘ ነው። በመሆኑም የባሕል ማዕከሉ የብሔረሰቡ ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያ ፕሮጀክት ነው።

ማዕከሉ መንገድ ዳር እንደመሆኑ ከፈጣሪያቸው ለመገናኘት የሚፈልጉ እስልምና እምነት ተከታዮች እንዲጸልዩ የሚያስችል መስጂድ ጭምር እንዲኖረው መደረጉን ጠቁመዋል።

የጉራጌ ዞን አስተዳዳሪ አቶ ላጫ ጋሩማ በበኩላቸው፤ የባሕል ማዕከሉ ለጉራጌ ዞን ብቻ ሳይሆን ለደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልል ሞዴል የሚሆን ነው ብለው፤ የባሕል ማዕከሉ ለዞኑ እና ለወልቂጤ ከተማ ተጨማሪ ውበት የሆነ ነው። ማዕከሉ በሕዝብ ትብብር ተዓምር መሥራት እንደሚቻል ያሳየ ነው በማለት የማዕከሉን ዘርፈ ብዙ ፋይዳዎች ጠቁመዋል።

እንደ አቶ ላጫ ማብራሪያ፤ የባሕል ማዕከሉ ተገንብቶ መጠናቀቁ አከባቢውን የኮንፍረንስ ቱሪዝም ማዕከል ያደርጋል። የባሕል ማዕከሉ ገንብቶ ለማጠናቀቅ በርካታ ዓመታት ያስቆጠረ ቢሆንም እንኳ በኅብረተሰቡ ተሳትፎ ትላልቅ ፕሮጀክቶችን ጀምሮ ማጠናቀቅ እንደሚቻል ማሳያ ነው።

ባሕል የአንድ ሕዝብ ማንነት መገለጫ በመሆኑ ለዚህ ትኩረት ሰጥተው በመሥራት እውን ላደረጉ አካላት ክብር ይገባቸዋል ያሉት የዞኑ ዋና አስተዳዳሪ፤ የባሕል ማዕከሉ ግንባታ ቢጠናቀቅም ተጨማሪ ሥራዎች ያስፈልጉታል ብለዋል። በቀጣይነትም የባሕል ማዕከሉ የጥናትና ምርምር፣ የኮንፈረንስ ማዕከል እንዲሁም የመዝናኛ ማዕከል እንዲሆን የማዕከሉን ግቢ ውስጥ የማስዋብ ቀሪ ሥራዎችን በመሥራት ሁሉም ርብርብ ሊያደርግ እንደሚገባ ገልጸዋል።

በባሕል ማዕከሉ ምረቃ መርሐ ግብር ላይ የተገኙት የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልል ምክር ቤት አፈ ጉባኤ ወይዘሮ ፋጤ ሰርሞሎ እንደተናገሩት፤ የቀቤና ብሔረሰብ ሕገ መንግሥቱና የፌዴራል ሥርዓቱ ካጎናጸፋቸው መብቶች ተጠቃሚ በመሆን ባሕሉን ቋንቋውን እና ታሪኩን ጠብቆ በማሳደግ ረገድ የተለያዩ ተግባራትን እያከናወነ ይገኛል። ለዚህም የቀቤና ብሔረሰብ የባሕል ማዕከል አንዱ ማሳያ ነው።

ኢትዮጵያ በዩኔስኮ የተመዘገቡ የሚዳሰሱና የማይዳሰሱ ቅርሶች ባለቤት መሆኑዋን የጠቆሙት አፈ ጉባኤዋ፤ የብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የኢኮኖሚያዊ፣ የማኅበራዊና የአስተዳደራዊ ሥነ ምግባር፣ የሥነ ልቦና ሁኔታዎች፣ የሥነ ቃልና ቋንቋ፣ የምግብ አዘገጃጀት፣ አመጋገብ፣ የቤት አሠራር፣ የአልባሳት፣ ጌጣ ጌጥና ሌሎች እሴቶች የባሕል አካል መሆናቸውን ጠቁመዋል። እነዚህን የባሕል እሴቶችን ጠብቆ ለማቆየት፣ ከትውልድ ወደ ትውልድ ለማሸጋገር፣ ለማስተዋወቅ፣ የሥራ እድል ለመፍጠር ባሕል ማዕከሎች ሚናቸው የጎላ ነው ያሉት አፈ ጉባኤዋ፤ ከዚህ ባሻገር በዚህ ዘርፍ የሚመራመሩ ተመራማሪዎች እና ለጸሐፊዎች እንደ ቋሚ የመረጃ ማዕከል ሆኖ የሚያገለግል ነው። በተጨማሪም የባሕል ማዕከሎች ሥራ እድል በመፍጠር ፤ በአግባቡ ከተያዙ ደግሞ የቱሪስት መዳረሻ የመሆን እድላቸው ሰፊ ነው።

የቀቤና ባሕል ማዕከል ከኢትዮጵያ መዲና አዲስ አበባ በቅርብ ርቀት ላይ የሚገኝ በመሆኑ በአካባቢው ከሚገኙ ሌሎች የቱሪስት መስሕቦች ጋር ተዳምሮ የቱሪስት ቀልብ ለመሳብ እንደሚረዳ ገልጸዋል፤ ባሕል ማዕከሉ መገንባቱ የቀቤና ብሔረሰብ ሕገ መንግሥቱ ያጎናጸፈውን ባሕልን ታሪክን የመጠበቅ፣ የመንከባከብ እና ለቀጣይ ትውልድ የማስተላለፍ መብቱን እንዲጠቀም ይረዳል ብለዋል።

የወረዳው ሕዝብ ለባሕሉ ካለው መልካም አስተሳሰብና ለቀጣይ ትውልድ ለማስተላለፍ ካለው ጽኑ ፍላጎት ሀገር ውስጥ እና በውጭ የሚኖሩ የብሔሩ ተወላጆች የሕዝቡን አቅም በልማት በማኅበሩ አማካኝነት በማስተባበር ያስመዘገቡት ስኬት የሚደነቅ መሆኑን አንስተው፤ የቀቤና ሕዝብ በልማት ማኅበሩ አማካኝነት ያስገነባው ማዕከሉ ለሌሎች በአርዓያነት የሚጠቀስ ነው ሲሉ አብራርተዋል።

በባሕል ማዕከሉ ምረቃ ሥነ ሥርዓት ላይ ከሀገር ውስጥ እና ከውጭ ሀገራት የመጡ የብሔረሰቡ ተወላጆች፣ የፌደራል፣ የክልልና የዞን ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች፣ ከአጎራባች ዞኖች የተውጣጡ የሀገር ሽማግሌዎች፣ የብሔረሰቡ ተወላጆችና ሌሎችም ተገኝተዋል። የባሕል ማዕከሉ ተገንብቶ ለምረቃ በመብቃቱ ደስተኛ መሆናቸውን የብሔረሰቡ ተወላጆች ተናግረዋል።

ከብሔረሰቡ ተወላጆች መካከል ሐጂ አባድር አክመል እንዳሉት የማዕከሉ ግንባታ እጅግ ዘግይቶም ቢሆን ተጠናቆ በማየታቸው ደስተኛ መሆናቸውን ጠቁመዋል። የማዕከሉ ግንባታ ተጠናቆ ለአገልግሎት ክፍት ሆኖ ማየታቸው እንደ ዳግም የመወለድን ያህል ያስደስታል ያሉት ሐጂ አባድር የማዕከሉ ፋይዳም ዘርፈ ብዙ ነው ብለዋል። በተለይም የሕዝቡን አንድነት በማጠናከር ረገድ ከፍ ያለ ፋይዳ እንደሚኖረው ጠቁመዋል።

በምረቃ ሥርዓቱ ላይ ከተገኙት እንግዶች መካከል ከሀዲያ ዞን አርቲስት ካሳሁን ለማ እና ከጉራጌ ዞን ማረቆ ወረዳ አርቲስት ነጋሳ ሲጃ ማዕከሉ ለምረቃ በመብቃቱ ደስተኛ መሆናቸውን ጠቁመዋል። ማዕከሉ ለቀቤና ወረዳ ብቻ ሳይሆን ለአጎራባች ሕዝቦች ያለው ፋይዳ ከፍ ያለ መሆኑን አንስተዋል።

# ሳምንቱን በታሪክ

# የታሪክ ነጋሪው ታሪክ

**ዋለልኝ አየለ**

ባለፈው ረቡዕ ‹‹ዘመን በአዲስ ዘመን›› በሚል በዚሁ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ አንድ መጣጥፍ አውጥተን ነበር። አዲስ ዘመን ጋዜጣ የዘመን መስታወት ነው ብለናል። የዘመን መስታወት ነው ማለት በየዘመኑ የነበሩ ሁነቶችን ያሳየናል ማለት ነው። በዚህ ‹‹ሳምንቱ በታሪክ›› በተሰኘው ዓምድ እንኳን ብዙ ታሪኮችን አይተንበታል።

ዛሬ ደግሞ የራሱን ታሪክ ልናይ ነው። የዘመን መስታወት የሆነው አዲስ ዘመን ጋዜጣ መታተም የጀመረው ከ82 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ነው። የጋዜጣው 82ኛ ዓመት ባለፈው ረቡዕ ግንቦት 30 ቀን 2015 ዓ.ም በኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ሠራተኞችና አመራሮች ተከብሯል። ይህ የዜናም የታሪክም ነጋሪ የሆነ ጋዜጣ እስኪ ዛሬ የራሱን ታሪክ እናስታውስለት።

ከታሪክ መጻሕፍት ጀርባ ማጣቀሻ ሆኖ እናገኘዋለን። የታላላቅ ሰዎች ግለ ታሪክ ሲጻፍ ምንጭ ሆኖ ይገኛል። የታላላቅ ደራሲዎችና ፖለቲከኞች ሥራዎች ይገኙበታል። ወደ አንድ ምዕተ ዓመት የተጠጉ ሁነቶች ተሰንደው ይገኙበታል። ከ80 ዓመታት በፊት የነበሩ የኢትዮጵያ ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ጥበባዊ ሁኔታዎች ይገኙበታል። አዲስ ዘመን ጋዜጣ!

በዚህ ‹‹ሳምንቱ በታሪክ›› በሚለው ዓምድ ሥር ከብዙ ዓመታት በፊት በሳምንት ውስጥ የተከሰቱ ክስተቶችን የምናስታውሰው እንደ አዲስ ዘመን ጋዜጣ ያሉ አንጋፋ ታሪክ ሰናጆች ባስቀመጡት ሰነድ ነው። የሌሎችን ክስተቶች ታሪክ ሲናገር የኖረው አዲስ ዘመን ጋዜጣ የራሱ ታሪክ በጣም ሰፊ ይሆናል ማለት ነው።

አዲስ ዘመን ጋዜጣ በዕለተ ቅዳሜ ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተመሠረተ። እነሆ ለ82 ዓመታት የአገሪቱ ብቸኛ ዕለታዊ ጋዜጣ በመሆን የአራት ሥርዓተ መንግሥታትን (የአሁኑን ጨምሮ) ምንነት ሰንዶ አስቀምጧል፤ እያስቀመጠ ነው። የእነዚህ መንግሥታት ባሕሪም የሚታወቀው በዚሁ ጋዜጣ ነው።

አሁን ላይ ያለ ወጣት ንጉሣዊ ሥርዓቱ ምን አይነት እንደነበር አያውቅም። ቤተ መጻሕፍት በመግባት ግን ከአዲስ ዘመን ጋዜጣ ማግኘት ይችላል። የጋዜጣ ሰነድነት ከመጻሕፍትና ከሌሎች ሰነዶች ይለያል። ምክንያቱም ዜናዎች አሉበት። ዜና በወቅቱ ዜና ይሁን እንጂ ከዘመናት በኋላ ግን ታሪክ ይሆናል። ምክንያቱም የመንግሥታት ዕለታዊ ክንውኖች ስለሚጻፉበት ማለት ነው።

አዲስ ዘመን ጋዜጣ ስሙ ከታላላቅ ደራሲዎች ጋር ይነሳል። የእነዚህ ደራሲዎች ስም ሲነሳ አዲስ ዘመን፤ የአዲስ ዘመን ስም ሲነሳ የእነዚህ ደራሲዎች ስም ተያይዞ ይጠራል። በተለይ የበዓሉ ግርማ እና የጳውሎስ ኞኞ ግን ይደጋገማል። ምክንያቱም እነዚህ ደራሲዎች በታሪክ እና በፖለቲካ ውስጥ ከፍተኛ ተፅዕኖ ስለፈጠሩ ነው። ደራሲና ጋዜጠኛ ብርሃኑ ዘሪሁን እና ደራሲ ስብሐት ገብረእግዚአብሔር አዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ የሠሩ ታላላቅ ደራሲዎች ናቸው። ብርሃኑ ዘሪሁን የጋዜጣው ዋና አዘጋጅ ነበር። ሌሎች አንጋፋና ወጣት ደራሲዎችም በአዲስ ዘመን ጋዜጣ በቋሚ ተቀጣሪነትም በፍሪላንሰርነትም፣ በውጭ ጸሐፊነትም የሠሩ ብዙ ናቸው። እነ ማዕረጉ በዛብህ፣ ደራሲ ዘነበ ወላ፣ አንተነህ ይግዛው.... ይጠቀሳሉ። እስኪ ከአዲስ ዘመን ጋዜጣ ታሪክ ጋር ስማቸው የሚነሳውን ታላላቅ ደራሲዎች እና የአዲስ ዘመን ጋዜጣን የታሪክ፣ የጋዜጠኝነትና ሥነ ጽሑፍ ትዝታዎች እናስታውስ።

**በዓሉ ግርማ**

በዓሉ ግርማ የአዲስ ዘመን ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ የነበረ እና የሥነ ጽሑፍ አርበኛ ነው። በዓሉ ግርማ በተለይም ‹‹ኦሮማይ›› በተሰኘው መጽሐፉ ጋዜጠኝነትንም ሥነ ጽሑፍንም አሳይቷል።

መጽሐፉ ጋዜጠኝነትንና ሥነ ጽሑፍን የያዘ ነው። እንደ ጋዜጠኛ ያየውንና የሰማውን ጽፏል። የጋዜጠኛን ድፍረት አሳይቷል። ጋዜጠኛ አድርባይ፣ ወላዋይና ፈሪ መሆን እንደሌለበት አሳይቷል።

የጋዜጠኝነት ሙያ ሕይወትን እስከማጣት መስዋዕትነት የሚከፈልበት መሆኑን በተግባር አሳይቷል።

እንደ ሥነ ጽሑፍ ካየነውም፤ እነሆ መማሪያ እስከመሆን ደርሷል። ለብዙ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የጥናትና ምርምር ምንጭ ሆኗል። በጋዜጠኝነት ትምህርት ቤትም በሥነ ጽሑፍ ትምህርት ቤትም ማነፃፀሪያ ተደርጓል። የሥነ ጽሑፍ አላባውያን ለሚባሉት መሠረት ሆኗል። በየሥነ ጽሑፍ ውይይቱ የበዓሉ መጽሐፎች ስም ይነሳል። አገላለጾቹ ሥነ ጽሑፋዊ ውበት ያላቸው ናቸው። ረቂቅ አገላለጽ ይጠቀማል። ተምሳሌታዊ ትርጓሜን አሳይቷል። ፍቅርን አሳይቷል። ለሕይወቱ መጥፋት ምክንያት ስለሆነ እና ፖለቲካዊ ይዘት ስለሆነ ‹‹ኦሮማይ›› ተደጋገመ እንጂ ሌሎች መጽሐፎችም አሉት። የቀይ ኮከብ ጥሪ የሚለው መጽሐፉም እንዲሁ ፖለቲካና ሥነ ጽሑፍን የያዘ ነው። ከአድማስ ባሻገር በብዛት የሚደጋገመው በሥነ ጽሑፍ ሰዎች ዘንድ ነው። ሀዲስ፣ ደራሲው እና የሕሊና ደወል የሚሉትም ቢሆን ተደጋግመው የተነበቡ ናቸው። በአጠቃላይ በዓሉ ግርማ ለሥነ ጽሑፍና ለጋዜጠኝነት ሙያ መስዋዕት የሆነ ሰው ነው። እንደ ታሪክ ደግሞ በወቅቱ የነበረውን ክስተት አሳይቷል። ስለዚህ የበዓሉ ግርማ እና የአዲስ ዘመን ጋዜጣ ታሪክ የጋዜጠኝነትም ታሪክ ነው።

**ጳውሉስ ኞኞ**

ጋዜጠኛ የሆኑም ያልሆኑም ሰዎች ስለ ጳውሎስ ኞኞ እና አዲስ ዘመን ጋዜጣ አንድ ነገር ያውቃሉ። ይሄውም ‹‹አንድ ጥያቄ አለኝ›› የሚለው የጳውሎስ ኞኞ ጽሑፍ ነው። የትም ቦታ የጳውሎስ ኞኞ ስም ከተነሳ አዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ የነበረው ይሄ ዓምዱ ይጠቀሳል። ጳውሎስን ለማስታወስ ሲባልም የሬዲዮ ፕሮግራም እና የሕትመት ዓምዶችም ወጣ ገባ እያሉ ተሰይመዋል። በኩረጃ ሳይሆን እሱን ለማስታወስ መሆኑን እየጠቀሱ ማለት ነው።

ስለጳውሎስ ኞኞ የጋዜጠኝነት ፍቅር አንድ ጓደኛው የነበረ ሰው በሬዲዮ ሲናገር የሰማሁትን ገጠመኝ ላካፍላችሁ። ጳውሎስ ታሞ ተኝቶ ነው። ጓደኞቹ ሊጠይቁት ከቤቱ ይሄዳሉ። ሲሄዱ በፀና ታሞ ተኝቷል። ብዙም አያናግራቸውም፤ በሕመም ላይ እናጨናንቀውም ብለው ዝም ብለዋል። በቤቱ ውስጥ የተከፈተው ሬዲዮ እያወራ ነው። ጋዜጠኛው አንድ ስህተት ይሳሳታል። ይህኔ ጳውሎስ ‹‹አይ! አዳምጡትማ ይሄን ጋዜጠኛ...›› ብሎ የጋዜጠኛውን ስህተት አስተካክሎ ነገራቸው። በሕመም ላይ ያለ ሰው፤ እንኳን ስህተትን ነቅሶ ማውጣት ስለምን እየተወራ እንደሆነ ራሱ ልብ አይልም ነበር። ጳውሎስ ኞኞ ግን በሕመም ውስጥ ሆኖ እንኳን መረጃን እያጣራ ይሰማ ነበር ማለት ነው።

ስለ ጳውሎስ ኞኞ የሚነገር ሌላ አንድ አስቂኝ ገጠመኝ ደግሞ አለ። ለስቴዲየም መሥሪያ ተብሎ መዋጮ እየተዋጣ ነው። የኳስ ነገር ያልጣመው ጳውሎስ ‹‹ኧረ ይሄ ነገር ይቅር›› ይላል። በጣም ወሳኝ ጉዳይ እንደሆነ ሲነግሩት ‹‹አሥራ አንድ ጅሎች አንድ ቅሪላ ሲከታተሉ ለማየት አላዋጣም›› ብሎ የተሰበሰበው ብር ለሆስፒታል ግንባታ መዋል እንዳለበት ተናግሯል።

ጳውሎስ ኞኞን የሚያውቀው ሁሉ አንድ የሚያውቀው ታሪኩ ደግሞ በመደበኛው ትምህርት ከ4ኛ ክፍል በላይ ያልተማረ ምሑር መሆኑ ነው። የታሪክ ተመራማሪ ነው። በኢ-መደበኛ ትምህርት እና በጥልቅ ንባብ ምሑር መሆን እንደሚቻል ያሳየ ሰው ነው። ‹‹የሴቶች አምባ፣ አጤ ምኒልክ ፣ አጤ ቴዎድሮስ፣ አስደናቂ ታሪኮች፣ የኢትዮጵያና የጣሊያን ጦርነት፣ አራዳው ታደሰ፣ የኔዎቹ ገረዶች፣ የጌታቸው ሚስቶች፣ ምስቅልቅል፣ እንቆቅልሽ፣ አጤ ምኒልክ ከውጭ ሀገራት የተፃፃፏቸው ደብዳቤዎች፣ አጤ ምኒልክ በሀገር ውስጥ የተፃፃፏቸው ደብዳቤዎች›› የጳውሎስ ኞኞ መጽሐፎች ናቸው። ይሄ ሰው ጋዜጠኛ፣ ደራሲ፣ የታሪክ ተመራማሪ ብቻ አልነበረም። በእርሻ ሚኒስቴር (ለዚያውም ገና በ17 ዓመቱ) የእንስሳት ሐኪም ሆኖም ሠርቷል።

ጳውሎስ በጋዜጠኝነት ዘርፍ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ፣ በኢትዮጵያ ድምፅ ጋዜጣ፣ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፣ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን እንዲሁም በኢትዮጵያ ራዲዮ ለዓመታት መረጃ በመስጠት፣ በማስተማርና በማዝናናት ሕዝብን በማንቃት በጋዜጠኝነት ሙያው አንቱታን አትርፏል።

ጳውሎስ ኞኞን ዛሬ የምናስታውሰው ከአዲስ ዘመን ጋዜጣ ጋር ባለው ታሪክ ብቻ አይደለም። የራሱ የሕይወት ታሪክም በዚህ ሳምንት ስለሚታወስ ነው። ጳውሎስ ኞኞ ሕይወቱ ያለፈው ከ31 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ግንቦት 29 ቀን 1984 ዓ.ም ነው። ከአዲስ ዘመን ጋር ያላቸውን ቁርኝት የሥራ ታሪክ ብቻ ሳይሆን የሕይወት ታሪኩም አቀራርቦታል ማለት ነው። እነሆ መልካም ስም ከመቃብር በላይ ይውልና ሲወደስ ይኖራል።

**ብርሃኑ ዘሪሁን**

ዕውቁ የሥነ ጽሑፍና የታሪክ ሰው ብርሃኑ ዘሪሁን የአዲስ ዘመን ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ ነበር። የጋዜጣው ዋና አዘጋጅ እያለ ከመንግሥት ጋር ይጋፈጥ እንደነበርም ይነገራል።

ብርሃኑ ዘሪሁን በኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ ውስጥ ትልቅ አሻራ አስቀምጧል። ለታሪካዊ ልቦለድ አጻጻፍ ፈር ቀዳጅ ሆኗል። የተውኔት ሥራዎችን እና የታሪክ ምርምሮችን ሠርቷል።

‹‹የቴዎድሮስ እንባ፣ የታንጉት ምስጢር፣ ማዕበል የአብዮት ዋዜማ፣ ማዕበል የአብዮት መባቻ፣ ማዕበል የአብዮት ማግስት፣ ጨረቃ ስትወጣ››፣ አማኑኤል ደርሶ መልስ፣ የእንባ ደብዳቤዎች፣ የበደል ፍፃሜ›› የሚሉት መጻሕፍት ሲሆኑ፤ ‹ባልቻ አባነፍሶ፣ ‹‹ጣጠኛው ተዋናይ፣ የለውጥ አርበኞች፣ ሞረሽ...›› የተሰኙ ተውኔቶችን ጽፏል። የአዲስ ዘመን ጋዜጣ ታሪክ ሲነሳ የእነዚህ ሁሉ ሰዎች ታሪክ ነው የሚነሳው። ለዚያውም ትልልቅ ፖለቲካዊ ጉዳዮች ሳይዳሰሱ ማለት ነው። በግለሰብ ደረጃ እንኳን የአዲስ ዘመን ጋዜጣን ስም የሚያስጠሩ ብዙ ታላላቅ ሰዎች አሉ።

በፖለቲካው ዘርፍ ደግሞ ንጉሣዊ ሥርዓቱ ምን እንደነበር፣ በወቅቱ ምን አይነት ዜናዎች ይሠሩ እንደነበር፣ ምን አይነት ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች ይደረጉ እንደነበር ይነገረናል። በወታደራዊው የደርግ መንግሥትም ሆነ በአብዮታዊው ኢሕአዴግ ዘመን የነበሩ ሁነቶችን ሁሉ ከዚሁ ጋዜጣ ላይ ማግኘት ይቻላል። እነሆ በአሁኑ የብልጽግና አስተዳደርም አዲስ ዘመን ጋዜጣ ዕለታዊ ሁነቶችን እየዘገበ ዛሬን ለነገ እያስቀመጠ ነው።

ጋዜጣው ‹‹አዲስ ዘመን›› የሚለውን ስያሜ እንዴት አገኘ? የሚለውን እና የመጀመሪያው ዕትም ላይ የወጡ ጽሑፎችን እናስታውሳችሁ።

ቀዳማዊ አፄ ኃይለሥላሴ ሚያዝያ 27 ቀን 1933 ዓ.ም ከስደት ከቆዩበት እንግሊዝ ተመልሰው አዲስ አበባ ሲገቡ ለሕዝቡ ባደረጉት ንግግር ‹‹... ከማናቸውም አስቀድሞ ለሁላችሁም ልነግራችሁና ልትረዱት የምፈልገው ይህ ቀን ለአዲሲቱ ኢትዮጵያ የአዲስ ዘመን መክፈቻ መሆኑን ነው። በዚህም በአዲስ ዘመን ሁላችን መፈፀም ያለብን አዲስ ሥራ ይጀመራል ...›› ብለው ስለነበር ጋዜጣውም ‹‹አዲስ ዘመን›› ተብሎ ተሰየመ።

በጋዜጣው የመጀመሪያ ዕትም የመጀመሪያ ገጽ ላይ ንጉሠ ነገሥቱ በፋሺስት ኢጣሊያ ወረራ ምክንያት ከአምስት ዓመታት የስደት ቆይታ በኋላ አዲስ አበባ ሲገቡ የሚያሳየውን ፎቶግራፍ እና ስለጋዜጣው ዓላማ የሚገልፅ ጽሑፍ ወጥቶ ነበር።

‹‹ ... ይህ አዲስ ዘመን ተብሎ የተሰየመው ጋዜጣ ከዛሬ ጀምሮ ወደፊት ለመላው ለኢትዮጵያ ሕዝብ የረዳትነቱን ሥራ ይሠራ ዘንድ ተመሠረተ። ግርማዊ ቀዳማዊ አፄ ኃይለሥላሴ ለኢትዮጵያ አዲስ በሆነው ዘመን ለአገርና ለሕዝብ ጥቅም የሚያስፈልገውን ሥራ ሁሉ እያመለከተ፤ ይልቁንም ሕዝብ ለአገሩ፣ ለመሪውና ለንጉሠ ነገሥቱና ለንጉሠ ነገሥቱም መንግሥት ማድረግ የሚገባውን እየገለፀ የበጎን ሥራ መንገድ የሚመራ እንዲሆን ይህ ጋዜጣ በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ተመሠረተ።

ሥራውም በሦስት ቃሎች ይጠቀለላል። እውነት፣ ረዳትነትና አገልግሎት። እውነት ስንል በዚህ ጋዜጣ የሚነገረው ነገር ሁሉ መሠረቱ በፍጹም እውነትን እየተከተለ ለአንድ ጥቅም ብቻ ያልሆነና ለመላው ጥቅም የሚሠራ እንዲሆን ነው። አገልግሎት ስንል የኢትዮጵያን ነፃነት ለመመለስ ራሳቸውን መስዋዕት አድርገው የራሳቸውን ጥቅም ሁሉ አስወግደው ለሕዝባቸውና ለአገራቸው ሲሉ የሰው አቅም ሊሸከመው የማቻለውን ድካም ተቀብለው ማንኛውም ሰው ሊያደርገው ያልተቻለውን በኢትዮጵያ ሕይወት ውስጥ እስከዛሬ ድረስ ያልታየውን ሥራ ከፍፃሜ ላደረሱ ለተወደዱ ንጉሠ ነገሥታችንና ላቆሙት መንግሥት የሚያገለግል እንዲሆን ነው...›› የሚል ነበር።

አዲስ ዘመን ጋዜጣ ዕለታዊ ሁነቶችን እየዘገበ እነሆ 82 ዓመታት ተጓዘ።



የአዲስ ዘመን ጋዜጣ የመጀመሪያው ዕትም (ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም)

# የዝነኞች ገጽ

# የኮይሻ ሴታ ውስታ

ሙሉጌታ ብርሃኑ



አስታዋሽ ያጣ የጥበብ ባለውለታ መሆን የኮይሻ ሴታ ዕጣ ፈንታ ይመስላል። በባሕል ሙዚቃ ውስጥ ያልታየውን እንዲታይ፣ ያልተደመጠውንም እንዲደመጥ ያደረገ፤ ብዙ አሳይቶ እርሱ ግን ምንም ሳይታይ አሳዛኝ በሆነ የሕይወት መስመር ውስጥ አልፎ እስከወዲያኛው ሄደ። እነዚህ ከኮይሻ ሴታ የሕይወት ማኅደር ውስጥ የተቀነጨቡ እውነታዎች ናቸው። ኮይሻ ሴታ ተወልዶ ያደገው በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል በወላይታ ዞን በዳሞት ዳሌ ወረዳ አደ ዳሞት ቀበሌ ነው። ከልጅነቱ ጀምሮ በሙዚቃ ውስጥ የመኖርና ሙዚቀኛ የመሆን ትልቅ ሕልም ነበረው። ሕልሙ ሕልም ሆኖ ብቻም አልቀረም፤ በኢትዮጵያ ውስጥ ከአካባቢው በስተቀር እምብዛም የማይታወቀውን የወላይትኛ ሙዚቃን ተወዳጅና ተደማጭ ለማድረግ በቃ።

ኮይሻ አሃዱ ብሎ የሙዚቃ መሠረቱን ለመጀመሪያ ጊዜ የጣለው በተወለደባት አካባቢ በነበረው የቀበሌ የኪነት ባንድ ውስጥ ነበር። በ1971 ዓ.ም ባንዱን በመቀላቀል በሌሎች ሙዚቀኞች ሥራ ቢጀምርም፣ የኋላ ኋላ ግን የራሱን ሥራዎች እያቀረበ መጫወትም ጀመረ። የነበረው ተቀባይነትም ከባንዱና ከአከባቢው እየወጣና እየሰፋ ሄደ። በየመድረኩ ሁሉም ሰው 'ኮይሻ' ማለትና የእርሱን የሙዚቃ ጨዋታ መናፈቅ ጀመረ። ከደቡብ ምንጭ የፈለቀው የኮይሻ የሙዚቃ ጥበብ፣ ከደቡብ ወደ ምሥራቅና ምዕራብ እንዲሁም መስመሩን ሰንጥቆ ወደ ሰሜን በረዥሙ ፈሰሰ። ከሙዚቃ መድረኮች አልፎ በየእግር ኳስ ሜዳው የደጋፊዎች ማዕበል ኃይል ሆነው የሚጨፈርባቸው የሞራል ስንቅም ጭምር ናቸው።

ኮይሻ ሙዚቃዎቹ ተወዳጅ እንዲሆኑ ያደረገው በድምፅ ብቻ ሳይሆን ከድምፅ ጋር አጣምሮ በሚያሳያቸው የዳንስ ስልቶችም ጭምር ነው። ሙዚቃዎቹ በብዛት ቀድመው የነበሩ የሕዝብ ሙዚቃዎች ቢሆኑም በሙዚቃዎቹ ውስጥ የወላይታ ማኅበረሰብ ባሕልና ትውፊቶችን አስሶ በማውጣት በሀገር ደረጃ እንዲታወቁ አደርጓል። ከምንም ነገር በላይ ኮይሻ ለዚህ ማኅበረሰብ ባሕል ትልቅ ባለውለታ ነው። ዛሬ ላይ እንደ አሸን የፈላው የወላይታ ብሔር ተወዳጅ ሙዚቃና ሙዚቀኞች የኮይሻ ሴታ አሻራዎች ያረፉበት ናቸው።

'አሊ ጀናው' በ1984 ዓ.ም የሠራው የኮይሻ ሴታ የበኩር አልበሙ ነበር። ይህ አልበም የመጀመሪያ የሆነው ለኮይሻ ብቻ ሳይሆን በአልበም ደረጃ የተሠራ የመጀመሪያው የወላይትኛ ሙዚቃም ጭምር ነበር። ሙዚቃው በአምባሰል ሙዚቃ አሳታሚ ድርጅት አማካኝነት የተሠራ ሲሆን በዚህ አልበም ኮይሻ ትልቅ ውዝግብ ውስጥ ገብቶ ነበር። ማተሚያ ቤቱ ለኮይሻ 5 ሺህ ብር ሊከፍለው በመስማማት ከድምፃዊው ጋር ውል ይገባል። መጨረሻ ላይ በድምፃዊው እጅ የገባው ገንዘብ ግን 5 መቶ ብር ብቻ ነበር። ምንድነው ሲል በነገሩ ግራ የተጋባው ኮይሻ ይጠይቃል። የፈረምከው 5 መቶ ነው ተባለ። የት እንደገባች ያልታወቀቻው በ5 መቶና በ5 ሺህ መሐል ያለችው ይህቺ አንዲት ዜሮ ወደ ሌላ ችግር አመራች። በኋላ ላይ ግን ኮይሻ ቀጥ ብሎ ወደ ማተሚያ ቤቱ ባለቤት በመሄድ ጉዳዩን ያስረዳል። የማተሚያ ቤቱ ባለቤትም ነገሩን ካጤኑ በኋላ የተስማማውን 5 ሺህ ብርና በካሳ መልክ ደግሞ 1 ሺህ ብር ጨምረው እንደሰጡት ይናገራል።

አልበሙ ከወጣና አድማጭ ጆሮ ከደረሰ በኋላ የነበረው ተቀባይነትና ተደማጭነት ከተጠበቀው በላይ ሆነ። በየሙዚቃ ቤቱ የሚደመጠው የኮይሻ ሙዚቃ ነበር። ብዙ ነገሮች ለኮይሻ ቀና እየሆኑ የመጡ መሰሉ። ከወላይታ ተነስቶ አልበሙን ለመሥራት አዲስ አበባ የገባው ኮይሻ፣ አዲስ አበባን በጣም ወደዳት። የሙዚቃ ሥራውንም በተሻለ ለመሥራት በማሰብ እዚሁ አዲስ አበባ ከተመ። ነገር ግን ሁኔታዎች እንደጠበቀው አልሆንልህ አለው። የወደዳት አዲስ አበባ እርሱን ለመውደድ ተሳናት። በጉጉት ቢቀበላትም እርሷ ግን ጀርባዋን አዞረችበት። የትውልድ ቀዬውን ጥሎ፣ ልቡን በተስፋ ሞልቶ የነገ የሙዚቃ ትልሙን በአዲስ አበባ ቢመለከትም ሁሉም ነገር ግን የተገላቢጦሽ ሆነበት። ኑሮ በአዲስ አበባ ለእርሱ የዋዛ አልነበረችም። በፎ በምንም የማይከፈትና የማይገፋ ሆነ። ግራ መጋባቱ ከእለት ወደ እለት እየጨመረና ተስፋው እየተመናመነ መሄዱንም ቀጠለ። ሕይወቱ የጉዞ መስመሯን ስታ ወዲህና ወዲያ እንደምትናወዝ የባሕር ላይ መርከብ ሆነች። በወቅቱ እንዲህ እንዲሆን ያደረጉት በርካታ ምክንያቶች ነበሩ።

1980ዎቹ መባቻ ስሙ ገኖ የወጣበት ወቅት ነበር። ነገሩ ግን ፍየል ወዲህ ቅዝምዝም ወዲያ እንዲሉ የኮይሻ ሕይወት እንደስሙ አልነበረም። ስሙ ገኖ ሙዚቃውም ከጫፍ ጫፍ ማድመቂያ ሆኖ ሳለ የእርሱ ሕይወት ግን የደበዘዘና በማይነጋ ሌሊት ውስጥ እንዳለች ጨለማ ነበር። ብዙዎች የእርሱን ሙዚቃ አሳደው ሲያደምጡ፣ እርሱን ግን ከወዴት አለህ ብሎ የሚፈልገው አንድም ሰው አልነበረም። የኮይሻ ሙዚቃ እንደሻማ እያበራ፣ ኮይሻ ግን እንደሻማ ሲቀልጥ ነበር። በሀገር ውስጥ ከነበሩ ከተለያዩ ባንዶች ጋር በሃገር ውስጥና በውጭ ሃገራት እየተዘዋወረ ሥራዎቹን ቢያቀርብም ሕይወቱ ግን ከችግርና ስቃይ ለማምለጥ አልቻለችም። ብዙ ሰዎች የኮይሻን ግሩም ሙዚቃዎች ያውቃሉ ነገር ግን ሙዚቃው ምን አይነት ነው ከማለት በቀር ሙዚቃው የማነው ብለው አይጠይቁም።

ከዚህም የባሰው ደግሞ ጥቂት የማይባሉ ድምፃውያን የእርሱን ሙዚቃ እየወሰዱ ከፊትና ኋላ ግጥምና ዜማ እየለጣጠፉበት የመታወቅ አባዜአቸውን አርክተውበታል። 'በጨው ደንደስ በርበሬ ትወደስ' ሆነና የሙዚቃው ባለቤት የሆነው ኮይሻ ተቀብሮ በእርሱ ሙዚቃ ሌሎች ተወደሱበት፤ ተከብረው ነገሡበት። "ሁል ጊዜ ሙዚቃዎቹን በሰማሁ ቁጥር እንባ ይተናነቀኛል" ይላል ኮይሻ፤ ያለ እርሱ ፈቃድ ሙዚቃዎቹን ሰርቀው መኖሩን እንኳን ስለረሱት እያሰበ። በእርግጥም ሠርተው ምንም እንዳልሠሩ ልፋት መና ሲቀር በእጅጉ ልብን ይሰብራል። ከኮይሻ ሙዚቃዎች ተወስደው በጣም ተደማጭነትን ካተረፉ ሙዚቃዎች መሐከል ለአብነት ያህል እስቲ ሁለቱን እንመልከት።

'መቼ ትመጪያለሽ ሰኞ

ልጠብቅሽ ወይ ማክሰኞ

....... ....... ......

የዚህ ሙዚቃ ግጥሙ የተሠራው በአማርኛ ቢሆንም ዜማው ግን ሙሉ ለሙሉ የተወሰደው 'ጋሼ ወላሎሜ ሀያ' ከሚለው የኮይሻ ሙዚቃ ላይ ነው። ሌላው ሁለተኛው ሙዚቃ ደግሞ 'ቡሌ ኢያቡሌ' የተሰኘው ሙዚቃ ነው። በበርካቶች ዘንድ ተወዳጅና ተመራጭ ሙዚቃ ነበር። ለረዥም ጊዜያትም ተደማጭነት ነበረው። ይህን ሙዚቃ ከኮይሻ በመውሰድ ይዘቱን ጥቂት ለወጥ አድርጎ የሠራው በሕዝብ ዘንድ በጣም ተቀባይነትና ተወዳጅነት ያለው ድምፃዊ ቢሆንም ለዚህ ሙዚቃ መሠረት ከሆነው ከኮይሻ ፈቃድ ካለመጠየቁም ውጭ ምንም አይነት እውቅና አለመስጠቱ ፍጹም ስህተት ነው። እነዚህን ሁለት ሙዚቃዎች የማያውቅ አለ ብዬ አላስብም። የሙዚቃ አድማጭ ባንሆን እንኳን ሁኔታና አጋጣሚዎች እንድናውቃቸው ያደርጉናል። ብዙዎቻችን በሙዚቃዎቹ ስለመዝናናታችንም አልጠራጠርም፤ ቅሉ የሙዚቃዎቹን አባት ኮይሻን ባናስበውም።

‹‹ብዙዎች የእርሱን ሙዚቃ አሳደው ሲያደምጡ፣ እርሱን ግን ከወዴት አለህ ብሎ የሚፈልገው አንድም ሰው አልነበረም። የኮይሻ ሙዚቃ እንደሻማ እያበራ፣ ኮይሻ ግን እንደሻማ ሲቀልጥ ነበር። በሀገር ውስጥ ከነበሩ ከተለያዩ ባንዶች ጋር በሃገር ውስጥና በውጭ ሃገራት እየተዘዋወረ ሥራዎቹን ቢያቀርብም ሕይወቱ ግን ከችግርና ስቃይ ለማምለጥ አልቻለችም። ብዙ ሰዎች የኮይሻን ግሩም ሙዚቃዎች ያውቃሉ ነገር ግን ሙዚቃው ምን አይነት ነው ከማለት በቀር ሙዚቃው የማነው ብለው አይጠይቁም።››

የአሳዛኙ ድምፃዊ የመጨረሻዎቹ ሰዓታት በእጅጉ ቅስምን የሚሰብሩ ነበሩ። ወደ ኋላ ወደ ትውልድ መንደሩ መመለስም ሆነ በሚገኝባት አዲስ አበባ ወደፊት አንድ እርምጃ መሄድ ተስኖት በተስፋ መቁረጥ የደመነብስ ኑሮ መምራቱን ቀጠለ። ከሚኖርባት የቀበሌ ቤት ውስጥ ከመግባትና መውጣት ውጭ ሕልሙን የሚኖርባትን የሙዚቃ በር ግን አሁንም ለማግኘት አልቻለም። የእነዚያ ጣፋጭና ተወዳጅ ሙዚቃዎች አባት የሆነው ኮይሻ ሴታ ስም በሁሉም ኢትዮጵያዊ ልብ ውስጥ ቢገኝም ከእርሱ ጋር ግን ማንም አልነበረም። ኑሮው ቁልቁል እየተምዘገዘገ ሄዶ ከችግር ዋሻ ውስጥ ተፈጠፈጠ። የሚበላውን እንኳን እስከማጣት ደረሰ። ካገኘ ቀምሶ ካጣም ጾሙን ውሎ ማደር ጀመረ። በዚያች ቤት ውስጥ ሲኖር አጠገቡ ከነበሩት ጎረቤቱ በስተቀር ጎራ ብሎ የሚጠይቀውም ሆነ ከወዴት አለህ ብሎ የሚፈልገው ሰው አልነበረም።

ብዙ ጊዜ እየታመመ ለብቻው በተዘጋ ቤት ውስጥ እያቃሰተ ማንም ሳያውቅለት ለቀናት የማቀቀባቸው ጊዜያት ጥቂት የሚባሉ አልነበሩም። አቅሉን ከሳተበት አልጋ ላይ አንስተው የሰፈሩን ሰው በማስተባበር ሕክምና እንዲያገኝ ያደርጉ እንደነበርም ጎረቤቱ የነበሩት ሰው ከአንድ ሚዲያ ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ ላይ ገልጸው ነበር። ያለበት ሁኔታ ሁል ጊዜ ፍርሃትን ስለሚያጭርባቸው ጠዋትና ማታ ከቤቱ ጎራ እያሉ ይጎበኙታል። ከእለታት በአንደኛው ምሽት እንደልማዳቸው ወደ ኮይሻ ቤት ብቅ በማለት ቢመለከቱ በሩ ተዘግቷል። ኮይሻ ከቤቱ አልገባም። መጥፎ ስሜት ከውስጣቸው እያንዣበበ ሁኔታው አላምር ያላቸው እኚሁ ጎረቤቱ ይመጣል እያሉ ምሽቱን ሙሉ ቢጠብቁም ሳይመጣ ቀረ። ከቤቱ ውጭ አድሮም ሆነ ሳይነግራቸው የትም ሄዶ የማያውቅ በመሆኑ አንዳች ነገር ሳይሆን እንዳልቀረ በመጠርጠር በነጋታው ለፖሊስ ጣቢያ አመለከቱ። የፈሩት አልቀረም ነበር ኮይሻ እራሱን ስቶ ከመንገድ ላይ ወድቆ እንደነበር፣ እንዲሁም ወደ ሆስፒታል ስለመወሰዱ ሰሙ።

በሆስፒታል ውስጥ ከአፉ ላይ ኦክስጂን ተጠምዶ፣ ከችግር ጋር ሲታገል የከረመው ነፍስና ሥጋው አሁን ደግሞ ከሞት ጋር ፍትጊያ ተያያዘ። በዚህ ወቅት የብሔራዊ ቲያትር አባል የነበሩት ድምጻዊ አረጋኸኝ ወራሽና ፀጋዬ እሸቱ ወደ ሆስፒታሉ በመምጣት ኮይሻ ዳግም ቆሞ እንዲሄድ ጥረት ቢያደርጉም የኮይሻ ሁኔታ ግን እርሱን ለመርዳትና አለሁልህ ብሎ ከጎኑ ለመቆም ዳግም ዕድል የሚሰጥ አልነበረም። ኮይሻ ሌላ አልበም ለመሥራት እየተፍጨረጨረ በነበረበት በዚህ ጊዜ እቅዱ ሁሉ መና ቀረና በዚያው ወደ ማይመለስበት የሞት ዓለም ነጎደ። የአሳዛኙ ድምፃዊ ፍጻሜ በሚያሳዝን መልኩ ተጠናቀቀ። በ2010 ዓ.ም ኮይሻ በ50 ዓመቱ ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ።

ኮይሻ በሕይወት ሳለ በሠራቸው የሙዚቃ ሥራዎች ያበረከተው በጣም ብዙ ቢሆንም፣ ነገር ግን ለምን ምንም ዓይነት ሽልማት ሊበረከትለት እንዳልቻለ የብዙ ሰዎች ያልተመለሰ ጥያቄ ነው። ሌላው ቀርቶ የወላይትኛ ሙዚቃ በመላው ሀገሪቱ ተወዳጅ እንዲሆን ባደረገበት የትውልድ መንደሩ እንኳን ከሚገባው ጥቂቱን አለማግኘቱ ኮይሻ በኢትዮጵያ የሙዚቃ ታሪክ ውስጥ ውለታው ተቀብሮ የቀረ አሳዛኝ ድምፃዊ ያደርገዋል። በመላው ኢትዮጵያ እየዞረ ሥራዎቹን ያላቀረበበትም ሆነ ያልረገጠው መሬት አልነበረም። ጣፋጭ የሆኑ ሙዚቃዎችን አበርክቶ መራራ ሕይወትን የኖረ አሳዛኝ የጥበብ ሰው ኮይሻ ሴታ።

# ዓለም አቀፍ

## ትራምፕ የአሜሪካን የኒውክሌር ሚስጥሮች የያዙ ሰነዶች ወስደዋል በሚል ክስ ቀረበባቸው

የቀድሞው የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ዶናልድ ትራምፕ የአገራቸውን የኒውክሌር ሚስጥሮችን እና ወታደራዊ እቅዶችን ጨምሮ በመቶዎች የሚቆጠሩ ሰነዶችን አላግባብ በመያዝ ክስ ቀረበባቸው። በትራምፕ ላይ በቀረበባቸው 37 ክሶች መሠረት ትራምፕ እነዚህን ሰነዶች በፍሎሪዳ በሚገኘው ቤታቸው መታጠቢያ ክፍሎች አስቀምጠዋል እንዲሁም ለመርማሪዎች ሐሰት ተናግረዋል።

በተጨማሪም በሰነዶቹ አያያዝ ላይ የሚደረገውን ምርምራ ለማደናቀፍ ሞክረዋል ይላል ክሱ። በአውሮፓውያኑ አቆጣጠር 2024 በሚደረገው የፕሬዚዳንትነት ምርጫ እወዳደራለሁ ያሉት ትራምፕ "ምንም አይነት ጥፋት አልፈጸምኩም" ሲሉም አስተባብለዋል።

ክሱ በሳቸው ላይ ብቻ ሳይሆን በግል ረዳታቸው ዋልት ናውታም ላይ ነው። የቀድሞ የዋይት ሐውስ ወታደራዊ ዝግጅት አስተናባሪ የነበሩት ረዳታቸው ከአሜሪካው የፌደራል ምርመራ ቢሮ ኤፍቢአይ ሰነዶችን ለመደበቅ ሞክረዋል የሚልም ክስ ቀርቦባቸዋል። 49 ገጾችን የያዘው ይህ ቅጽ በቀድሞ የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ ቀረበ የተባለውንም የፌደራል ክስ ይዟል።

ትራምፕ በግላቸው ይዘውታል የተባሉት ሚስጥራዊ ሰነዶች የአሜሪካ የኒውክሌር ፕሮግራሞች፣ የአሜሪካ እና የውጭ አገራት የጦር መሣሪያዎችና የመከላከያ አቅም፣ አሜሪካ እና አጋሮቿ በወታደራዊ ጥቃቶች ሊኖራቸው የሚችል ተጋላጭነትና ለውጭ ጥቃት ምላሽ ሊሆን የሚችል አጸፋዊ ምላሽ እቅዶችን አካቷል።

ትራምፕ ሥልጣናቸውን ሲለቁ ወደ 300 የሚጠጉ ሚስጥራዊ ፋይሎችን በፓልም ቢች ወደሚገኘው ማር አ ላጎ ወደተሰኘው ቤታቸው መውሰዳቸውን አቃብያነ ሕግ ተናግረዋል። በውቅያኖስ ዳርቻ የሚገኘው ይህ ቤታቸው ታዋቂ የሆኑ ሰዎች ክበብ መሆኑም ተነግሯል።

በዚህ ቤታቸው በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ አባላት እና እንግዶች የተስተናገዱበት ሲሆን በአንደኛው አዳራሽም እነዚህ ምስጥራዊ ሰነዶች እንደተገኙም ክሱ ጠቅሷል። ትራምፕ እነዚህን ደብዛቸው ጠፍቷል የተባሉ ሰነዶችን ጠበቃቸው "ደብቀዋቸዋል ወይም አጥፍተዋቸዋል" በሚልም የኤፍቢአይን ምርመራ ለማደናቀፍ



መሞከራቸውንም አቃብያነ ሕጉ በተጨማሪ አስረድተዋል።

"እዚህ ምንም የለም ብለን ብንነግራቸው አይሻልም ወይ?" ብለው ትራምፕ ለአንዱ ጠበቃቸው አስተያየታቸውን እንደሰጡ በክሱ ላይ መመላከቱን ቢቢሲ ዘግቧል።



## አውሮኘላን ከተከሰከሰ ሳምንታት በኋላ አራት ልጆች በሕይወት ተገኙ


በካምቦዲያ የተሳፈሩበት አውሮኘላን ከተከሰከሰ ሳምንታት በኋላ አራት ልጆች በሕይወት መገኘታቸው ተገልጿል። ከካምቦዲያ ነባር ጎሳ ማኅበረሰብ የሚገኙት አራት ልጆች ሲበሩበት የነበረው አውሮፕላን ጫካ ውስጥ ከተከሰከሰ አምስት ሳምንታት በኋላ በሕይወት መገኘታቸውን የሀገሪቱ ፕሬዚዳንት ጉስታቮ ፔትሮ ተናግረዋል።

የካምቦዲያ ጦር ልጆቹን አውሮኘላኑ በተከሰከሰበት አቅራቢያ በካኩይታ እና ጓቬሬ ግዛት አዋሳኝ ላይ ማግኘት ችሏል። ሰባት ሰዎችን አሳፍሮ በአማዞን ግዛት ውስጥ ሲጓዝ የነበረው አውሮፕላን ሞተሩ በመበላሸቱ የአደጋ ጊዜ ጥሪ አሰምቶ ነበር። በአደጋው አብራሪውን ጨምሮ ሦስት ጎልማሳዎች አስከሬን በአውሮፕላኑ ውስጥ ተገኝቷል። የ13፣9፣4 ዓመት ልጆች እንዲሁም የ12 ወር ሕጻን በሕይወት ተርፈዋል።

ፕሬዚዳንት ፔትሮ በካምቦዲያ ጫካ ጠፍተው የነበሩት ልጆች መገኘት ለሀገሪቱ ትልቅ ደስታ ነው ብለዋል። ሕጻናቱ አሁን ላይ በድካም ውስጥ መሆናቸውን እና የሕክምና ባለሙያዎች ሁኔታቸውን እንዲያዩ እንደሚደረግ ፕሬዚዳንቱ ገልጸዋል።

በአነፍናፊ ውሾች የታገዙት የነፍስ አድን ሠራተኞች ልጆቹ ሲበሉት ከነበረው አትክልት የወዳደቀ ፍራፍሬ ቀደም ሲል አግኝተው ነበር። የካምቦዲያ ጦር እና አየር ኃይል አውሮፕላኖች በፍለጋው መሳተፋቸውን አል ዐይን ዘግቧል።

# ስፖርት



# የአንጋፋው ቦክሰኛ ፈርጣማ ክንዶች ይጣራሉ

**ዓለማየሁ ግዛው**

ኢትዮጵያ በኦሊምፒክ መድረክ የዓለም ሕዝብ ፊት በክብር እንድትቆም ያደረጉ በርካታ ባለውለታዎች አሏት። በተለያዩ የስፖርት ዓይነቶች በየዘመናቱ በትውልድ ቅብብሎሽ ስመ ገናናነቷን ጠብቃ እንድትራመድ እልፍ ጀግኖች ዋጋ ከፍለዋል። ከነዚህም ባለውለታዎች መካከል "የኋላው ከሌለ የለም የፊቱ "እንደሚባለው የመጀመሪያው የኦሊምፒክ ተሳታፊ ቦክሰኛ በቀለ ዓለሙ በቅጽል ስሙ (ጋንች) ተጠቃሽ ነው።

የቶኪዮ እና ሜክሲኮ ኦሊምፒክ ተሳታፊ እንዲሁም የአፍሪካ ሻምፒዮን የሆነው ቦክሰኛ በቀለ ዓለሙ (ጋንች) ለኢትዮጵያ ቦክስ ስፖርት እድገት ፋና ወጊ በመሆን የሚይተካ ሚናን ተጫውቷል። በኢትዮጵያውያን የቦክስ አድናቂዎች ዘንድ ትልቅ ስም መገንባት የቻለ ቦክሰኛም ነው።

ቦክሰኛው የተወለደው እአአ በ1941 ሲሆን የቦክስ ስፖርትን አሐዱ ብሎ የጀመረው ፊልም በማየት ነበር። የቦክስ ፌዴሬሽንና ክለቦች ከመቋቋማቸው በፊት ባለተሰጥዖ መሆኑን አሳይቷል። በአማተር ደረጃ በርካታ ብሔራዊ ሻምፒዮናዎችን አሸንፏል። በቀለ ዓለሙ (ጋንች) የቦክስ ክለቦች ባለመኖራቸው ለበርካታ ጊዜ በቅዱስ ጊዮርጊስ ስፖርት ክለብ ስም ይወዳደር ነበር። በዘመኑ በዓለም አቀፍ መድረክ ታላቅነትን የማስመዝገብ አቅም ያለው ከፍተኛ ቦክሰኛ መሆኑንም አሳይቷል። አፍሪካውያን ከነጮች ጋር በስፖርት መሳተፍ ይቅርና አብሮ መታየት ወንጀል በሆነበት ዘመን እሱ ግን በቦክስ ሪንግ ውስጥ ያስመዘገበው ድንቅ ሥራና ስኬት በዓለም አቀፍ ደረጃ በቦክስ አድናቂዎች ዘንድ እውቅና አስገኝቶለታል።

በቀለ አፍሪካ ውስጥ የሚካሄዱ የቦክስ ውድድሮችን በመሳተፍ የአፍሪካ ቦክስ ሻምፒዮን መሆን ችሏል። የአህጉሪቱን የቦክስ ስፖርት እንዲነቃቃና እንዲስፋፋም አድርጓል። ከአህጉሪቱ በጣም ከባድ የሆኑትን የመካከለኛ ሚዛን ቦክሰኞች በመፋለምም ጥንካሬውን አስመስክሯል።

እአአ ለ1960 የሮም ኦሊምፒክ ሀገሩን ለመወከል የተመረጠ ቢሆንም በወቅቱ የቦክስ ልዑክ በመቀነሱ ምክንያት ሳይሳተፍ ቀርቷል። ቢሆንም በቀለ ውስጥ ባለው እንከን የለሽ ችሎታውና በራስ መተማመን ተመስግኖ ታላቅ አድናቆትን አግኝቷል። ለጥቁሮች አይሆንም፤ ከነጭ ቦክሰኞች ጋር መፋለም ንቀት ነው ተብሎ ለነጮች ብቻ የተባለውን የቦክስ ስፖርት ጥቁሮችም አቅም እንዳላቸው በማሳየት በቃላት ሊገለጽ የማይችል ውለታን ውሏል።

በቀለ ቦክስን አጠናክሮ በመቀጠል እአአ በ1964 የቶኪዮ ኦሊምፒክ ተሳትፎውን ማድረግ ችሏል። ወደ ውድድሩ ቀለበት ሲገባ ያለውን ፍትሐዊነት የጎደለው አመለካከት አይቶ ተስፋ አልቆረጠም። ሪንጉ ውስጥ ገብቶ በኩራት ተቧቅሷል። አሠልጣኝና ትጥቅ ባይኖረውም ተስፋ ሳይቆርጥ ተሳትፎውን አጠናክሮ ቀጥሏል።

ልምዱንና በራስ መተማመኑን በመጠቀም በ1968 የሜክሲኮ ኦሊምፒክ በመካከለኛ ሚዛን ዲቪዚዮን ከታላቋ ብሪታኒያ ተፋላሚ ጋር ተፋልሟል፣ ውጤት ባይቀናውም። በቀለ በኦሊምፒክ ለመሳተፍ ያደረገው ጉዞ ቀላል አልነበረም። ከፍተኛ ደረጃ ላይ ለመድረስ እና የሦስት ጊዜ የኦሊምፒክ ተሳታፊ ለመሆን ሁሉንም ችግሮች መታገል ነበረበት። የገንዘብ እጥረቶችን፣ የባለሥልጣናት ድጋፍ እጦትን፣ የግብዓት እጥረትንና የወቅቱን የነጮች እይታን ማሸነፍ ነበረበት። መንፈሱ በዚህ ባለመታወኩም ጠንክሮ ሠልጥኖ ግቡ ላይ ነበር ትኩረት ያደረገው።

የእሱ ስኬት በኢትዮጵያም ሆነ በአጠቃላይ በአህጉሪቱ



**አንጋፋው ቦክሰኛ በቀለ ዓለሙ (ጋንች) በቅዱስ ጳውሎስ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል በፀና ታሞ ይገኛል፣**

ያሉ ወጣት ቦክሰኞችን አነሳስቷል። ምንም እንኳን ንቁ የቦክስ ሕይወቱ ከብዙ ቆይታ በኋላ ቢያበቃም፤ በቀለ አፍሪካውያን ወጣቶችን ማበረታታቱን ቀጥሏል፤ ለስኬቶቹም እውቅና አግኝቷል። ይህም በአህጉሪቱ ከተፈጠሩት ታላላቅ ቦክሰኞች አንዱ በመሆን አሻራውን አስቀምጧል።

በቀለ ዓለሙ አስደናቂ የቦክስ ዓለም መሪነት ጉዞን ከጀመረ ዓመታት ተቆጥረዋል ነገር ግን ታሪኩ ትውልድን በማነሳሳቱ ቀጥሏል። የእሱ ስኬቶች በትጋት እና በማያወላውል ቁርጠኝነት ሊከፈት ለሚችለው አቅም ምስክር ሆነው ይቆያሉ። በስፖርታዊ ጨዋነት ያበረከተው ትሩፋት በቁጥር አይገመትም። ፈር ቀዳጁ ቦክሰኛ የኢትዮጵያን ቦክስ በዓለም አቀፍ ካርታ ላይ አስቀምጦ ለታላላቅ አትሌቶች አርዓያ ሆኗል።

የቀደሙት ስፖርተኞች ምንም እንኳን ፈር ቀዳጆችና ግንባር ቀደም መሆን ቢችሉም ከራሳቸው ሀገርን በማስቀደም የሚችሉትን አበርክቷል። ለስፖርቱ ከከፈሉት ዋጋ አንጻር ያገኙት ትርፍ የሕዝባቸውን ፍቅርና አድናቆት ብቻ ነው። በመሆኑም ቤተሰባቸውን ለማስተዳደርም ሆነ ለራሳቸው የሚበቃ በቂ ገንዘብ ማፍራት አልቻሉም። ከዛም አልፎ የጤና ችግር እንኳን ሲገጥማቸው መታከሚያ ገንዘበ በማጣት አጋዥ ፍለጋ እጃቸውን ሲዘረጉ ይስተዋላል።

እንዳለመታደል ሆኖ ፈር ቀዳጁ ቦክሰኛ በቀለ ዓለሙ (ጋንች) ዕጣ ፋንታም ከዚህ የተለየ አልሆነም። ጠንካራ ቡጢ የሚሰነዝሩ ክንዶቹ ዝለው ዛሬ ላይ የአልጋ ቁራኛ ሆኗል። በጠና ሕመም ውስጥ ሆኖም የያኔው ፈርጣማ ክንዱ ከስፖርት ቤተሰቡ እርዳታ እንዲጠይቅ ተገዷል። በአሁኑ ወቅት ሕመሙ ስለጸናበት በቅዱስ ጳውሎስ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ተኝቶ እየታከመ ይገኛል። ይህን ታላቅ አርዓያና የሀገር ባለውለታ ለመታደግም የሁሉንም ስፖርት ቤተሰብ ርብርብ ያስፈልጋል።

በቀለ ዓለሙ የሕክምናው ወጪ ከፍተኛ በመሆኑ ቤተሰቦቹና ጓደኞቹ ኅብረተሰቡ እና በጎ ፍቃደኞች እንዲረዱት እና የሕክምና ወጪውን እንዲሸፍንለት ይጠይቃል። በዓለም ዙሪያ ያሉ የቦክስ አፍቃሪዎች ለበቀለ ዓለሙ (ጋንች) የሕክምና ገንዘቡን በማዋጣት ድጋፋቸውን እንዲያደርጉ ጥሪ ቀርቧል። አሁን የስፖርት ማኅበረሰቡ ከጎኑ በመቆም ለሕክምና የሚያስፈልገውን ገንዘብ አስተዋፅዖ በማድረግ ድጋፉን የሚገልጽበት ጊዜ ነው። የቦክሰኛው የጤና ሁኔታ በጣም አሳሳቢ በመሆኑ ማንኛውም ድጋፍ የወደፊት ሕይወቱን ለማስቀጠል እጅግ አስፈላጊ ብቻ ሳይሆን የአገር ባለውለታን ማስታወስ ነው።




# የአፍሪካ ሕፃናት ቀን ለሕጻናት

**ጽጌረዳ ጫንያለው**

ሰላም ልጆች እንዴት ናችሁ፤ ትምህርት እንዴት ይዟችኋል? መቼም በጣም ጥሩ ነው የሚል መልስ እንደምትሰጡኝ አምናለሁ። ምክንያቱም ጎበዝና ቤተሰቡን የሚሰማ ልጅ በትምህርቱ ውጤታማ አለመሆን አይችልም። ይህ ደግሞ ዘወትር ደስታን ይፈጥርለታል። ደስታ አለ ማለት ደግሞ ምኞት ሁሉ ጥሩ ይሆናል። ከዚህ አንጻርም ትምህርት እንዴት ነው ስትባሉ ሁልጊዜ መልሳችሁ በጣም ጥሩ ነው የሚል ይሆናል።

ልጆች ለዛሬ ይዤላችሁ የቀረብኩት ሀሳብ የምታውቁት ቢሆንም ቀናችሁን ምክንያት አድርጎ ማንሳት ጠቀሜታው የጎላ ነውና ስለ ሰኔ 9ኝ እናወራለን። እንደምታውቁት ሰኔ 9 የአፍሪካ ሕፃናት ቀን ተብሎ በዓለም አቀፍ ደረጃ ጭምር ይከበራል። ይህ ቀን እንዴትና ለምን ተመረጠ ካላችሁ ትንሽ ነገር በጉዳዩ ዙሪያ ያነበብኩትን ላካፍላችሁ።

ቀኑ ታስቦ የሚከበርበት ምክንያት በአፓርታይድ ጊዜ በደቡብ አፍሪካ መብታቸው እንዲከበር የጠየቁ ሕፃናት በግፍ ስለተጨፈጨፉ እነርሱን ለማሰብ በሚል ነው እንዲከበር በአዋጅ ጭምር የተቀመጠው። ስለዚህም በየዓመቱ ጁን 16 ቀን በእኛ ደግሞ ሰኔ 9 ዕለቱ ታስቦ ይውላል። የአፍሪካ ሀገራት ሕጻናትም ቀኑን በተለያየ ዝግጅት ያከብሩታል። እኛ ሀገርም ቢሆን እንዲሁ ቀኑን በማሰብ በተለያየ መሪ ሀሳብና ዝግጅት ይከበራል።

ቀኑ ታስቦ እንዲከበር ውሳኔውን ያስተላለፈው የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ሲሆን፤ በ26ኛ መደበኛ



የሀገራትና የመንግሥታት የመሪዎች ጉባኤያቸውም ነው ውሳኔን እንዲያስተላልፉ የሆኑት። ዓመቱ ደግሞ ጁላይ 1990 ነው። የአፍሪካ ሕጻናት መብቶች ደህንነት ቻርተር ከኖቬበር 29 ቀን 1999 ጀምሮ ቻርተሩን ባፀደቀው ሀገሮች ሥራ ላይ ውሏል። ይህም ቻርተር በኢትዮጵያ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ኦክቶበር 2 ቀን 2002 ከፀደቀ በኋላ የመቀበያ ሰነዱ በቻርተሩ አንቀጽ 47(2) መሠረት ዲሴንበር 27 ቀን 2002 የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ዋና ፀሐፊ ቢሮ ገቢ ሆኗል። ስለሆነም በቻርተሩ አንቀፅ 47(3) መሠረት ከጃንዋሪ 2003 ጀምሮ በኢትዮጵያ ሥራ ላይ ውሏል። በዓሉም መከበር የጀመረው ከዚህ ዓመት ጀምሮ እንደነበር መረጃዎች ያሳያሉ።

ለመሆኑ ልጆች ይህ ቀን መከበሩ ምን ጥቅም አለው ማለታችሁ አይቀርም። ጥቂት ስለበዓሉ መከበር ደግሞ እናንሳ። አንዱ የሕፃናትን ደህንነትና ጥቅም ማስጠበቅ ማስቻሉ ሲሆን፤ እንዴት ካላችሁ የእያንዳንዱ ሀገር ግዴታ እንዲሆን በተፈራረሙት ቻርተር አስቀምጠዋልና በቻርተሩ ላይ ያለውን ተግባር እንዲከውኑ ስለሚገደዱ መብታቸው የተከበረ መሆኑን ለማረጋገጥ ያስችላል። ለሕጻናት ጉዳይ ሁሉም ሀገር የበለጠ ትኩረት እንዲሰጥም ያደርጋል።

በአስቸጋሪ የኑሮ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙና ከችግራቸውም ለመውጣት የሁሉም አካላት ተሳትፎን ለሚሹ ልጆች በቀላሉ እንዲደረስላቸው ዕድል ይሰጣል። ማኅበረሰብን መሠረት ያደረገ ድጋፍ ለማድረግም ወሳኝነት አለው። ይህ ሲባል ሕፃናት ቀያቸውን ሳይለቁ በሚኖሩበት አካባቢ ደስተኛ ሆነው እንዲቀጥሉ ያግዛቸዋል። በማኅበረሰብ ላይ የተመሠረተ የሕፃናት እንክብካቤ እንዲኖርም ያስችላል። በተጨማሪም ቀኑ ሲታሰብ በርካታ ሕፃናትን ለመድረስ እድል ያመቻቻል።

ከሁሉም በላይ ደግሞ ልጆች በሚያደርጉት እንቅስቃሴ ልዩ ተሰጥዖዋቸውን እንዲያወጡበት ያደርጋቸዋል። ምክንያቱም ዕለቱ ሲከበር የተለያዩ ዝግጅቶችን የሚያደርጉት የበዓሉ ባለቤት የሆኑት ሕጻናት ናቸው። እናም ወግና ባሕላቸውን አውቀውና ጠብቀው የአዲስ ፈጠራ ባለቤት እንዲሆኑ ያስችላቸዋል። ልዩ ፍላጎታቸውን እንዲያውቁም ዕድል ይሰጣቸዋል።በተመሳሳይ የፈጠራ ሥራቸውን በማሳየት ወላጆች እንዲሁም ማኅበረሰቡ እንዲደግፋቸውና እንዲደሰትባቸውም ያደርጉበታል።

ራሳቸውም ቢሆን ተጠቃሚ የሚሆኑበትን ዕድል ይፈጥሩበታል። ምክንያቱም በዕለቱ በሚፈጠረው የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራ መሠረታዊ መብትና ግዴታቸውን እንዲያውቁበት ይሆኑበታል። ፍላጎቶቻቸውን ተረድተው በቀጣይ እንዲያጎለብቱበት መንገድ ይጠርግላቸዋል።

ልጆች ለመሆኑ ሰኔ 9 ቀን የአፍሪካ ሕፃናት ቀን ሆኖ ሲከበር ዘንድሮ ለስንተኛ ጊዜ እንደሆነ ታውቃላችሁ ? በአፍሪካ ደረጃ 33ኛ ጊዜ ነው። በሀገር አቀፍ ደረጃ ደግሞ ለ32ኛ ጊዜ በተለየ መሪ ሀሳብና ዝግጅቶች ይከበራል። እናም ይህ ሁሉ ጥቅም እንዳለው አውቃችሁ በዓሉን በፍቅርና በደስታ ማክበር ይኖርባችኋል። መልካም በዓል በማለት በሚቀጥለው ሳምንት በሌላ ጉዳይ እስከምንገናኝ ለዛሬ የያዝኩትን ሀሳብ ልቋጭ። መልካም ሰንበት!!